# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፩ኛ ዓመት ቁጥር ፩ መስከረም/ጥቅምት ፲፱፻፺፮ ዓ.ም




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## በዚህም መጥተዋል

ሐምሌ 19 ቀን የቅዱስ ገብር ኤልን በዓል ለማክበር በሄድሁበት አንድ ደብር የገጠመኝ ነው:: ካህናቱ ዋዜማ ቆመው እንደ ወጡ የቤተ ክርስቲያኑ ድምፅ ማጉያ ሳይዘጋ አንድ ወጣት ዜ ማውና ግጥሙ ከዚህን ቀደም ስናዳምጠው የነበረውን መዝሙር ካሴት፣ ነገር ግን የእኛ የሆነውን ንዋያተ ማኅሌት በመቀየር በኪ ቦርድ እና በኦርጋን የታጀበ «መዝሙር መሰል» ዜማ ከፈተ:: ወዲያውኑ በነገሩ ያዘኑት የቤተ ክርስቲያኑ ዲያቆናት ቴፑ እንዲዘጋ አድርገው የካሴቱን ባለቤት ጠርተው ቢጠይቁት እኔ መዝሙሩን ከዚህን ቀደም የማውቀው ግጥም እና ዜማ ስለሆነ ነው የገዛሁት አለን:: መናፍቃኑ ዜማና ግጥማችንን ሳይነኩ የሙዚቃ መሣሪያዎቻቸውን ለጆሮዎቻችን ለማለ ማመድ በዚህ የማታለያ ዘዴ መጥተዋልና ጠንቀቅ ማለቱ ይበጃል እላለሁ::

*የኳላሸት ተሾመ*
*ሚዛን ተፈሪ*

## «ቢዚ» ነኝ

*ካለፈው የቀጠለ*

በቀን ውሎአቸው አምላካቸውን እንዳያስቡ ሳይታወቃቸው ከአምላካቸው በሀሳብም በግብርም እንዲርቁ መላ ፍጠሩ:: ባሎች ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር የሚነጋገሩበትና የሚወያዩበት ጊዜ እንዳይኖራቸው፣ ልጆቻቸውን ለመምከርና ለመቆጣጠር ጊዜ እንዲያጡ አድርጉ:: በመዝናኛ ሥፍራ፣ በየመኳኳሪያው ሁሉ ሥጋዊ ስሜታቸውን የሚያነሣሱ ሙዚቃዎችንና ፊልሞችን አቅርቡላቸው:: የቡና ጠረጴዛዎች፣ ለአሉባልታና በዋዛ ፈዛዛ ጊዜ ማሳለፊያ ወሬዎች የተመቻቹ እንዲሆኑ በተቻላችሁ ሁሉ ጥረት አድርጉ:: ዓይናቸው ከቴሌቪዥን መስኮት /ስክሪን/ ላይ ሳይነቀል በተቀመጡበት እንዳሉ ውለው እንዲያመሹ፣ በተለያዩ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች እና የቪዲዮ ካሴቶች ለሥጋዊ ስሜታቸው ለዝሙት የሚያነሣሡ ፊልሞችን እንዲያዘጋጁ በማበረታታት በሰፊው አቅርቡላቸው:: ፖስታ ሣጥናቸው በተለያዩ የሐሰት ማስታወቂያዎች ይሞላ:: በሐሰት ማስታወቂያዎች ፍሬያማ የማይሆኑ ተስፋዎችን አቅርቡላቸው:: እርሱን ሲጠባበቁ ከሁሉም ይዘገያሉ:: ወንዶች በሚስቶቻቸው የማይደሰቱና ቆንጆዋን ፍለጋ ወደ ዝሙት እንዲጓዙ አበረታቱ:: የተለያዩ መሸታ ቤቶች፣የምሽት ክበባት እንዲቋቋሙ ሴተኛ አዳሪነት እንዲስፋፋ በተቻላችሁ ሁሉ ድጋፍ አድርጉ:: ወጣቱንም ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ ሰንበት ት/ቤት መሄድን እንዳያስብ በተለይ ከፍራሽ ጋር ተጣብቆ እንዲውል ጫት ቤቶች በብዛት እንዲስፋፉ አድርጉ::

ሕፃናቱም ቢሆኑ በገና ወቅት የገናን ዛፍ በመሥራት፣ በገና አባት ስጦታ እንዲታለሉና የገናን እውነተኛ ታሪክና መልእክት እንዳይረዱ ዘዴ ፍጠሩ:: በትንሣኤ ፋሲካም ስለሚበላውና ስለሚጠጣው ስለ ዶሮው፣ ስለ በጉ፣ ስለ ቅርጫው እንዲያስቡ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ያገኙትን ሕይወት ችላ እንዲሉ፣ በበሉትና በጠጡትም ነገር ጨጓራቸውን እንዲታመሙ ከሐኪም ቤት ሐኪም ቤት እንዲንከራተቱ መጠጡን አብዝተው እንዲወስዱ በስካር ናላቸው እንዲዞር አበረታቱ:: ከሐኪም ቤት ሐኪም ቤት እንዲንከራተቱ ምክንያት ፍጠሩ::

ከዚህ ሁሉ መሰናክል አምልጠው ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢሄዱ እንኳን ሌላውን በመጠበቅ ጊዜያቸውን እንዲያሳልፉ ቢገናኙም በወሬ ጊዜያቸውን እንዲጨርሱ፣ በአሥራር፣ በኃላፊነት ጉዳይ፣ በገንዘብ ነክ ነገሮች ላይ እንዲጨቃጨቁ፣ በዘር በጎጥ በመከፋፈል ዘራቸውን፣ ጎጣቸውን በመጠበቅ የሥራ ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው የሥራ ጊዜያቸውን ብቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ሳለ ወንድማቸውን በማማት፣ በአንዱ በመፍረድ፣ ሌላውን በመኮነን የጸሎት ጊዜያቸውን እንዲጨርሱ በትጋት ሥሩ::

በተቻለ መጠን ሥጋዊ ሕይወታቸው የተሟላ ይሁን:: ምናልባትም ስላልገዙት መኪና፣ ስላልሠሩት ቤት እንዲጨነቁና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ጥሩ ገንዘብ ሊያገኙ የሚችሉበትን የጥፋት መንገድ መልካም አስመስላችሁ አቅርቡላቸው:: ሁልጊዜ ሥጋዊ ሕይወታቸው የሚጎድለው ነገር እንዳለ አሳዩአቸው:: ይህንንም ለማሟላት ቀን ከሌሊት በአሳብ እንዲወጠሩ፣በየማይሳካ ተስፋ እና ዕቅድ ላይ ታች እንዲዋትቱ ገፋፏቸው በበዓላት ቀን በover time እንዲሠሩ ገፋፏቸው:: ይህም Busy ያደርጋቸዋል:: መንፈሳዊውን ነገር ከመፈጸም ፍጹም ተዘናግቶ Busy መሆንም በዲያብሎስ ቀንበር ሥር ለመውደቅ መንገዱ ያመቻቻል::

የስብሰባው ተሳታፊዎች ፐየሆኑት አጋንንት በአንድ ድምፅ ዕቅዱንና ስልቱን ለመፈጸም አጨብጭበው ተለያዩ:: ሁሉም የሚያገኙትን ሰው Busy ለማድረግ ተሥማሩ::» ብሎኝ በረጅሙ ተነፈሰ::

መቼም ሲነግረኝ በስብሰባው ላይ የተሳተፈ ይመስል ነበር:: ማን ነገረህ? አልኩት:: አንዱ ጋኔን ለወዳጁ ሲነግረው ነው የሰማሁት አለኝ:: ለመሆኑ Busy የሚለውን ቃል ትርጉም ታውቃለህ? አለኝ:: በፍጹም:: ይኸውልህ:–

B- Being
U- Under
S- Satan
Y- Yolks /በዲያብሎስ ቀንበር ሥር መዋል/ ማለት ነው:: ሾውረኝ አለ፥ መንገደኛው:: ልቡናዬ ለካስ እንዳች ሳልሠራ ቀኑን በሙሉ በሐሳብ ተወጥሬ፣ ከቦታ ቦታ በመመላለስ፣ ዘመኔን በዙረት የምጨርሰው ሳልሠራ የሠራሁ የሚመስለኝ፣ ሳልሠራ የሚደክመኝ፣ ለመጸለይ፣ ቃለ እግዚአብሔር ለመማር፣ የታመመ፣ የታሰረ ለመጠየቅ፣ ያዘነ የተጨነቀ ለማጽናናት ጊዜ የለኝም፣ «Busy» ነኝ የምለው በሰይጣን ቀንበር ተይገ ኑሯል? አለ መንገደኛው ልቤ:: ደኅና ሁኑ:: ወስብሐት ለእግዚአብሔር•


## ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ እና «አዋልድ መጻሕፍት እና መንፈሳዊነት በግቢ ውስጥ»

የሚሉ መጻሕፍት በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል ተዘጋጅተው በመሠራጨት ላይ ይገኛሉ:: ሁለቱንም በማኅበሩ የሐመር እና ስምዐ ጽድቅ ማከፋፈያዎች ያገኟቸዋል::

☎ 565159


| የኅትመት ውጤቶች ማከፋፈያዎቻችን | |
|---|---|
| ከተማ | ስልክ |
| ጎንደር | 08 - 116240 |
| ባሕር ዳር | 08 - 204444 |
| ደብረ ማርቆስ | 08 - 713961 |
| ፍቼ | 01 - 351199 |
| መቀሌ | 04 - 409761 |
| ናዝሬት | 04 - 409761 |
| አርባ ምንጭ | 06 - 811597 |
| ሻሸመኔ | 06 - 104795 |
| አዋሳ | 06 - 202173 |
| ጅማ | 07 - 114275 |
| ደሴ | 03 - 117545 |
| አሶሳ | 07 - 751222 |
| ድሬዳዋ | 05 - 120493 |
| ነቀምት | 07 - 614322 |

አዲስ አበባ 01-565159/ 573726
መ.ሣ.ቁ. 80078 ማኅበረ ቅዱሳን

### የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለባለው ታደለ እና/ወይም መስፍን ጥላሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ
Balew Tadelle and/or Mesfin Tilahun
የባንክ ሒሳብ ቁጥር 68608 አዲስ አበባ ከፍለው
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ

መስቀል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በላዩ ላይ ተሰቅሎ ከመቀ ደሱና ከመክበሩ በፊት የውርደትና የንቀት ምልክት ነበር:: የመስቀል ሞት የሚፈረድባቸው በጣም ክፉዎችና ዓመፀኞች ነበሩ:: ዘፍ.40÷18:: የፋርስ ሀገር ሰዎች የመሬት አምላክ /አርሙዝድ/ የሚባል ጣዖት ያመልኩ ስለነበር ክፉ ሰው በመሬት ከተቀበረ አምላካችን ይረክሳል ሲሉ ከፍ አድርገው በመስቀል ላይ ይሰቅሉ ነበር:: ሮማውያንም ስለ ዜግነት ክብር ሲሉ የሮማዊ ዜግነት ያሏቸውን በስቅላት አይገድሉም ነበር:: በዘመነ ኦሪትም በእስራኤላውያን ዘንድ በእንጨት ላይ የተሰቀለ የተረገመ ነበር:: ዘዳ. 21÷22::

በረከተ ወንጌል

---

በሮም ያሉ የጣዖት ካህናትም ለአማልክቶቻችን የማይታዘዙ ክርስቲያኖች በመኖራቸው አማልክቶ ቻቸው በዚህ ተቆጥተው ይህ መቅሰፍት እንደ ደረሰ አድርገው ለሕዝቡ በመናገራቸው የሕዝቡ ጥላቻ እየገፋ እየጠነከረ መጣ:: በዚህ ጊዜ ኔሮን ክርስቲያኖችን ለማ ጥፋት አመቺ ሁኔታ ተፈጠረለት:: ብዙ ክርስቲ ያኖች ያለ ፍርድ በጭካኔ ተጨፈጨፉ:: ብርሃናተ ዓለም የተባሉት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ የሰማዕትነት ጽዋቸውን የጨለጡት በዚህ ዘመን ነው::

ኪነ ጥበብ

---

እግዚአብሔር በጎ አድራጊ ነው:: በባሕርይው በጎነ ት እንጂ ሌላ አይስማማውም:: ጨለማው ብርሃን ይሁን ያለ እግዚአብሔር ለሚወዱትና እንደ አሳቡም ለተጠሩት ሁሉን ነገር የሚያደርግላቸው ለበጎ ነው:: ቅዱስ ባስልዮስ «ለእኛ በጎ ነገርን ያደረገ ይቅር ባይ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን::...ሰውሮናልና፣ረድቶናልና፣ ጠብቆ አቅርቦ ናልና፣ ወደ እርሱም ተቀብሎናልና እስከዚህችም ሰዓት አድርሶናልና» በማለት በጎ አድራጊ እግዚአብሔርን አመስግኗል::

---

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ


ዋና አዘጋጅ - ዲ.መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ- አሉላ ጥላሁን
አዘጋጅ - ዲ. ያሬድ ገ/ መድኅን
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ
E -mail:EOC-M-KIDUSAN@ telecom.net.et.
Internet – www.telecom.net.et/~EOTC-MK


«ማኅበረ ቅዱሳን»
እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል::


ሐመር
፲፩ኛ ዓመት ቁጥር ፬
መስከረም/ጥቅምት ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.


## ይዘት


የማኅበሩ መልእክት

- የካህናት ሥልጠና ሊበረታታ÷ በቁጥርና በዓይነትም ሊጨምር ይገባል ........ ፪

ደብዳቤዎች ........ ፬

ከስሙ ኑ በረከት

- ዝክረ ቅዱሳን ........ ፮
- የእንቁጣጣሽ ሥነ ቃላዊ ዳራ ........ ፯

ትምህርተ ሃይማኖት

- ሥርዓተ ጸሎት ወስግደት ........ ፱
- እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል ........ ፲፩

የጥያቄዎቻችሁ መልሶች

- ባሕረ ሐሳብ ምንድን ነው ? ........ ፲፫
- «እንዲያው ኢትዮጵያዊ ኢየሩሳሌም ሲሉት» ........ ፲፰

ምስራፍ ........ ፳

ኪነ ጥበብ

- ሮምን እንደጐበኘኋት ........ ፳፪

እናስተዋውቃችሁ

- ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ........ ፳፬
- ቅድስት እሌኒ ........ ፳፯

የግእዝ ሥነ ጽሑፍ እኛ «እኛ» የሆንበት...ነው ........ ፳፱

ዓምደ ወራዙት

- አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል ........ ፴፪

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

- ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ........ ፴፬

ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ

- የኑፋቄው መሻ ዙር ከኬልቄዶን እስከ ቅብዐት ........ ፴፯

ስቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት ........ ፴፰


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

## የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ::

# የካህናት ሥልጠና ሊበረታታ ÷ በቁጥርና በዓይነትም ሊጨምር ይገባል!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊትና ታሪካዊት እንደ መሆንዋ መጠን አገልግሎቷም የሰፋ ነው:: ከከተማ እስከ ገጠር የተተከሉ የገዳም፣ የደብርና የገጠር መደብነት ያላቸው ከ110 450 በላይ አብያተ ክርስቲያናት፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ልዩ ልዩ ፈተና ተቋቁመውና በእምነታቸው ጸንተው በውስጣቸው የሚያገለግሉ በአጥቢያቸው የሚኖሩ ከሦስት መቶ ሺ በላይ ካህናትና፣ ከአርባ ሚልዮን በላይ ምእመናንን ይዛ ትገኛለች:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን የሚያገለግሏት እርስዋም በመንፈሳዊ ሕይወት በመምራት ልትጠብቃቸውና ልትከባከባቸው የሚገባት ግን እኒህ ብቻ አይደሉም:: ገና ወደ በረትዋ ያልተጨመሩ ሀብተ ዉልድና ስመ ክርስትና ልትሰጣቸውና ልትከታተላቸው የሚያስፈልጋት በአገር ውስጥም ይሁን በባሕር ማዶ የሚገኙ ወገኖች ብዙ ናቸው:: ከዚህም ሌላ የሀገራችን የትምህርት፣ የባሕል፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የሥነ ጥበብ ወዘተ መሠረት የነበረች እንደ መሆንዋ እኒህን ሊያ ሳዩ የሚችሉ ተቋማትን መገንባትና ማጠናከርም ይጠበቅባታል::

ይህንን ተልእኮዋን ለመፈጸም በሃይማኖት፣ በዕውቀትና በሥነ ምግባር የታነፁ አገልጋዮች ካህናት ያስፈልጓታል:: በመሆኑም ባሳለፍነው የ1995 ዓ.ም የአገልግሎት ዓመት ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲሁም ከሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በዲግሪና በዲፕሎማ ከተመረቁት ደቀ መዛሙርት ጀምሮ በብዙ የካህናት ማሠልጠኛዎችና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የካህናት ሥልጠና ተካሂዶ በግንቦት፣ በሰኔና በሐምሌ ወራት ተመርቀዋል:: ቅዱስ ሲኖዶስ ለካህናት ማሠልጠኛዎች በጀት ከመመደቡ በተጨማሪም የተወሰኑ አህጉረ ስብከትና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለአገልጋዮች ሥልጠና ልዩ ትኩረት በመስጠታቸው ሥልጠናዎቹ ካለፉት ዓመታት በተሻለ ሁኔታ ተከናውነዋል:: በዚህም በአጠቃላይ ከ404 በላይ አገልጋዮች ካህናት ተመርቀዋል::

ከቅድስት ሥላሴና ከአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጆች ጀምሮ በየደረጃው በተቋቋሙ የካህናት ማሠልጠኛዎች ድረስ የሚሰጠው ሥልጠና በገንዘብና በዐቅም ማነስ እንዳይደከም ምእመናን በገንዘባቸው በዕውቀታቸውና በጉልበታቸው መደገፍ ይጠበቅባቸዋል:: ቤተ ክርስቲያናችንም የካህናት ማሠልጠኛዎቹ ወደ ኮሌጅ ደረጃ ከፍ እንዲሉ ኮሌጆቹም ደረጃቸውንና ጥራታቸውን ጠብቀው ወደ መንፈሳዊ ዩኒቨርስቲዎች እንዲያድጉ ከወዲሁ ማሰብ ይኖርባታል:: አንድ ኮሌጅ ብዙ የጋራ የሆኑ የትምህርት ዓይነቶችን ቢያስተምርም በአንድ የትምህርት ዓይነት ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም:: መንፈሳዊ ዕውቀትን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከዘመናዊ ትምህርት ጋር አስማምተው የያዙ ምሁራን ለቤተ ክርስቲያን እጅግ በጣም ያስፈልጓታል። ስለዚህ ኮሌጆቹ ከሥነ መለኮት ትምህርት በተጨማሪ በአስተዳደር፣ በሒሳብ መዝገብ አያያዝ፣ በታሪክ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በሥነ ልቡና ወዘተ. በማሠልጠን የትምህርት አድማሳቸውን ከፍ የማድረግ ሥራ መሥራት አለባቸው። በሌላ በኩል ደግሞ አዳዲስ የካህናት ማሠልጠኛዎችን በመክፈት በየጊዜው ካህናት እንዲሠለጥኑ በማድረግ የራሳችን ስለ ኾኑት ነገሮች ሁሉ የሚፈለገውን ያህል ዐውቀው የሚያሳውቁ በተለያዩ መንገዶች ቤተ ክርስቲያንን የሚፈታተናትን ኃይል የሚመክቱ አገልጋዮችን ማፍራት ይገባል።

በዘመናዊ ትምህርት ምክንያት እየተፈጠረ ያለውን አዲሱን ጠያቂና ተመራማሪ ትውልድ ጠብቆ ለመጓዝ ከጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በተጨማሪ በዘመናዊ አቀራረብ የተዘጋጁ መንፈሳዊ ትምህርቶችን የተማረ ካህን አስፈላጊ ነው። ለዚህም ተፈጻሚነት ደግሞ በእጃችን ባለንና እንዲኖረን በምንፈልገው መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ይገባናል።

እንደሚታወቀው ባለውና በሚፈለገው መካከል ያለውን ክፍተት መሙላት ከሥልጠና ግቦች አንዱ ነው። በመሆኑም ለአበው ካህናት ሥልጠና ከመስጠቱ አስቀድሞ እነርሱ ቀድሞ ያላቸውና ዘመኑን ከመዋጀት አንጻር ከእነርሱ የሚፈለግባቸው ነገር በውል መጠናት ይኖርበታል። ከዚህም በመነሣት የሥልጠናው ዓይነት ፣ ዓላማ፣ አፈጻጸምና ግብ በዝርዝር ተለይቶ ሊታወቅ ይችላል። በሌላ በኩል ሥልጠና ተግባር ተኮር እንደ መሆኑ ከተሰጠ በኋላ የተገኘው ዕውቀትና ግንዛቤ ጥቅም ላይ ስለ መዋሉ ክትትል ማድረግ ያሻል። በተጨማሪም በአገልገሎት ~መካከል የሚሰጥ ሥልጠና /In-service training/ ቀጣይነት ያለውና የማያቋርጥ ሂደት ነው። ከዚህ አኳያ በተለይም የካህናት ማሠልጠኛዎች የሚገኙባቸው አህጉረ ስብከት በተወሰኑና በታቀዱ ጊዜያት ሁለገብ ዐውደ ጥናቶችን፣ዐውደ ትምህርቶችንና ወርክሾፖችን በየደረጃው የማዘጋጀታቸውና የካህናትን ዐቅም የማጠናከራቸው አስፈላጊነት አጠያያቂ አይሆንም።

ምእመናን መደበኛ በኾነና ባልኾነ መልኩ በየጊዜው የሚሰጡ የካህናት ሥልጠናዎችን በአሳብ፣ በሞያ፣ በገንዘብና በቁሳቁስ የመርዳት ድርሻ ይኖራቸዋል።

ያሉንን መንፈሳዊ ኮሌጆች ከማጠናከርና ከማበረታታት ጀምሮ በሁሉም አቅጣጫ የሚሠጡትን የካህናት ሥልጠናዎችን ዐቅማችን በፈቀደው ሁሉ ከደገፍን ቤተ ክርስቲያናችን የሚጠበቅባትን ታላቅ መንፈሳዊ ተልእኮ ለመፈጸም ከፍተኛ ኃይል ታገኛለች። ምእመናንም በመልካም ተግባራቸውና በሃይማኖታቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ይችላሉ። ለሁሉም የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ረድኤትና በረከት አይለየን። አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## በአግባቡ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ ዓመታዊ ክብረ በዓላት በማድረግ ቅዱሳንን ከዕለተ ክብራቸው ዋዜማ ጀምሮ በዋዜማ በማኅሌት ታዘክራለች፡፡ ታድያ ምእመናንና የሰንበት ተማሪዎች ይህንኑ በዓል ለማክበር ከምሽቱ ጀምሮ ክብረ በዓሉ በሚከናወንበት አጥቢያ ይሰባሰባሉ፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ምእመናን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ከታደሙ በኋላ የመጡበትን ዓላማ በመርሳት ለቦታው የማይገባ ወሬ ሲያወሩ፣ ከዚያም አልፎ ሌላ ተግባር ሲፈጽሙ ይታያሉ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንመጣው በቅኔ ማኅሌት አባቶች የሚያቀርቡትን ስብሐተ እግዚአብሔር በጥሙና እየተከታተልን ከቅዱሳን በረከት ለመካፈል እስከ ኾነ ድረስ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡

*ከንፈ ወ/ጊዮርጊስ*
*ሐይቅ*

## ምን ይሆን?

ባለፈው ወር በመገናኛ ብዙኃን ዜና ስሰማ የካቶሊክ ድርጅት የጉንዳ ጉንዲ ማርያም ገዳምን እንደገና ለማደስና በውስጧም ያሉት ቅርሶች እንዲመዘገቡ፤ መንገዱም እንዲሠራ የተለያዩ አካላት ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪ ማቅረቡን ሰማሁ፡፡ ከሰማሁበት ዕለት ጀምሮ አእምሮዬ አላረፈም፡፡ ሰዎችን ስጠይቅ መልስ ሊሰጡኝ አልቻሉም፡፡ ለመሆኑ ካቶሊክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጉንዳ ጉንዲ ገዳምን ለመርዳት የተነሣችበት ምክንያት ምን ይሆን?

*ገነተ ማርያም*
*ነፋስ መውጫ*

## ሐሰተኞች ነቢያት

ዕለቱ እሑድ ሰኔ 22 ቀን 1995 ዓ.ም ነበር፡፡ በዕለቱ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ «መልእክት ለዓለም» በተሰኘ ሬድዮ ዘወትር የሚተላለፍ የኑፋቄ ትምህርት ሰማሁ፡፡ አንዳንድ የዋህ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ምእመናን ለማደናበርም ተብሎ ትምህርቱ ሲቀርብ «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፡፡ አሜን፡፡» በሚል ይጀመርና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በግእዝ በማንበብና በመተርጐም ሲሆን፤ ፍጻሜው ደግሞ «ወስብሐት ለእግዚአብሔር» በሚል ነው፡፡ ይህንን ግእዝ በመቀላቀል የሚሰጠውን የኑፋቄ ትምህርት የሰሙ አንዳንድ ምእመናን ቤተ ክርስቲያናችን በሬድዮ ትምህርት ማስተላለፍ የጀመረች መስሏቸው የተወናበዱም ነበሩ፡፡ እናም ከላይ በጠቀስኩት ሬድዮ በገለጽኩት መልኩ የሚሰጠው ትምህርትና ሌሎችም ተመሳሳይ የሆኑ የሬድዮ ፕሮግራሞች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድምፅ አለመሆናቸውን ምእመናን ያውቁ ዘንድ ያስፈልጋል፡፡ «...ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ...» በማለት በማቴ.24÷24 አስቀድሞ ተነግሯልና፡፡

*ዲ/ን ፈጠነ አረጋ*
*አማሮ*

## በርቱ በሉልኝ

የወንድሞቼ አገልግሎት ቢማርከኝ ተግባራቸውም ቢያስደንቀኝ በርቱ ተበራቱ ትሉልኝ ዘንድ፤ ሞራላቸውም ተገንብቶ የቤተ ክርስቲያን አለኝታ እንዲሆኑና በአገልግሎታቸው እንዲጸኑ መንፈሳዊ ምክር እንድትለግሡልኝ ወደ እናንተ ጻፍኩኝ፡፡ አካሄዳቸው በሕንድ ሀገር በሃይደርባድ ከተማ የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል ቢሆንም የተዋሕዶ ልጅነታቸው ከሄዱበት ዓላማ ጐን ለጐን መንፈሳዊ አገልግሎት መፈጸም እንዳለባቸው ሁሌም ያሳውቃቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት እምነታችንን፣ ባሕላችንን እንዲሁም ሥርዓታችንን በማስተዋወቅ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ይህንን ደብዳቤ እንድጽፍ ያነሣሣኝ ግን ባለፈው የትንሣኤ በዓል ያደረጉት አርአያነት ያለው ሥራ ነው፡፡ ይኸውም እነዚህ ዘጠኝ የተዋሕዶ ልጆች ወንድሞቼ በበዓሉ ላይ ለ50 ሰዎች የሚሆን ምግብ ያዘጋጃሉ፡፡ በአካባቢው የሚገኙ ነዳያንንም በዓሉን አስመልክተው ይመግባሉ፡፡ በመካከላቸው የሚገኘው ወንድሜ ከጻፈልኝ ኢ–ሜይል ጋር አያይዞ ከላከልኝ ፎቶግራፍ ለመረዳት እንደ ሚቻለው ወንድሞቼ ትርጉም ያለው የትንሣኤ በዓል አክብረዋል፡፡ ታድያ እነዚህ ወንድሞቻችን ይህንን ተግባር በአርአያነት አጠናክረው እንዲቀጥሉ በርቱ ትሉልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ፡፡

*አፈ ወርቅ አጥናፍ ሰገድ*
*አ/አ*

## በአጥፊዎች ሳንጠፋ

ባለፉት ሁለት ተከታታይ እትሞች ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ፤ አሁን በዩኒቨርሲቲው የቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያደረገውን የፊደላት ቅነሳ አስነብባችሁናል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መምህሬ «ፊደላቱን ለሌላ ቋንቋ ገብሮ ከሞቱ ቋንቋዎች አንዱ ግእዝ ነው» ሲሉ አንጀቴ ደብኖ ነበር፡፡ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ገደሉት፡፡ ይህን አሳብ የሚያራምዱ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ደግሞ ይኸውና ሊቀብሩት ነው፡፡ ግእዝ መቀነስ ቢያስፈልገው ኖሮ አባቶቻችን በቀነሱት ነበር፡፡ ያለ ሀብታቸው ሥጦታ አበርካች፣ በማይመለከታቸው ፈራጅ በቤተ ክርስቲያን ንብረት በሕዝብ ሀብት ላይ ለዚያውም ሊቃውንቱን ሳያማክሩ ወሳኝ መሆናቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ አባቶቻችን በብዙ ድካም ያቆዩልንን አንጡራ ሀብታችንን በግድ የለሽነት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ማጣት የለብንምና የቤተ ክርስቲያናችን የበላይ ኃላፊዎች /ቅዱስ ሲኖዶስ/ በአጥፊዎች ሳንጠፋ መፍትሔ ሊፈልግ ይገባል፡፡

ዲ/ን አሰፋ ጌትነት
ደ/ብርሃን
ሰሎሞን ጌታቸው
5ኛ ሜ/ክ/ጠ ሆስፒታል

## በመጽሐፍ

የመጽሔታችሁ አምዶች ይህኛው ከዚህኛው ይበልጣል /ያንሣል/ ባይባሉም የግእዝ ቋንቋ ዓምዳችሁ እጅግ መልካምና ወቅቱ የሚፈልገው ነው እላለሁ፡፡ ለእኛ ለወጣቶች ቋንቋች ንንና በእሱም በኩል ከብዙ ዕውቀቶች ጋር የሚያስተዋውቀን ነውና፡፡ ቋንቋ ውን በሰፊው እንድንማር በመጻሕፍት መልክ የተዘጋጁ ካሉ ብትጠቁሙን፤ ወይም እናንተ በመጽሐፍ መልክ በሰፊው ተዘጋጅቶ እንዲታተም ብታደ ርጉ መልካም ነው እላለሁ፡፡

ካሣ ይመር
አዊ ዞን

<u>ከአዘጋጁ</u>፡- እናመሰግናለን፡፡ ለግእዝ ማስተማሪያ ይሆኑ ዘንድ የተዘጋጁ ብዙ መጻሕፍት ቢኖሩም ለመነሻ ያህል ቋን ቋውን ለማወቅ በመምህር ዜና ማርቆስ እንዳለው የተዘጋጁትን «ጥንታዊ ግእዝ በዘመናዊ አቀራረብ» እና «ግእዝ ለአራ ተኛ ክፍል» የተሰኙትን መጻሕፍት ማንበቡ ይጠቅማል፡፡

## አኩሪ ተግባር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን የ31 ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮ ጵያ ቴሌቪዥን «ስኬት» በተሰኘው ፕሮግራም ላይ ሐምሌ 25፤ ነሐሴ 2 እና 9 ቀናት በተከታታይ ቀርቧል፡፡ ዝግጅቱ ቤተ ክርስቲያናችን ዘር፣ ሃይ ማኖት፣ ቀለም፣ ክልል ሳትለይ ሕዝበ አዳምን ለማገልገል የቆመች እንደ ሆነች ያስረዳ ነበር፡፡ በዚህም እኛ ል ጆቿ እንኮራለን፡፡ በመሆኑም ሁላች ንም በእንቅስቃሴዋ ሁሉ በሥራና በጸ ሎት ከጐንዋ ልንቆም ይገባል እላ ለ ሁ፡፡

ጳውሎስ ያዕቆብ
/ጃንሜዳ/

## አቡሻክር

ቤተ ክርስቲያናችን የምትገ ለገልበት ጥንታዊ የቀን አቆጣጠር ሥርዓት አላት፡፡ ይኸውም አቡሻ ኽር ነው፡፡ በዚሁ ሥነ ቀመር ዙሪያ ሊቃውንትን አነጋግራችሁ በአዲሱ ዓመት የዝግጅታችሁ መጀ መሪያ ብታደርጉት የብዙ ምእመ ናን ጥያቄ ምላሽ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡

ሽፈራው ማሞ
አሰሳ

<u>ከአዘጋጁ</u>፡- እናመሰግናለን፡፡ ስለ አቡሻኽር ለእርስዎና ለሌሎች አንባ ብያን ጥያቄ ምላሽ ይሆን ዘንድ የዚህን እትም የጥያቄ ዎቻችሁ ዓ ምድ እንዲመለከቱ እንጋብዛለን፡፡

## እንደገና ቢመረመሩ

እንደ እፉኝት ልጆች የኢ ትዮጵያ ልጆች ሆነው የራሳቸውን ፊደል ማንም ሳይቀንስባቸው ራሳ ቸው ለመቀነስ ጥረት እያደረጞ ያሉት «ምሁራን»፤ ኢትዮጵያውያን መሆናቸው አጠራጥሮኛል፡፡ አሁ ንም ቢሆን በራሳቸው አሳብና ፍላ ጎት ከደረሱበት ደረጃ ላይ ቢደር ሱም ባሉበት ቆመው የፊደል ምን ጭ /ባለቤት/ ከሆነችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር መወያየት ይኖርባቸዋል፤ የእርሷም ፈቃደ ኛነት መጨመር ያለበት ይመስ ለኛል፡፡

አበባው መሠረት፣ ስማቸው
እግዜሩ፣ ፍሬ ሕይወት
ባሕር ዳር
ዲ.ን ዳንኤል አሥራት
ሾኔ

## የንቃታችሁ አብነት

ሰዎች በማወቅም ይሁን ሳያውቁ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የጥፋት መረባቸውን ሲዘረጉ እና ንተ ተከታትላችሁ መልስ ስትሰጡ ሳይ በእጅጉ እደሰታለሁ፡፡ በሄዱበት ተከትላችሁ፣ ያጣመሙትን አቃ ንታችሁ፤ የጣሉትን አንሥታችሁ የምትሰጡት መልስ አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ምን ያህል በንቃት እየ ተከታተላችሁ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ለዚ ህም ባለፉት ሁለት ተከታታይ እት ሞች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ያደረገውን የፊደል ቅነሳ በሚመለከት የሰጣችሁት አጥጋቢ ምላሽ ለዚህ ዐቢይ አብነት ነው፡፡ ብርታቱን ይስጣችሁ፡፡

ም/ዐሥር አለቃ አራጋው ምላ
እንትጮ

## አመስግኑልን

እምነታችንንና ትውፊታ ችንን ጠልተን የሰው በምኝናፍቅበት፣ ስለ ገንዘብም የእኛ የኾነውን ሁሉ ራ ሳችንንም ጭምር ለባዕዳን በምናስ ገዛበት ጊዜ ገንዘባቸውንና ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው የከበረ ጽሌያ ችንን ወደ ሀገራችን ያመጡልንን ዶ/ር አያንን ሁሉን በጊዜው በሚሠራና በሚያሠራ በእግዚአብሔር ስም አመስ ግኑልን፡፡

ሲ/ር ሙሉ ብርሃን
ደሴ ሆስፒታል

## በቋንቋቸው እንመግባቸው

አዎ ÷ በብዙ ቋንቋዎች ማስተ ማር የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አንዱ መገለጫ ነው፡፡ በዚህ ርእስ ጉዳይ ባለፈው የተላለፈው የማኅበሩ መልእክት ያስተላለፋችሁት መልእክት በእጅጉ አስደስቶናል፡፡ እኔና መሰል ጓደኞቼ ዘወትር የምንነጋገርበት ጉዳይ ነበርና፡፡ በመልእክቱ በሚገባ እንደ ተገለጠው የሐዋርያዊት ቤተ ክር ስቲያን መገለጫዎች ከሆኑት ነጥቦች ውስጥ አንዱ ዘር ጎሳ ሳትለይ፣ የቦታ ርቀት ሳይበግራት በየትኛውም ቦታ ያሉ ሕዝቦችን አሉበት ድረስ ሄዳ ማስተማሯ ነው፡፡ የእነ አባ ዜና ማርቆስን፣ አባ ተክለ ሃይማኖትን፣ አባ አኖሬዎስንና ሌሎች ቅዱሳን አባቶቻ ችንን ዜና ሕይወት ስንሰማ ይህንኑ እንረዳለን፡፡ በዚህም እንኮራለን፡፡ ታድያ ዛሬም የእነዚህ አባቶቻችን ተጋድሎና አገልግሎት በእኛ ሊደገም ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ በማኅበረ ቅዱሳን መጀመሩ በእጅጉ የሚያስደስትና የአባቶቻችን ልጆች መሆናችንን እንድ ናውቅ ያደርገናልና በርቱ፡፡ የቤተ ክር ስቲያናቸውን ትምህርት በቋንቋቸው ሊመገቡ የሚጓጉ ብዙዎች ናቸውና፡፡

ተክለ መድኅን /መንዲ/




©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ዝክረ ቅዱሳን

## በአውራኅ መስከረም ወጥቅምት

1 ወርኀ መስከረም

መስከረም 2

- ምትረተ ርእሱ ለዮሐንስ

መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ በዘመኑ ንጉሥ ሄሮድስ የወንድሙ የፊልጶስ ሚስት የሆነችውን ሄሮድያዳን በማግባቱ ቢገሥጸው በግዞት ቤት አኖረው:: በልደት በዓሉ ቀን ንጉሡ ባዘጋጀው ግብዣ የሄሮድያዳ ልጅ በዘፈነች ጊዜ ንጉሥ ሄሮድስ ተደስቶ የፈለገችውን ሊያደርግላት ቃል ገባላት:: እሷም ከእናቷ ጋር ተመካክራ የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ ቆርጠህ ስጠኝ አለችው:: ንጉሡም በዚህ ቀን ያለችውን ፈጸመ::

መስከረም 3

- አባ ዜና ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ

መስከረም 4

- ልደተ ዮሐንስ ወንጌላዊ

በገሊላ አውራጃ ከአባቱ ከዘብዴዎስና ከእናቱ ከማርያም ተወለደ:: እንደ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት እናቱ ከ36 ቱ ቅዱሳት አንስት አንዷ ነበረች::

መስከረም 5

- ዕረፍቱ ለአቡነ አሮን ዘመቄት

መስከረም 6

- በዓለ ነቢዩ ኢሳይያስ

መስከረም 7

- ልደተ ሐና እመ እግዝእትነ ማርያም

መስከረም 8

- የካህኑ የአሮን በትር የለመለመችበት

መስረከም 9

- የቅዱስ ፋሲለደስ ልደት

መስከረም 10

- የንግሥት ሳባ ኢትዮጵያዊት ዕረፍት

መስከረም 11

- ቅዱስ ያሬድ ኢትዮጵያዊ

መስከረም 12

- በዓለ ቅዱስ ሚካኤል
- ጉባኤ ኤፌሶን

መስከረም 13

- ቅዱስ ሩፋኤል ሊቀ መላእክት

መስከረም 14

- በዓለ አጋቶን ወመቃርዮስ

መስከረም 15

- ፍልሰተ አጽሙ ለእስጢፋኖስ

መስከረም 16

- የመስቀል ደመራ
- ዕረፍተ ጦቢት

መስከረም 17

- በዓለ መስቀል

መስከረም 18

- ዕረፍቱ ለአቡነ አኖሬዎስ ኢትዮጵያዊ

መስከረም 19

- አባ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም

መስከረም 20

- ኤልሳዕ ነቢይ

መስከረም 21

- ብዙኃን ማርያም
- ሊቃውንት በ324 ዓ.ም በጉባኤ ኒቂያ ተሰባሰቡ

መስከረም 22

- ዕረፍቱ ለቅዱስ ዮልዮስ ሰማዕት

መስከረም 23

- ዕረፍቶሙ ለአውናብዮስ ወእንድርያስ

መስከረም 24

- ክርስቶስ ሠምራ ደብረ ሊባኖስ የገባችበት

መስከረም 25

- ዕረፍቱ ለዮናስ

መስከረም 26

- ብሥራተ ዘካርያስ
- ካህኑ ዘካርያስ ከሚስቱ ከኤልሳቤጥ ልጅ እንደሚወልድ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አበሠረው::
- እመቤታችን በዮሴፍ ቤት የወደቀ ዕንጨት ያለመለመችበት

መስከረም 27

- ሰማዕቱ ኤዎስጣቴዎስ

መስከረም 28

- አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ

መስከረም 29

- ዕረፍተ ቅድስት አርሴማ

መስከረም 30

- ማርቆስ ወንጌላዊ ወአትናቴዎስ ሐዋርያ

2. ወርኀ ጥቅምት

ጥቅምት 1

- ዕረፍተ ቅድስት አንስጣስያ

ጥቅምት 2

- ልደተ አባ ሕርያቆስ

ጥቅምት 3

- ቅድስት ታኦድራ

ጥቅምት 4

- በዓለ አብርሃ ወአጽብሃ

ጥቅምት 5

- ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ወቅዱስ ኪራኮስ

ጥቅምት 6

- ሄኖክ ወልደ ሴት የተሰወረበት

ጥቅምት 7

- አባ ባውላ ዘጠመው

ጥቅምት 8

- ቅድስት ሶስና ዳግማዊት

ጥቅምት 9

- አቡነ መዝገበ ሥላሴ

ጥቅምት 10

- አውማንዮስ ሊቀ ጳጳሳት

ጥቅምት 11

- ቅዱስ ፋሲለደስ

ጥቅምት 12

- ሳሙኤል ዳዊትን ያነገሠበት ዕለት

ጥቅምት 13

- ዕረፍቱ ለሰማዕቱ ያዕቆብ

ጥቅምት 14

- ዕረፍቱ ለቅዱስ ገብረ ብክርስቶስ

ጥቅምት 15

- የጳውሎስ ረዳት የሴላስ ዕረፍት

ጥቅምት 16

- አባ ጳውሊ ዐቢይ መነኮስ

ጥቅምት 17

- 2116 የደብረ ዳሞ መነኮሳት በካቶሊካውያን የታረዱበት

ጥቅምት 18

- የሠለስቱ ደቂቅ ዕረፍት

ጥቅምት 19

- በርተሎሜዎስ ወብእሲቱ

ጥቅምት 20

- ዕረፍቱ ለዮሐንስ ሐጺር

ጥቅምት 21

- በዓለ ድንግል ማርያም ወፍልሰተ ሥጋሁ ለአልዓዛር

ጥቅምት 22

- ሉቃስ ወንጌላዊ

ጥቅምት 23

- ቅዱስ ጊዮርጊስ

ጥቅምት 24

- የቆስጠንጢኖስ ልደትና 24ቱ ካህናተ ሰማይ

ጥቅምት 25

- ቅዱስ መርቆሬዎስ ሰማዕት

ጥቅምት 26

- ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ቶማስና ፊልጶስ ሐዋርያ

ጥቅምት 27

- አባ መብዓ ጽዮን ወአባ ጽጌ ድንግል

ጥቅምት 28

- ልደተ ኖኅ ወአባ መቃርስ

ጥቅምት 29

- ሳሙኤል ዘወገግ

ጥቅምት 30

- አስተርእዮተ ርእሱ ለዮሐንስ

ማስገንዘቢያ:- ይህንን ጥቆማ ለማቅረብ ምንጭ የሆነን ስንክሳር ነው:: የቅዱሳኑ ቃል ኪዳናቸው ከሁላችን ጋር ይሁን::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የእንቁጣጣሽ ሥነ ቃላዊ ዳራ

*ሐጎሳ ዘማርያም*

በማንኛውም የሰው ልጆች ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሥነ ቃል ዓይነቶች ይከሰታሉ:: እኒህም የሥነ ቃል ዓይነቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ ኖረዋል፤ አሁንም አሉ፤ ወደ ፊትም ይኖራሉ:: «አፍዓዊ ኪነተ ቃል በዘመናቸው ክዋኔያቸው በቃል የነበረና ዛሬም የኾነ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍበት አንድ መንገዳቸው በቃለ የነበረና ዛሬም የኾነ፤... ቢዜሙም ቢደረደሩም የቀረርቶ፣ የልመና፣ የልቅሶ፣ የቡሔ፣ የእንቁጣጣሽ ወዘተ ግጥሞችን የሚያካትት ቅርጽ ነው::» /ፈቃደ አዘዘ፣ስለ <u>ሥነ ጽሑፍ 13 መጣጥፎች መድብል</u> «አፍዓዊ ኪነተ ቃል ምንድን ነው?» ፣ገጽ 88/:: እንደ መስኩ ምሁራን አገላለጽ ሥነ ቃል ስለ አንድ ባሕላዊ ክንዋኔ፣ ስያሜና ታሪክ የሚነገርበት የ«Folklore» አንዱ መስክ ነው:: /Richard M.Dorson, <u>Folktale and Folk life: An Introduction</u>, P.21/ ::

ስለሆነም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ስለ እንቁጣጣሽ በዓል ስያሜና ስለ ታሪካዊ የትመጣው /ዳራው/ ስናነሣ ስለ በዓሉ ሥነ ቃል መናገራችን ነው:: ይህም «እንቁጣጣሽ» የሚለው የዘመን መለወጫችን ከስያሜው ጀምሮ ሥነ ቃል ነክ ነው፤ ቃላዊ ታሪኩና በቃል ሲተላለፍ የመጣው የስያሜው ትንተናም የሥነ ቃል አካል ነው ማለታችን ነው:: ዕለቱ «እንቁጣጣሽ» ብቻ ሳይሆን «ቅዱስ ዮሐንስ» እየተባለም ይጠራል::

ከዚህ በመቀጠል «እንቁጣጣሽ በአዲስ አበባ የልጃገረዶች ዘፈን ይዘት፣ ቅርጽና ሥነ ቃላዊ ባሕርያት ትንተና» በሚል ርእስ በለምለም በቀለ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ከቀረበው ጥናት ያገኘነውንና ከሌሎች ጥቂት ምንጮችም ያሰባሰብነውን የዘመን መለወጫ በዓላት ስያሜዎች ሐተታ እንደ ሚከተለው አቅርበናል::

◈ ◈ ◈

## ቅዱስ ዮሐንስ

መጥምቁ ዮሐንስ÷ሄሮድስ ንጉሠ አይሁድ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮድያዳን አግብቶ ነበርና «የወንድምህ ሚስት ለአንተ ልትሆን አልተፈቀደም» ብሎ በማስተማሩ ጳጉሜን አንድ ቀን ታሰረና መስከረም ሁለት ቀን አንገቱ በሰይፍ ተቀልቶ ዐረፈ:: ስለዚህ ይህ ቅዱስ አባት የሐዲስ አዲስ ካህን፣ነቢይና ሐዋርያ እንደ መሆኑ መጠን መታሰቢያው የአዲስ ዘመን መባቻ ተደርጐ፣ በእስክንድርያና በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በዓላት የሚከበሩበት፣ አጽዋማት የሚገቡበት፣ ዕለታት የሚገኙት ከዚህ ዕለት ተነሥቶ ስለሆነ «ርእሰ ዐውደ ዓመት ዮሐንስ ወላዲ መጥቅዕ ወአበቅቴ» እየተባለ ይዘመርለታል፤ ቀኑም በስሙ ይጠራል፤ ዘመኑም በዚህ ዕለት ይለወጣል÷ ይታደሳል::

*<u>የቃል አስረጅ፦</u> መምህር ሀብተ ማርያም ተድላ፣ የሊቃውንት ጉባኤ ምክትል ሰብሳቢ፣ ሐምሌ 29 ቀን 1985 ዓ.ም*

◈ ◈ ◈

ዘመነ ዮሐንስ ስንል ሁለት ዮሐንሶች /መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ፤ ሐዋርያውና ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ / አሉና ዘመኑ በማንኛው ዮሐንስ እንደ ተሰየመ ማወቅ ያስፈልጋል:: ዘመኑ የተሰየመው አራተኛውን ወንጌል በጻፈው በዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ነው::

*አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ÷ መስከረም አንድ ቀን 1979 ዓ.ም. ÷ በኢትዮጵያ ሬድዮ ዓለም ዓቀፍ አገልግሎት ከሰጡት ቃለ ምልልስ*

◈ ◈ ◈

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የመሸጋገሪያው ዕለት በየዓመቱ ቅዱስ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል:: ይህም የነቢዩ የዘካርያስ ልጅ መጥምቁ ዮሐንስ ነው÷ በዘመነ ብሉይ መጨረሻና በዘመነ ሐዲስ መጀመሪያ ላይ ተነሥቶ «መንግሥተ ሰማያት ልትሰጥ ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» እያለ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ስለ አስተማረ በየዓመቱ የዘመኑ መጀመሪያ በእርሱ ስም እንዲጠራ ተደርጓል::

*ቀ-ሲ-ን ልሣኑ በዛብን ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ ÷ ቁጥር 7÷1987 ዓ.ም*

◈ ◈ ◈

## እንቁጣጣሽ

ሌላው የዘመን መለወጫ መጠሪያ «እንቁጣጣሽ» የሚለው ስያሜ ነው:: እንቁጣጣሽ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የደስታ፣የብሩህ ተስፋና የአዲስነት ስሜት የሚያሳድር ነው::

ስለ እንቁጣጣሽ በቃል የተነገረ እንጂ በጽሑፍ የሠፈረ አልተገኘም:: ሆኖም በቃል ሲወርድ ሲዋረድ እንደ መጣ...ዕንቁ ብሎ አዕናቁ ከግእዝ የተወረሰ ቃል ነው:: ዕንቁ ለአንድ÷ አዕናቁ ለብዙ ይነገራል:: ጣጣሽ፡- «ፃዕ ፃዕ» ከሚለው የግእዙ ቃል የተወረሰ ነው፤ በአማርኛ ጣጣ፣መባዕ፣ ግብር፣ መፍቀድ፣ገጸ በረከት /በረከተ ገጽ/ ማለት ይሆናል:: መጻሕፍተ ብሉያት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበውን መባዕ፣ የሚገባውን ግብር «ፃዕፃዕ» ይሉታል:: በየዓመቱ እንቁጣጣሽ ማለታችን «የእንቁጣጣሽ ግብር÷የእንቁጣጣሽ ገጸ በረከት ነው» ብለን የምሥራች ማሰማታችን ነው::

በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ እንቁጣጣሽ የተበረከተው ለቀዳማዊ ምኒልክ እናት ለንግሥት ማክዳ ነው:: ንግሥት ማክዳ ቀዳማዊ ምኒልክን በወለደች ጊዜ ሕዝቡ ንጉሥ ተወለደ ብሎ እልል እያለ «የአበባ እንቁጣጣሽ» ለንግሥት ማክዳ አበረከተ:: እንቁጣጣሽ መባሉም መጀመሪያ ለንግሥቲቱ ስለ ተገበረ ነው:: ለንጉሥ ቢሆን ኖሮ «ዕንቁ ፃዕፃሁ» ይባል ነበር እንጂ «እንቁጣጣሽ» አይባልም ነበር:: በሸዋም ሕዝቡ ግብር አለብኝ ሲል «ጣጣ አለብኝ» ይላል:: ከዚህም በቀር ንጉሥ ሰሎሞን ከደስታው ብዛት የተነሣ ለንግሥቲቱ አስቀድሞ ለጣትሽ መታሰቢያ ይሁንሽ ብሎ የዕንቁ ቀለበት ሰጥቷት ነበር እያሉ ሊቃውንት ነግረውናል::

- *የቃል አስረጅ÷ ሊቅ ሣህሌ ወልደ ተክሌ*
- *ሊቀ ሥዩማን አክሊሉ ገብረ ኪሮስ÷ <u>አዲስ ዘመን ጋዜጣ</u>÷ መስከረም 5 ቀን 1955 ዓ.ም*
- *«እንቁጣጣሽ ምንድን ነው?»፣<u>መነን መጽሔት</u>፣ /አ.አ፣ መስከረም/1965 ዓ.ም. ቁጥር 1፣ገጽ 8*

◈ ◈ ◈

የእንቁጣጣሽም ታሪክ ንግሥተ አዜብ ለንጉሥ ሰሎሞን ተንካራ የሚባል እንቁ ወስዳ ገጸ በረከት ብትሰጠው «እንቁጣጣሽ ይሁን» ብሏታል ይባላል:: በኢትዮጵያ ሕግ የተሰበከው ስንግሥት አዜብ በምኒልክ እናት ነውና በዚህ ምክንያት ይህ ሲታሰብ ይኖራል:: በዚህም ቀን የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ በዓል ይከበራል:: ...የኢትዮጵያ ሴቶች ለምለም ሣር ከራሳቸው ላይ እያሰሩ አበባ በእጃቸው እየጨበጡ በዓሉን ያከብራሉ:: ለምለም ሣርና አበባ መያዛቸው በኖኅ ጊዜ ማየ አይኅ /የጥፋት ውኃ/ ጉደለ ስትል ርግብ ለምለም ቅጠል በአፏ ይዛ ታይታ ነበርና ምንም ማየ አይኅ የጥፋት ቢሆን ክረምት አለፈ በማለት ይመስላል::

*«ስለ ርእሰ ዐውደ ዓመት፣» <u>ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ</u>፣ /አ.አ፣1951 ዓ.ም. 2ኛ ዓመት ቁጥር 36/ ገጽ 281::*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

◈ ◈ ◈

እንቁጣጣሽ ከዘመን መለወጫ በዓል አንደኛው ዘርፍ ነው:: ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ዜና ጥበብ እየሰማች ስትደነቅ ትኖር ነበር:: በጆሮዋ የሰማችውን በዓይኗ ዓይታ ለመረዳት ስለፈለገች በግመሎች ላይ ሽቱና እጅግ ብዙ ወርቅ እንዲሁም በኢትዮጵያ የሚገኝ በኢየሩሳሌም የማይገኝ ልዩ ልዩ ገጸ በረከት አስጭና ከብዙ ሠራዊት ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ገባች:: ከንጉሡ ሰሎሞንም ጋር ተገናኝታ የያዘችውን ገጸ በረከት ከሰጠችው በኋላ ብዙ ነገሮችን ጠየቀችው:: እርሱም አንድ ነገር ሳይሰውር ገለጸላት:: ቤተ መንግሥቱንና በቤተ መንግሥቱ የሚገኙትን እጅግ በጣም የከበዱ ዕቃቆችን ሁሉ አስጎብኝቷት ሲያበቃ «ዕንቁ ለጣትሽ ጌጥ ይሁንሽ» ሲል እጅግ በጣም የከበረ ዕንቁ አበረከተላት /ሰጣት/:: ይህም ዕንቁ ከሌሎች ንዋያት ሁሉ የሚበልጥ ተመሳሳይ የማይገኝለት በጨለማ የሚያበራ ከመሆኑም ሌላ ብርሃኑንም እስከ አራት ዓይነት እየለዋወጠ የሚያሳይ መሆኑ ይነገራል:: ዕንቁጣጣሽ በዚህ ምክንያት ተጀምሮ አሁን ከሚፈጸመው ሥነ ሥርዓት ደርሶ በመፈጸም ላይ ይገኛል:: የሚከበረውም ከላይ እንደ ተገለጸው መስከረም አንድ ቀን ሲሆን ንግሥተ ሳባና ሰሎሞንም የተገናኙት በዚህ ወር መሆኑ ታውቋል::

በመስከረም ወር ምድር በአዝርዕትና በአትክልት በአበባና በፍሬ የምትሸፈንበት በተለያዩ አበቦችም የምታሸበርቅበት በመሆኑ በዚህ ወር የዕንቁጣጣሽ በዓል እንዲከበርበት የተመረጠበት ጊዜ ነው ለማለት ያስደፍራል::

በዕንቁጣጣሽ ዕለት በየሀገሩ የሚፈጸሙት ባሕሎች የተለያዩና ብዙ በመሆናቸው ሁሉንም ለማቅረብ አይቻልም:: ይሁንና በዚህ ዕለት ልጃገረዶች የአበባ ዓይነቶችን በማዛመድና ልዩ ልዩ ኅብረ መልክእን በመፍጠር፤ ለቤተ ሰቦቻቸውና ለወገኖቻቸው ዕንቁ ጣጣሽ በማለት የአበባ ጉንጉን ያበረ ክታሉ:: ተቀባዮችም «በየዓመቱ ያምጣሽ» እያሉ አበባውን ይቀበላሉ÷ ከተቀበሉም በኋላ ገንዘብ ይሰጣቸዋል÷ እነርሱም ባገኙት ስጦታ የፈለጉትን ዕቃ ገዝተው የዕንቀጣጣሽ በረከት እያሉ እንደ ማስታወሻ አድርገው ይጠቀሙ በታል::

በሀገራችን ንግሥትና በጠቢቡ ሰሎሞን ጊዜ በበረከት ልውውጥ የተጀመረው የዕንቁጣጣሽ ታሪካዊ ባሕል ሲወርድ ሲዋረድ ከአለንበት ዘመን ስለደረሰ በዓሉ በየዓመቱ ከዘመን መለወጫ ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር የሚከበር መሆኑ ታውቋል::

*ቀ–ሊ–ኅ ልሣኑ በዛብኅ፣*
*ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ፣*
*ቁጥር 7፣1987 ዓ.ም*

◈ ◈ ◈

«እንቁጣጣሽ ግጫ ማለት ነው፤ ግጫ ደግሞ የሣር ዓይነት ነው:: የአበባ÷ የእርጥብ ስጦታ መስጠት የተጀመረው በኖኅ ዘመን ነው:: ኖኅ የጥፋት ውኃ በጐደለ ጊዜ መጉደሉን ለማረጋገጥ ርግብን ልኳት የወይራ ቅጠል አምጥታለች:: እርሱም የመርከቡን ጣራ አንሥቶ ከወጣ በኋላ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በማቅረብ ልዩ ልዩ ፀዓዳ ሽታ ያላቸውንም አበቦች አቅርቧል:: ...ንግሥተ ሳባ ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ዘንድ ስትሄድ 500 ደናግልት ተከትለዋት ነበር:: የእልፍኝ አሽከሮቿም እነሱ ሲኾኑ የአበባውም የዕንቁ ጣጣሹ አሰጣጥ በእነሱ ተፈጽሟል:: ስለዚህ ዛሬ ልጃገረዶች አበባ ቀጥፈው እንግጫ ነቅለው ሽልመው የሚያቀርቡበት ነው:: ይህም በአበው ዘንድ ሲያስመርቃቸው በጐረምሳው ዘንድ ደግሞ የማታጨት ዕድል ያስገኝላቸዋል::

*«እንቁጣጣሽ ምንድን ነው?፣»*
*<u>መነን መጽሔት</u>፣ /አ.አ፣ መስከረም*
*1965 ዓ.ም ቁ.1፣ ገጽ 8::*
*አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ*

◈ ◈ ◈

«ዕንቁ» እና ጣጣሽ» የሚባሉትን ሁለት ቃላት ለይቶ መመልከት ይቻላል:: ዕንቁ የሚባለው የከበረና ከማዕድናት በላይ የኾነ የጌጥ ዕቃ መሆኑ ይታወቃል:: ጣጣሽ:– ሲባል ደግሞ «ያንቺ ግዳጅ ዕንቁ ነው» ማለት በዕንቁ ታጌጫለሽ፣ ታሸበሮቂያለሽ፣ የተለየሽ ነሽ በማለት ዕለተ ዮሐንስ /ወርኃ መስከረም/ ይከበራል:: እንቁጣጣሽ የሚባለው ቃል ለአንዲት ኢትዮጵያዊት ንግሥት እንደ ተነገረ ይተረካል፤ በዚሁ ዕለተ ዮሐንስ ወጣት ልጃገረዶች ይህን የምሥራች ለማድረስ ወደ ንግሥት ይሄዳሉ፤ ንግሥቲቱ በሌላ ስጦታ ልታስተናግዳቸው ስትሞክር ልጃገረዶቹ በስጦታዋ ስላልተስማሙ «ንግሥት ሆይ÷ አንቺ ጣጣሽ፣ ግዳጅሽ፣ ነው፤ ታድያ እንዴት እንቁ አጣሽ?» ስላሏት በዚሁ ተለመደ ይባላል::

...ልጃገረዶቹ የርግብ አምሳል ናቸው፤ ኖኅ ርግቢቱን ልኮ ውኃው ደርቆ እንደኾነ እንድታይ ሲልካት ውኃው ደርቆ መሬቱ ሁሉ ለምልሞ አብቦ ስላገኘችው የወይራ ቅጠል ይዛ የምሥራቹን ነገረችው:: ...ወጣት ልጃገረዶቹ የኖኅ ርግብ ምሳሌ ሆነው በክረምቱ የነበረው ችግር ተወግዶ መሬት መለምለሟን፣ ማበብዋንና ለፍሬ መድረሷን ለኖኅ ልጆች ለእኛ ለሁላችን ያበሥሩናል:: ...

በወርኃ ክረምት የነበረው የመብረቅ የነጎድጓድ ድምፅ፣ የጐርፉ፣ የዶፉ፣የማጡ፣ የድጡ መከራ አግዶት የነበረው ሕይወት ሁሉ በሰላም የሚንቀሳቀስበት፤ መሬት የምት ለመልምበት፣ የምታብብበትና ፍሬዋን የምትሰጥበት በወርኋ መስከረም ብቅ ስትል በመባቻዋ ዕለተ ዮሐንስ ወጣቶች በአበባ አጊጠውና ንጹሕ የኾነ ለብሰው ጣጣሽ ግዳጅሽ እንቁ በመሰለ አበባ ማጌጥ የኾነ ወርኃ መስከረም እንኳን ደኅና መጣሽ በማለት ሲቀበሏት ይታያሉ:: በዚህ ዕለት የሚበራው ችቦ ከሌሎች ቀኖች ችቦዎች የሚለይበት የራሱ ምክንያት አለው፤ ይኸውም የጨለማው፣ የመብረቁ፣ የውሽንፍሩ፣የበረዶው ወቅት አልፎ የብርሃን መምጣት፣ የፀሐይ መውጣት ተምሳኤት መሆኑ ነው፤ እሰየው ብሎ የደስታ መግለጫ ነው::

*<u>የቃል አስረጅ</u>:– መምህር*
*ሀብተ ማርያም ተድላ የሊቃውንት*
*ጉባኤ ምክትል ሰብሳቢ ፣ሐምሌ 29*
*ቀን 1985 ዓ.ም*

◈ ◈ ◈

ይህን የዘመን መለወጫ ስጦታ ጉዳይ ስናየው በብዙ አገሮች ተመሳሳይነት ያለው ነው:: ዛሬ በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ የኖኅ ትውልዶች /የሴም፣ የካምና የያፌት ዘሮች/ ለመሆናቸው ምንም ጥያቄ የለውም:: እናም ይህ ቅርስ ከኖኅ ዘመን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ልምድ ሳይሆን አይቀርም:: ኖኅ ከዚያ ከጥፋት ውኃ ሲወጣ ምድር አረንጓዴ ለብሳ ተክሎች ለምልመው አገኛቸው:: እርሱ ከመርከቡ ከመውጣቱ በፊትም ርግብ የውኃን መጉደል የምድርን አረንጓዴ መልበስ የወይራ ቅጠል የምሥራች በማምጣት አበሠረችው:: ... ለማንኛውም ዛሬ በምድር ላይ ያሉ ሰዎች በአብዛኛው የዘመን መለወጫቸውን የሚያከብሩት የክረምት ወቅት ተገባዶ ፀሐይ ስትወጣ ምድር አረንጓዴ ስትለብስና አበቦች ሲያብቡ ነው:: እንግዲህ ጻድቁ ኖኅ ከአስጨናቂው የጥፋት ውኃ በኋላ ያለውን ጊዜ እንደ አዲስ ዘመን እንደ ኖረው ሁሉ ከአስፈሪው፣ ከጨለማው፣ ከቀዝቃዛውና መውጫ መግቢያ ከሚያሳጣው የክረምት ወቅት ስናልፍ መጪውን ጊዜ እንደ አዲስ ዘመን እንቀበለዋለን:: ክረምቱ አረንጓዴ አልብሷት በአበቦች አሣምሯት ከሄደው ምድር ርጥቦች የኾኑትን በስጦታ መልክ እንለዋወጣለን፤ መልካም ምኞታችንንም እንገላለጻለን፣ ይህም ከጻድቁ አባታችን ከኖኅ የወረስነው በጐ ትውፊት ነው::

*<u>ምንጭ</u>:– ለምለም በቀለ÷*
*«እንቁጣጣሽ በአዲስ አበባ የልጃገረዶች ዘፈን ይዘት፣ቅርጽና ሥነ ቃላዊ ባሕርያት ትንተና፣»*
*ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ መስከረም 1986 ዓ.ም::*



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ሥርዓተ ጸሎት ወስግደት

ዲ. ያረጋል አበጋዝ

*ባለፈው እትም ዲ/ን ያረጋል ጸሎት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ ከገለጠ በኋላ ክርስቲያኖች በሚጸልዩበት ጊዜ ሊከተሏቸው ስለ ሚገቡ ሥርዓቶች ፍትሐ ነገሥትን መሠረት በማድረግ አቅርቦልናል:: ቀጥሎም በቀን ውስጥ ክርስቲያኖች ለምን ያህል ጊዜና በምን በምን ሰዓት መጸለይ እንደ ሚገባቸው እና ጸሎት የትና በምን ሁኔታ እንደሚደረስ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን አቅርቦልናል:: በዚህኛው እትም ደግሞ ስለ ስግደትና ሥርዓቱ ጠቅለል ባለ መልኩ ያቀርብልናል:: በዚህ አጋጣሚ ባለፈውም ሆነ አሁን የቀረቡት ትምህርቶች ያተኮሩት ምእመናን በየግላቸው ስለሚያደርጓቸው ጸሎታትና ስግደቶች ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን ትምህርት እንደሆነ ልናስገነዝብ እንወዳለን:: የማኅበር ጸሎትንና ስግደት በሚመለከት ግን ወደፊት የምናወጣ መሆናችንን እንገልጻለን::*

ስግደት ሰው ተገዥነቱንና አምልኮቱን ለእግዚአብሔር ከሚገጽባቸው መንገዶች አንዱ ነው:: የእግዚአብሔርን ገዥነትና ፈጣሪነት እያሰቡ ግንባርና ጉልበትን መሬት በማስነካት የእኛን ፍጡርነትና ተገዥነት የምንመሰክርበት ነው:: ይህ ዓይነቱ ስግደት የአምልኮ ስግደት ይባላል:: ለእግዚአብሔር ወደ መሬት ወድቀን ስንሰግድ ከመሬት አፈረ የሠራንና ያስገኘን እርሱ መሆኑን ማመንና መመስከር እንዲሁም ማስታወስና እና በዚሁም ሥጋዊነታችን «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» የተባለው ቃል እንደማይቀር በማሰብ መዋቲነታችንን ወደ አፈር መመለሳችንን ሁሉ መግለጽ ነው:: መሬት ከወደቀ /ከሰገደ/ በኋላ መነሣት ደግሞ ምንም ወደ አፈር ብንመለስ መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበደላችን ምክንያት የተፈረደብንን የሞት ፍርድ አስወግዶ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ነው፤ ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም» ብሎ በቃሉ ተስፋ የተሰጠ በተግባር ደግሞ ሞትንና መቃብርን /በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረትን/ ድል አድርጎ ተነሥቶ ተስፋ ትንሣኤን ያስጨበጠን ስለሆነ ብንሞትም በክርስቶስ የምንነሣ መሆናችንን ማዘከርና መመስከር ነው:: ዮሐ 11÷25 ፣ 1ኛ ተሰ 4÷13-14፣ ሮሜ.6÷5::

መገኛችንንና ፍጻሜያችንን ለማዘከርና ለማስተዋል÷ በተግባርም ለመመስከር እንዲህ ለእግዚአብሔር መስገድ ግዴታ ነው:: ለእግዚአብሔር አለመስገድ ÷ አመስግን ሲሉት «አነ ውጹእ እምዝንቱ ግብር፤ እኔ ከዚህ ነገር ውጭ ነኝ፤ ይልቁንም ከሥላሴ ጨምራችሁ አመስግኑኝ» እንዳለ ዲያብሎስ መሆን ነው:: በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ አንዴ ከፍሬ ቅዳሴ በፊት ሁለተኛው ፍሬ ቅዳሴ ላይ ሁለት ጊዜ ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ይላል:: በዚህ ጊዜ መስገድ ግዴታ ነው:: አንዳንዶች ግን ከመስገድ ይልቅ መቀመጫ ፈልገው ይቀመጣሉ:: ይህ ግን ተገቢ አይደለም:: ስግዱ ተባለ እንጂ ንበሩ /ተቀመጡ/ አልተባለምና::

ይህ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ የአምልኮ ስግደት ከእግዚአብሔር ውጭ ለማንም አይደረግም፤ ሊደረግም አይገባም:: ከተደረገም አምልኮ ጣዖት ይሆናል:: «ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ እንደተባለ::» ሉቃ.4÷8:: ከዐሥሩ ትእዛዛት አንዱ «በላይ ከሰማይ ካለው÷ በታችም በም ድር ካለው፤ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸው» የሚል ነው:: ዘጸ. 20÷4:: ምስል ወርድ ÷ ቁመትና ርዝመት ያለው ባለ ሦስት ንጻሬ /three dimensional/ በመሆኑ ለምስል መስገድ እግዚአብሔር የከለከለው ነው ÷ ፍጹም ጣዖታዊ ነው:: ስለዚህ በመላእክትም ቢሆን በቅዱሳንም ቢሆን በእመቤታችንም ቢሆን በምንም አንጻር ለተቀረጸ ምስል መስገድ ኃጢአት ነው:: ለሥዕል ግን ይሰገዳል÷ ሰሎሞን በቤተ መቅደሱ የኪሩቤልን ሥዕል እንደሣለ ይኸውም ወካይነት ያለው ስለሆነ ለባለ ሥዕሉ የሚደረገው የአክብሮት ስግደት ይደረጋል::

የአምልኮት ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ እንደሆነ ሁሉ ለእመቤታችንና ለቅዱሳን የአክብሮት ስግደት ይደረጋል:: ለእመቤታችን ነቢያት በትንቢት «ግንባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል» እያሉ ተናግረዋል:: ኢሳ.49÷23:: ይህ የተነገረው ለጽዮን ተራራ ነው የሚል ካለ ትንቢቱን የሐሰትና የኃጢአት ትንቢት ማድረጉ ነው:: ይኸ ግን የተነገረ ለእመቤታችን ተገቢ የጸጋ ስግደት ስለሚገባት ነው:: ለዚህ ነው መጥ ምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ የእመቤታችንን ድምፅ ሲሰማ በተአምራት የሰገደው:: ለቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃንና ሰማዕታትም የአክብሮት ስግደት መስገድ ተገቢና ቅዱስ መጽሐፍ የሚያስተምረን ነው:: ኢያሱ ለቅዱስ ሚካኤል /ኢያሱ 5÷14/ ዳንኤል ምሥጢርን ለሚነግረው መልአክ /ዳን.10/፤ ናቡከደነፆር ለዳንኤል /ዳን. 2÷46/፤ ቆርኔሌዎስ ለቅዱስ ጴጥሮስ /የሐዋ. 10÷ 25/፤ የወኅኒ ጠባቂው ለቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ /የሐዋ. 16÷30/ እንደ ሰገዱ::

በስግደት ጊዜ የስግደቱን ምንነት የሚለየው ስግደቱን የሚፈጽመው ሰው ኅሊና ነው:: ለእግዚአብሔር ሲሰግድ የእግዚአብሔርን ገናናነትና ኃይልነት እንዲሁም አባትነት እያሰበ በፍጹም መፍራትና በፍጹም ፍቅር ሆኖ ነው÷ ለእመቤታችን ለቅዱሳን ሲሰግድ ደግሞ እግዚአብሔር ያከበራቸው መሆኑን እያዘከረ በረከታቸውን እየተማፀነ ነው:: ለጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር መስቀልና ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስግደት ይገባል:: ክቡር ዳዊት «ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ፤ እግዚአብሔር እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን» እንዳለ መዝ.131÷7:: ጌታችን መስቀልን እንደ ዙፋን አድርጎ በዕለተ ዓርብ ከ6 ሰዓት እስከ 9 ሰዓት ድረስ አጋንንትን የተበቀለበት በፍርድ የነገሠበት ቅዱስ ሥጋው የተቆረሰበትና ክቡር ደሙ የፈሰሰበት ስለሆነ ስግደት ይገባዋል:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት በመሆኑ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ዕለት ዕለት የሚፈተትባት በሜሮን የከበረች የእግዚአብሔር ሕያው ስም የተቀረጸበት ጽላት ያለባት ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረቢያና የሥራ ሁሉ ማሳረጊያ ናት:: «በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ይሰግዱ ዘንድ» እንዳለ ለዚህ ስሙ ማደሪያ ለሆነች ለቤተ ክርስቲያንና ለታቦቱ /ጽላት/ ስግደት ይገባል:: ፊልጵ.2÷10:: ይህ የአክብሮት ስግደት ÷ እግዚአብሔር ያከበራቸውን ማክበር ÷ ከበረከታቸው ተሳታፊ ስለሚያደርግ እና



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያከበራቸውን» የእግዚአብሔርን ትእዛዝም መፈጸም ስለሆነ ነው:: ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ ተብሏልና:: ሮሜ.13÷7::

## ስግደት ሦስት ወገን ነው:–

1. ሰጊድ :–መላ አካልን ወደ ምድር በመጣል ራስን ምድር አስነክቶ መስገድ ነው::
2. አስተብርኮ:– ራስን ከጉልበት አድርሶ መመለስ ነው
3. አድንኖ:– ራስን ብቻ ዘንበል አድርጎ መመለስ ነው::

ስግደት ከጸሎት ጋር የተባበረ ነው:: ይኸውም ጸሎት በሚደረግበት ጊዜ ሲጀመር ለቅድስት ሥላሴ በመስገድ ጀምሮ በመስገድ መፈጸም ይገባል:: ታላቁ ነቢይ ኢያሱ እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ፊት ተሸንፈው ባፈሩ ጊዜ ቀኑን ሙሉ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በግንባሩ ተደፍቶ ሰግዶ ውሏል:: በዚህም እግዚአብሔር የደረሰባቸው ሽንፈት በምን ምክንያት እንደሆነና ያንን እንዲያስወግዱ ነግሯቸዋል:: ኢያሱ 7÷ 6–15:: ስለሆነም ጸሎት ከስግደት ጋር ሲዋሐድ ያማረና የተወደደ ነው::

በአጠቃላይ ስግደትን በሚከተሉት ዓይነቶች መክፈል ይቻላል::

1. ለእግዚአብሔር አምልኮትንና ለቅዱሳን ደግሞ አክብሮትን ለመግለጽ የሚደረግ ስግደት፤

2. ከጸሎት ጋር የሚደረግ ስግደት– ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት በእያንዳንዱ የጸሎት ጊዜ ከአንድ አቡነ ዘበሰማያት ሦስት ስግደት÷ በአጠቃላይ 12 አቡነ ዘበሰማያት 36 ስግደት ይሆናል:: በሰባቱ የጸሎት ጊዜያት አጠቃላይ 84 አቡነ ዘበሰማያት 252 ስግደት ይሆናል::

3. ለትሩፋትና ሥጋን ለማድከም የሚደረጉ ስግደቶች:– ስግደት የራስን ወዝና ጉልበት ለእግዚአብሔር መባዕ አድርጎ ማቅረብ ነው:: ከዚህ ጋር የሥጋን ኃይልና ተከታይ ጠባይዐት ለማድ ከም ÷ ፈተና ሲነሣ ለማስታገሥ ስግደት ታላቅ መሣሪያ ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጌቴ ሴማኒ ሲጸልይና ሲሰግድ ከቆየ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ ብሏቸዋል:: እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት ደግሞ ከስግደት ጋር የሚፈጸም መሆኑን በተግባር አስተምሯል:: ማቴ. 26÷41::

## ስግደት የማይደረግባቸው ዕለታትና ጊዜያት

1. በበዓለ ኀምሳ /ከትንሣኤ እስከ ጰራቅሊጦስ/ እና በሰንበተ ክርስቲያን መስገድም ይሁን ተንበርክኮ መጸለይ አይገባም:: ምክንያቱም በዓለ ኀምሳና ሰንበተ ክርስቲያን ከትንሣኤ በኋላ በመንግሥተ ሰማያት ለምንኖረው ሕይወትና ለምናርፈው ዕረፍት ምሳሌያት ስለሆኑ በእነዚህ ጊዜያት መስገድ መንግሥተ ሰማያትን የድካም ዓለምናት የሚል አንድምታ እንዳይኖረው ነው÷ እንዲሁም ከትንሣኤ በኋላ ያለውን ሕይወት እያዘከርን ለዚያው ብቁ እንድንሆን ራሳችንን ማዘጋጀት ስለሚገባን ነው::

2. በጌታችን ዐበይት በዓላት እና ወር በገባ በ12፣ በ21 እና በ29 ቀን አይሰገድም:: ይኸም በ12 የሊቀ መላእክት የቅዱስ ሚካኤል፣ በ21 የእመቤታችን በዓላት ሲሆኑ በ29 ደግሞ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በድንግል ማኅፀን በድንግልና የተፀነሰበትና የተወለደበት ዕለት ስለሆነ ነው:: በሌሎች ዕለታት በጻድቃን በሰማዕታት በመላእክት በዓላት ስግደት አይከለከልም::

3. ሥጋ ወደሙን ከተቀበሉ በኋላ ለአንድ ቀን አይሰገድም:: ይህም ከላይ በቁ.1 እንደተገለጸው ከቅዱስ ምሥጢር የተቀበለ የከበረ በመሆኑ የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ክቡርነት ለመግለጽ ነው:: እንዲሁም «ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ ከእኔ ጋር ይኖራል» ብሎ ጌታችን ተናግሮአልና ከክርስቶስ ጋር ስንኖር ጻዕርና ገዐር ድካምና ውጣ ውረድ የሌለው ዓለም መሆኑን ለመግለጽ እንዲሁም የምንድነው በእኛ ድካም ብቻ ሳይሆን በእርሱ ቸርነት መሆኑን ለመግለጽ ነው::

## ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ የስግደት ሥርዓት

1. በመጀመሪያ «እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐተ ስግደተ እንዘ አሐዱ ሠለስቱ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ/ ለአብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ አንዲት ስግደት እሰግዳለሁ፤ አንድ ሲሆኑ ሦስት÷ ሦስት ሲሆኑ አንድ ለሚሆኑ ብሎ ግንባርን መሬት በማስነካት በመላ ሰ ው ነ ት መሬት ላይ በመውደቅ ይሰገዳል::

2. «እሰግድ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ፤ አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እሰግዳለሁ» በማለት ለእመቤታችን መስገድ ይገባል::

3. «እሰግድ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተቀደሰ በደሙ ክቡር፤ /በክቡር ደሙ ለተቀደሰ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እሰግዳለሁ» ብሎ ለክቡር መስቀሉ መስገድ ይገባል::

4. ቤተ ክርስቲያኑ በስሙ ለተሰየመለት ጻድቅ ወይም መልአክ «እሰግድ ለታቦተ እገሌ» ብሎ መስገድ ይገባል::

5. እሰግድ ለስም ለዘሀሎ ውስተ ዝንቱ መንፈሳዊ ቤት

6. «እሰግድ ለአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኩሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት አምሳለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፤ ከሁሉ በላይ ለምትሆን ሐዋርያት ለሰበሰቡዋት ለኢየሩሳሌም ሰማያዊት አምሳል ለሆነች ለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እሰግዳለሁ» በማለት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስግደት ማቅረብ ይገባል:: ከዚህ በተረፈ ሊኖሩ የሚችሉ ነገሮች እያንዳንዱ ክርስቲያን እንደሚሠራው ትሩፋት ሁኔታ ሊፈጽማቸው የሚችሉ ናቸው:: ከዓመት ሁሉ በተለይ በዐቢይ ጾም ስግደት በዝቶ የሚፈጸም ሲሆን ይኸ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርሰው በዕለተ ስቅለት ነው:: በዚህች ዕለት ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ሲል የተቀበለውን መከራ በማሰብ ከቷና ወደ ቀያፋ ከዚያም ወደ ጲላጦስ ሲመላለስ አይሁድ እያዳፉና እየገፉ መሬት ላይ እየጣሉ ያንገላቱትን በማሰብ ቸርነቱን በማድነቅ በዚያው አንጻር እኛ ደግሞ ለዚህ ቸርነቱ ተገቢ ያልሆነ ሥራ እየሠራን እርሱን ማሳዘናችንን በፊታችን እያየን /ገላ. 3÷1/ ይቅር እንዲለንና እንዲምረን፤ እርሱ ድል አድርጎ እንደ ተነሣ እኛንም የክብር ትንሣኤ ለመነሣት እንዲያበቃን መለመን ብዙ ስግደት ይሰግዳል::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል፡፡» መዝ. 109÷2

ወልደ ሚካኤል

ልዑል እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በአርአያው ፈጥሮ በገነት አኑሮ ስሙን እንዲቀድስና ክብሩን እንዲወርስ ቢያዘጋጀውም በዲያብሎስ ተንኰልና በራሱም በሰው ተታላይነት ወድቆአል፡፡ ነገር ግን አባታችን አዳም እንደ ወደቀ ሳለመቅረት፣ ለመነሣትና ከፈጣሪው ጋር ቢጣላም ለመታረቅ እውነተኛ ንስሐ ገባ፡፡ በዚህም መሠረት ወደ እርሱ አንድነት እንደሚመልሰውና የቀደመ ክብሩን እንደሚሰጠው ቃል ገባለት፡፡

የሰው ልጅ ከወደቀበት የተነሣውና ከዲያብሎስ ተገዥነት ነጻ የወጣው መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ ተራራ በራሱ ፈቃድ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ ክቡር ደሙን አፍስሶ በፈጸመው የቤዛነት /የማዳን/ ሥራ ነው፡፡ በመስቀሉ የወደቀ አዳም ተነሣበት፣ የተመሳቀለው ሕይወቱ ተስተካከለ፣ ዲያብሎስ ድል ተነሣ፣ የሰው ልጅ በክርስቶስ ሥጋና ደም ተዋጅቶ ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ ወጣ፡፡ ክቡር መስቀል ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ሁሉ ሥራ የፈጸመበት ስለሆነ እናከብረዋለን እንመካበታለን፡፡

መስቀል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በላዩ ላይ ተሰቅሎ ከመቀደሱና ከመክበሩ በፊት የውርደትና የንቀት ምልክት ነበር፡፡ የመስቀል ሞት የሚፈረድባቸው በጣም ክፉዎችና ዓመፀኞች ነበሩ፡፡ ዘፍ.40÷18፡፡ የፋርስ ሀገር ሰዎች የመሬት አምላክ /አርሙዝድ/ የሚባል ጣዖት ያመልኩ ስለነበር ክፉ ሰው በመሬት ከተቀበረ አምላካችን ይረክሳል ሲሉ ከፍ አድርገው በመስቀል ላይ ይሰቅሉ ነበር፡፡ ሮማውያንም ስለ ዜግነት ክብር ሲሉ የሮማዊ ዜግነት ያሏቸውን በስቅላት አይገድሉም ነበር፡፡ በዘመነ ኦሪትም በእስራኤላውያን ዘንድ በእንጨት ላይ የተሰቀለ የተረገመ ነበር፡፡ ዘዳ. 21÷22፡፡ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰው የናቀውን ማክበርና የረከሰውን መቀደስ ፈቃዱ ስለሆነ ይህንን የንቀትና የውርደት ምልክት የነበረውን መስቀል ራሱ የሰውን ድኅነት ሊፈጽምበት ሥጋውን ሊቆርስበትና ደሙን ሊያፈስበት መረጠ፡፡ ስለዚህም ሐዋርያው እንዳለ «ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ፡፡» ፊልጵ. 2÷8፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ በመስቀል ላይ እንደሚሰቀል የመስቀልን ቅርጽና ሁናቴ በተለያየ ትንቢትና ተምሳሌት ከቀድሞ ጀምሮ ይገልጥ ነበር፡፡

ለምሳሌም፡-

1. በዓለመ መላእክት ቅዱሳን መላእክት ከዲያብሎስ ጋር በተዋጉ ጊዜ ድል ያደረጉት ለወደፊት ሰው ሆኖ ደሙን የሚያፈስበትን መስቀል ምልክት በብርሃን የመስቀል ትእምርት /ምልክት/ ሰጥቶአቸው ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ «በሰማይ ሰልፍ ሆነ፣ ሚካኤልና መላእክቱም ዘንዶውን ተዋጉ፡፡ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውምም» ያለው ይህንን ነው፡፡ ራእ.12÷7–10፡፡
2. እስራኤል የተባለ ያዕቆብ ሁለቱን የዮሴፍ ልጆች ኤፍሬምንና ምናሴን ሲባርክ እጆቹን አስተላልፎ በማመሳቀል ባረካቸው፡፡ ይህም ለወደፊት የዓለም ሁሉ ርግማን ስለሚወገድበትና የሰው ልጅ ሁሉ የሚባረክበትን መስቀልን በተምሳሌት የሚያሳይ ነው፡፡ ዘፍ. 48÷13–16፡፡
3. እስራኤላውያን በበረሃ ሳሉ የእግዚአብሔርን ከሃሊነት በመጠራጠራቸው መርዛማ እባብ ተነሥቶ እየነደፈ በጨረሳቸው ጊዜ ሙሴ ከነሐስ የተሠራ የእባብ ቅርጽ በዓላማ ላይ ሰቀለ፡፡ መርዛማው እባብ በመርዙ እየነከሰ ብዙዎችን እንደ ገደለ ዲያብሎስም በመርዙ ብዙዎችን ከእግዚአብሔር በመለየት ሞተ ነፍስ እንዲሞቱ አድርጎአል፡፡ በዓላማ ላይ የተሰቀለው ከነሐስ የተሠራው የእባብ ቅርጽ ያለው የክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ዓላማው ደግሞ የመስቀል ምሳሌ ነው፡፡ ይህ መርዝ ሳይኖረው መልኩን ሲያዩና ድምፁን ሲሰሙ እንደ ተፈወሱ ክርስቶስም ንጹሐ ባሕርይ ሆኖ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በኃጢአት ለደከሙና ለታመሙ ሁሉ መድኃኒት መሆኑን የሚገልጽ ነበር፡፡ ዘኁ. 21÷4–9፣ ዮሐ. 3÷14–15፡፡
4. አማሌቃውያን ከእስራኤላውያን ጋር ሲዋጉ ሙሴ እጆቹን ሲዘረጋ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር፣ እጁንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር፡፡ ሙሴ እጆቹን ዘርግቶ መዋል ስለ ከበደው አሮንና ሖር እጆቹን ደገፉ፡፡ ዘጸ.17÷8–13፡፡ በዚሁም እስራኤላውያን አማሌቃ ውያንን አሸነፉ፡፡ ይኸም አማሌቅ የአጋንንት ሙሴ የክርስቶስ የተዘረጉት እጆቹ ደግሞ የመስቀል ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በመስቀሉ አጋንንትን ድል ማድረጉን አመልካች ነበር፡፡

ለአብነት ያህል እነዚህ ተጠቀሱ እንጂ በቅዱስ መጽሐፍ መስቀልን በተመለከተ ብዙ ምሳሌ አለ፡፡ በትንቢትም እንዲሁ ተነግሮአል፡፡

ለምሳሌም፡-

1. ክቡር ዳዊት፡- «ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ፣ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው» ብሎአል፡፡ መዝ.59÷4፡፡ ይህም ለሚፈሩት ለምእመናን አጋንንትን የሚያባርሩበት ምልክት የተባለ መስቀልን ሰጣ ቸው ማለት ነው፡፡
2. «ቀነውኒ እደውየ ወእገርየ–እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ» ሲል ዳዊት የተናገረው ጌታችን በመስቀል ላይ በቀኖት ንጹሓት እጆቹና እግሮቹ ስለ እኛ ሲሉ እንደሚቸነከሩ በትንቢት ሲገልጽ ነው፡፡ ዳዊት ለራሱ አስመስሎ "ቸነከሩኝ" ማለቱ እርሱ ተቸንክሮ አይደለም፡፡ እርሱ የሞተው በሕመሙ ነው፣ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ ሚሆነውን በራሱ ይናገራል፡፡ ልበ አምላክ ያሰኘው አንዱ ይህ ነው፡፡ 1ነገ.2÷1–10፡፡
3. በቀራንዮ አደባባይ እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ በመስቀል ሕዝብንና አሕዛብን በእቅፉ ሊሰበስባቸው እንደሚጠራቸው ሲናገር ኢሳይያስ እንዲህ ይላል፡- «ለአሕዛብም በሩቅ ምልክትን ያቆማል÷ ከምድርም ዳርቻ በፉጨት ይጠራቸዋል እነሆም÷ እየተጣደፉ ፈጥነው ይመጣሉ፡፡» ጌታችን ለምድር ሁሉ ማዕከል በሆነች በቀራንዮ መስቀሉ ለሁሉም የዓለም ሕዝብ መሞቱን ሲገልጽ ነው፡፡ እንዲሁም «...ጌታ እንደገና እጁን ይገልጣል ለአሕዛብም ምልክትን ያቆማል ከእስራኤልም የተጣሉትን ይሰበስባል ከይሁዳም የተበተኑትን ከአራቱ የምድር ማዕዘኖች ያከማቻል» በማለት ጌታን ምልክት በተባለ መስቀል ላይ እጆቹን በቀኖት ተቸንክረው በመገለጥ እስራኤል ዘነፍስን ወደ አንድ መንጋነት እንደሚሰበስብ ኢሳይያስ በትንቢቱ አስረዳ፡፡ ኢሳ..11÷11–13፡፡
4. «በትረ ኃይል ይፌኑ ለከ እግዚአብሔር እምጽዮን፣ እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል፡፡» መዝ.109÷2፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስን ድል ያደረገው የኃይል በትር በተባለ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በዕፀ መስቀል ነው:: እግዚአብሔር በሰውና በእባብ ላይ በፈረደ ጊዜ ሰውን «እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ» ብሎ ነበር:: ይህ ለጊዜው ሰው እባብን ሲያይ በበትር ራሱን የሚቀጠቅጠው መሆኑን ሲሆን ፍጻሜው ግን ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስ ቶስ በትር በተባለ መስቀሉ በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ አዳምን ያሳተውን ዲያብሎስን እንደሚቀጠቅጠው የሚያ ስረዳ ነው:: ይህች ዲያብሎስን በበትሩ የቀጠቀጠው የኃይል መገኛ የሆነችው ጽዮን ንጽሕት ድንግል ማርያም ናት:: ዘፍ. 3÷15 ፤ መዝ.73÷14::

በአጠቃላይ በትንቢትና በተምሳሌት ሲነገር የነበረው የመስቀል ነገር የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በፍጹም ድንግልና ተጸንሶ በፍጹም ድንግልና ተወልዶ በዚሁ በተዋሐደው ሥጋ በቀራንዮ በክቡር መስቀል ላይ በመሰቀሉ አማናዊ ሆኖአል:: ስለዚህ መስቀልን ስናስብ ክርስቶስን፣ ክርስቶስን ስናስብ መስቀልን ማሰባችን ነው:: መስቀልን ማሰብ ተሰቃዩን ክርስቶስን ማሰብ ነው::

**መስቀልን ለምን እናከብራለን?**

ቅዱስ መስቀልን በፍጹም ክብር እናከብረዋለን:: መስቀልን የምናከብርበትም ምክንያት:-

1. የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅርና ውለታ የምናዘክርበት ነው:: መስቀል ሲነሣ በዚያ ላይ ሳይገባው ለእኛ ሲል ሥጋችንን ተዋሕዶ የሞተልንን ያውም ከሁሉም ባነሰና በተናቀ ሞት ሞቶ በመስቀል ላይ ሥጋውን የቆረሰልንንና ደሙን ያፈሰሰልንን ኢየሱስ ክርስቶስን መዘከር ማለት በመሆኑ መስቀልን በማክበር የተደረገልንን የማዳን ሥራ ማወቅ ነው:: ዮሐ.3÷16:: ጌታችን በቃለ ወንጌሉ «ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚ ያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዳ ይኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባል» ብሎ የተናገ ረውን ቃል በፍቅሩ የፈጸመበት ነውና:: ይህንን መስቀል ማዘከር እንዲገባም «ከዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስ ቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተስሎ ነበር» ገላ 3÷1::

2. ለዓለም ድኅነት የሆነው ሥጋውና ደሙ የተፈተተበት ነው:: የሰው ኃጢአት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተሻረበት በዚሁ በክርስቶስ መሥዋዕትነት የሰው ልጅ የተገባለት ቃል ኪዳንና የተሰጠው ተስፋ የተፈጸመበት ነው:: ይኸውም ኢየሱስ ክርስ ቶስ ራሱን አንድ ጊዜ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ከዚያ በኋላ በዚሁ በተፈጸመው የማዳን ሥራ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚሆን ሥጋውንና ደሙን ለኃጢአት ማስተሰረያ አድርጎ የሰጠበት ነው:: «የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል» ዕብ 10÷10::

3. መስቀል ዲያብሎስ የተሸነፈበትና ያፈረበት እንዲሁም የዕዳ ደብዳቤያችን የተደመሰሰበት ነው::

ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን እንደሚከተለው ገልጾአል:- «በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንም በትእ ዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፤ አለቅነ ትንና ሥልጣናትን ገፎ ÷ ድል በመን ሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው::» ቈላ.2÷14–15:: ስለሆ ነም ዲያብሎስ ተጠርቆና ተጨንቆ የተወገደውና አለቅነቱንና ሥልጣኑን የተገፈፈው በቅዱስ መስቀል ነው:: ዛሬም ዲያብሎስን የምናባርረው ድል በተነሣበት በዚሁ በክቡር መስቀል ነው::

4. በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጠብ ግድግዳ የፈረሰበትና ሰው የተወሰደበት ሰላም ተመልሶለት ከፈጣሪው ጋር የታረቀበት ነው:: «እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሐደ በዐዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ÷ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸ ውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው::» ኤፌ 2÷14–17::

5. **መስቀል የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ዙፋኑ ነው::**

መስቀል በዕለተ ዓርብ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ኢየሱስ ክርስቶስ መላ አካሉን አሳርፎበት የዋለ ዙፋን ነው:: ለዚህ ዙፋንም ክብርና ስግደት የሚገባ መሆኑን ክቡር ዳዊት «ወንሰ ግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ፤ የጌታችን እግር በቆመበት ሥፍራ ሁሉ እንሰግዳለን »ብሏል:: መስቀል የጌታችን ቅዱሳን እግሮቹ ብቻ ሳይሆኑ መላ አካሉ የዋለበት የዕለተ ዓርብ ዙፋኑ፤ ሥጋ ውንና ደሙን የፈተተበት መቅ ደሱ ታላቅ በመሆኑ ስግደትና ክብር ይገ ባዋል:: መዝ. 131÷7::

6. **መስቀል መንፈሳዊ ኃይል የምናገኝበት ነው::**

«የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ነገረ መስቀሉ ለምናምን ኃይላችን መሆኑን ተናግሮአል:: 1ቆሮ.1÷18:: ክቡር ዳዊትም «ዘይሜህሮን ጸብአ ለእደውየ፤ ለእጄ ሰልፍን ያስተምራቸዋል» ሲል በጣታችን በመስቀል አምሳያ ላይና ታች ግራና ቀኝ አማትበን አጋንንትን እንደምናሸንፍ ገልጾአል:: ስለሆነም መስቀል ትምክህታችን ነው:: «ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ::» ገላ 6÷14::

ነገር ግን ምንም እንኳ መስቀል እንዲህ የከበረ ቢሆንም ለክርስቶስ ለአምላካቸው ጠላቶች ሆነው የተነሡ ወገኖች የመስቀሉም ጠላቶች ሆነው እንደሚነሡ ሐዋርያው አስቀድሞ ነግሮናል፤ «ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና... መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው፤ አሳባቸው ምድራዊ ነው::» ፊልጵ. 3÷18–19::

መስቀል ከዚህ በላይ ከተገለጹት ነገሮች በተጨማሪ:- ራስን ለእግዚአብሔር መስጠትንና ከዚህ ዓለም ግብር መለየትን ያመለክታል:: ቅዱስ ጳውሎስ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» ማለቱ ተሰቅሎ ሞቶ ሳይሆን በዚህ ዓለም ሳለ ሕይወቱ ክርስቶስ ሥራ የሚሠራበት እንጂ እርሱ የራሱን ፈቃድ የሚያደርግበት አለመሆኑን መናገሩ ነው:: ገላ. 2÷20::

ጌታችንም «እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ» ማለቱ የራስን ፈቃድ ትቶ ራስን ለእግዚአብሔር በማስገዛት እርሱ ከተቀበለው የመከራ ጽዋ ለመቋደስ መዘጋጀትን ነው:: ሉቃ 9÷ 23::

«የኢየሱስ ክርስቶስም የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከም ኞቱ ጋር ሰቀሉ» ማለቱም በመስቀል የሚያምን ክፉ ግብርን እኩያት ፍትወታትን ማስወገድ እንደሚገባው የሚገልጽ ነው:: ገላ.5÷24::

ስለዚህ መስቀልን ስናከብር አምላካችን ያደረገልንን ውለታ እያሰብን ታስቦ በማይደረስበት ተነግሮ በማያልቅ ቸርነቱ የሰጠንን ክቡር ሥጋውንና ቅዱስ ደሙን እየተቀበልን በሕይወታችን ክርስቶስ በእኛ እንዲኖርበት ክፉ ፈቃዳትን በማራቅ በትእ ምርተ መስቀል አማትበን አጋንንትን በማባረር መስቀሉን እንድና ከብር ያስፈልጋል:: የእግዚአብሔር ቸርነት÷ የእመቤታችን አማላጅነት÷ የቅዱሳን ጸሎት አይለየን:: አሜን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ባሕረ ሐሳብ ምንድን ነው? ስሌቱስ እንዴት ነው?

ቤተ ክርስቲያናችን በአዲስ ዘመን መባቻ /መስከረም 1 ቀን/ በዓመቱ በዓላት የሚውሉበትን አጽዋማት የሚገቡበትን ቀናትና ዕለታት በባሕረ ሐሳብ እያሰላች ለምእመናን እንደ ምታውጅ በዚያውም ላይ ተጠቃሚ ለሚሆኑ ልዩ ልዩ ወገኖችም እንደ ምታሳውቅ ይታወቃል፡፡ ይሁንና የስሌቱ አኳኋን ለምንገኝ ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ እም ብዙም አይታወቅምና ሊረዳን በሚችል መጠን አብራርታችሁ እንድታቀርቡልን እጠይቃለሁ፡፡

*<u>ውድ አንባብያችን</u>፡- ላላኩልን ጥያቄ የምንሰጠው ምላሽ እርስዎ እንደ ገለጹት በየሥፍራው ለሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ እጅግ የሚጠቅም ሆኖ ስላገኘነው አብራርተን ለማቅረብ ጥረት አድርገናል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የጥያቄውን መልስ አጠናቅሮ በማቅረብ የረዳንን ተባባሪ ዘጋቢያችንን ጌታቸው በቀለን እናመሰግናለን፡፡*

ባሕረ ሐሳብ የግእዝ ቃል ሲሆን በዐረብኛ አቡሻኽር በአማርኛ የዘመን አቆጣጠር ይባላል፡፡ ባሕረ ሐሳብን ወይም የዘመን አቆጣጠርን የቀመረው 12ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ድሜጥሮስ ነው፡፡ ቅዱስ ድሜጥሮስ፡-

- ❖ ነነዌ፣ በአተ ጾም /የዐቢይ ጾም መግቢያ/ ፣ጾመ ሐዋርያት – ከሰኞ
- ❖ ደብረ ዘይት፣ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ – ከእሑድ
- ❖ ርክበ ካህናት፣ጾመ ድኅነት /ከረቡዕ/
- ❖ ዕርገት –ከሐሙስ
- ❖ ስቅለት – ከዓርብ

ባይወጡ /በነዚህ ቀናት ቢውሉ /እያለ ይመኝ ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ መጥቶ፣ «ድሜጥሮስ ሆይ÷ ይህ ሁሉ በሐሳብ ይፈጸማል? ቢያደርጉት ነው እንጂ፤ ሱባኤ ግባ» ብሎታል፡፡ ቅዱስ ድሜጥሮስም በአንድ የጸሎት ጊዜው ሰባት ጊዜ አቡነ ዘበሰማያት እየደገመ ከቀኑ ሰባት ሱባኤ ከሌሊቱ 23 ሱባኤ ግባ ብሎታል፡፡ ስለምን የቀኑን አሳነሰው ቢሉ ቀን በማስተማር፣ የተጣሉትን በማስታረቅ ስለሚውል ሌሊት ግን ከዚህ ሁሉ ነጻ ነውና የሌሊቱን ሱባኤ አበዛው፡፡ ከቀኑ ሰባት ሱባኤ 7X7=49 አቡነ ዘበሰማያት ይደግማል፡፡ በ30 ሲገደፍ /ሲካፈል/ ትርፉን /19ኙን/ ጥንተ መጥቅዕ ብሎታል፡፡ ከሌሊቱ ደግሞ 23X7=161 አቡነ ዘበሰማያት ይደግም ነበር፡፡ በ30 ሲካፈል ትርፉን /11ዱን/ ጥንተ አበቅቴ ብሎታል፡፡ መጥቅዕ ለቀን አበቅቴ ለሌሊት ያገለግላሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ድሜጥሮስ የአጽዋማትና የበዓላት ኢይዓርግ ኢይወርድ /ከዚህ አይወጣም ከዚህ አይወርድም/ ተገልጾለት በሰባት አዕዋዳት አውዶ፣ በሶርያ፣ በአንጾኪያ፣ በሮም ላሉት ለሦስቱ ሊቃነ ጳጳሳት አራተኛ በኢየሩሳሌም ላለው ኤጲስ ቆጶስ ጽፎ ሰደደላቸው፡፡ እነርሱም ተቀብለው ሐዋርያት በዲድስቅልያ ካስተማሩት ጋር አንድ ሆኖ ቢያገኙት ደስ ብሏቸው ተቀብለው ባሕረ ሐሳቡን አስተምረውታል፡፡

<u>ባሕረ ሐሳብ ማለት ምን ማለት ነው ?</u>

ባሕረ ሐሳብ ማለት ቁጥር ያለው ዘመን ማለት ነው፡፡ አንድም ሐሳበ ባሕር ይለዋል፡፡ ስለ ምን ዘመንን ባሕር አለው? ቢሉ፡- ባሕር ከምንጩ፣ ከነቅዑ ወጥቶ ቢፈስ አያልቅም፣ ዘመንም ምጽአተ ክርስቶስ እስኪያግደው ድረስ ሰውን እያሳለፈ ሲመላለስ ይኖራል፡፡ አንድም ከባሕር ሁከት እንዳይታጣ፣ ከዘመንም ሁከተ ሥጋ ሁከተ ነፍስ አይታጣምና፡፡ አንድም ከባሕር ማዕበል ሞገድ እንዲነሣሣ ከዘመንም ማዕበለ ኃጢአት ማዕበለ ክህደት ይነሣልና፡፡ መልሕቅ ጥለው፣ ዓላማ ተከትለው የባሕር ሁከቱን ማዕበለ ሞገዱን ፀጥ እንዲያደርጉት፣ የዘመንንም ሁከተ ሥጋ ሁከተ ነፍስ፣ ማዕበለ ኃጢአት ማዕበለ ክህደት ጹመው ጸልየው ምህላ ይዘው ፀጥ ያደርጉታልና፡፡ አንድም ባሕረ ሐሳብ ባለው መርሐ ዕውር የሚል አብነት ይገኛል፡፡ የዕውር መሪ፣ ዕውርን የሚመራ ማለት ነው፡፡ ዕውርን /ዐይነ ስውርን/ እሾህ እንዳይወጋው፣ እንቅፋት እንዳይመታው፣ ባሕር ጠልቆ ገደል ወድቆ እንዳይሞት መሪው ጠብቆና መርቶ ከቤት እንዲያደርሰው፣ የዘመን ቁጥርም አላዋቂውን ሰው ሶከ ኃጢአት /የኃጢአት እሾኽ/ እንዳይወጋው እቅፍተ ሥጋ እቅፍተ ነፍስ እንዳያገኘው፣ በባሕረ ኃጢአት ሰጥሞ በክህደት ወድቆ እንዳይሞት ጠብቆና መርቶ እንደ ነቢያት /ዳንኤልና ዕዝራ/ አጽዋማት በዓላት የሚውሉበትን ወደ ማወቅ ያደርሰዋልና፡፡

ባሕረ ሐሳብን ካህኑም ክርስቲያኑም፤ ክርስቲያኑም ካህኑም ሊማረው ይገባል፡፡ ከሀገሩ ተሰዶ፣ ተማርኮ አሕዛብ ሀገር ቢሄድ እንኳን ጾም አይገድፍም፤ በዓል አይሽርም፤ ምክንያቱም አጽዋማት የሚገቡበትን በዓላት የሚውሉበትን ተምሯልና፡፡ ባሕረ ሐሳብን ያልተማረ ካህን÷ ካህን፤ መነኩሴውም መነኩሴ፤ መባል አይገባውም፡፡ ባሕረ ሐሳብን ያልተማረውን ካህን በደረቅ ወንዝ፣ ሰው በሌለው መንደር ይመስለዋል፡፡ ደረቅ ወንዝ ነጋድያን ሲሄዱ የዛፉን ፍሬ ለምለሙን መስክ አሻግረው አይተው ከዚያ አርፈን ጠል ነስተን እንሄዳለን ብለው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ ሲደርሱ ውኃ ባጣቡት ጊዜ ተሳቅቀው ይሄዳሉ፡፡ ሰው የሌለው ሀገርም እንደዚሁ እንግዶቹ መንደሩን አይተው ከዚያ አድረን እንሄዳለን ብለው ከዚያ ሲደርሱ ሰው ባጡበት ጊዜ ተሳቅቀው ይሄዳሉ፡፡ ይህንንም መጽሐፍ /ባሕረ ሐሳብን/ ያልተማረውን ካህን ጠምጥሞ፣ መነሳንሱን ይዞ፣ ቀሚሱን አንጽቶ ሲሄድ ባዩት ጊዜ ምእመናን አጽዋማትን በዓላትን ጠይቀን እንረዳለን ብለው ይቀርባሉ፡፡ ባጡበት ጊዜ ተሳቅቀው ይሄዳሉ፡፡

ዓለም ከተፈጠረ አንሥቶ እስከ ልደተ ክርስቶስ ድረስ ያለው ዘመን ዘመነ ብሉይ፣ ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ይባላል፡፡ ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ያለው ዘመን ዓመተ ምሕረት፣ ዓመተ ሥጋዌ፣ ዘመነ ሐዲስ ይባላል፡፡ መላው ደግሞ ዓመተ ዓለም ይባላል፡፡

በድሜጥሮስ ቀመር የዘመን መስፈሪያዎች ወይም መቁጠሪያዎች ሰባት አዕዋዲት አሉ፡፡ እነዚህም፡-

1.ዐውደ ዕለት 2.ዐውደ ወርኅ
3.ዐውደ ዓመት 4. ዐውደ አበቅቴ
5. ዐውደ ፀሐይ 6. ዐውደ ማኅተም
7. ዐውደ ቀመር ናቸው፡፡

ለዘመናት መቁጠሪያ የሚያገለግሉት፡- ቀመር፣ ዓመት፣ ወር፣ ሳምንት፣ ዕለት፣ ቀን፤ ሰዓት፣ ካልዒት ቅጽበት /ሰከንድ/ ናቸው፡፡ አራቱ ማለትም ዐውደ አበቅቴ፣ ዐውደ ፀሐይ፣ ዐውደ ማኅተምና ዐውደ ቀመር በዓመት የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ዓመት የተባለው በፀሐይ 365 ቀን÷ በጨረቃ ደግሞ 354 ቀን ነው ፡፡

ዕለት የተባለ 24 ሰዓት፤ አንድ ቀን የተባለ 12 ሰዓት፤ ካልዒት የተባለው አንድ ደቂቃ ነው፡፡ ዐውድ ወይም ዙር እንደገና ተመላልሶ መምጣትን ያመለክታል፡፡

*<u>ዐውደ ዕለት</u>*፡- ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት ሰባቱ ዕለታት ናቸው፡፡ እነዚህም ዐውደ ወርኅን ወይም ወሮችን ለማስገኘት በሰባት፣ በሰባት ሲመላለሱ ይኖራሉ፡፡

*<u>ዐውደ ወርኅ</u>*፡- በፀሐይ ዘወትር 30 ቀን ነው፡፡ በጨረቃ ግን አንድ ወር 30፤ አንድ ጊዜ 29 ይሆናል፡፡ እነዚህም ዓመትን ለማስገኘት በ30 በ30 ሲመላለሱ ይኖራሉ፡፡

*<u>ዐውደ ዓመት</u>*፡- በፀሐይ 365 ቀን፣ በጨረቃ 354 ቀን፣ በከዋክብት 364 ቀን ነው፡፡

*<u>ዐውደ አበቅቴ /ንዑስ ቀመር/</u>*፡- 19 ዓመት ነው፡፡ የ19 ዓመት ተመላልሶ መምጣት ማለት ነው፡፡

*<u>ዐውደ ፀሐይ</u>*፡- 28 ዓመት ነው፡፡ አንድ ዐውደ ፀሐይ 19 ጊዜ ሲመላለስ አንድ ዐቢይ ቀመር ይሆናል፡፡ (19×28 =532)

*<u>ዐውደ ማኅተም /ማዕከላዊ ቀመር/</u>*፡- 76 ዓመት ነው፡፡

ዐውደ ማኅተም ሰባት ጊዜ ሲመላለስ አንድ ዐቢይ ቀመር ይሆናል ፡፡ (7×76=532)

*<u>ዐውደ ቀመር /ዐቢይ ቀመር/</u>*፡- 532 ዓመት ነው፡፡



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

## የዘመነ ሐዲስ አጽዋማትና በዓላት በድሜጥሮስ ቀመር

በባሕረ ሐሳብ ትምህርት መሠረት ያለፉትን ዓመታት፣ አሁን ያለንበትን ዓመትም ሆነ ወደፊት እስከ ምጽአት የሚመጡትን ዓመታት ከዚህ በታች በተገለጹት ቀመሮች እየሠራን የየዘመኑን አቆጣጥር፤ አጽዋማት የሚገቡበትን፤ በዓላት የሚውሉበትን ማወቅ እንችላለን:: የሚጀምረውም ከወንጌላዊው ነው:: የዚህ ቀመር አሠራር ግልጽ እንዲሆንልን የ1996 ዓ.ምን መሠረት በማድረግ እንመለከታለን::

1. ዓመተ ዓለም /ዓ.ዓ/:–

ዓመተ ዓለም ማለት የዓመተ ምሕረትና የዓመተ ኩነኔ ድምር ነው:: ዓመተ ፍዳ /ዓመተ ኩነኔ/ የተባለው ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው 5500 ዘመን ነው:: ዓመተ ምሕረት የሚባለው ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ዘመን /አሁን በያዝነው 1996 ዓ.ም/ ነው:: በዚህም መሠረት:–

*ዓመተ ዓለም =ዓመተ ምሕረት +ዓመተ ኩነኔ*

በዚህ ቀመር መሠረት የ1996 ዓ.ም በዓመተ ዓለም ስንት ነው?

ዓመተ ዓለም = ዓመተ ምሕረት + ዓመተ ኩነኔ

1996 + 5500

= 7496 ዓ.ዓ ነው::

2. ወንጌላዊው

ወንጌላዊውን /ዘመኑን ማን እንደሆነ/ ለማወቅ ዓመተ ኩነኔን ከዓመተ ምሕረት ጋር በመደመር ለአራቱ ወንጌላውያን /ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ/ በማካፈል የምናገኘው ነው:: የምናገኘው ድርሻ መጠነ ራብዒት ይባላል:: በዚህም መሠረት:–

ቀሪው 1 ከሆነ ዘመኑ ማቴዎስ ነው፤
ቀሪው 2 ከሆነ ዘመኑ ማርቆስ ነው፤
ቀሪው 3 ከሆነ ዘመኑ ሉቃስ ነው፤

ምንም ቀሪ ባይኖር ዘመኑ ዮሐንስ ነው:: ከነዚህ ውጭ ግን የሚመጡ ቀሪዎች የሉም:: ቀመሩም:–

ወንጌላዊ= ዓመተ ምሕረት +ዓመተ ኩነኔ / 4

❖ በዚህ ቀመር መሠረት የ1996 ዓ.ም ወንጌላዊው ማነው?

ወንጌላዊው= 1996+5500 / 4 = 7496 / 4 = 1874 ቀሪ 0

ከዚህ የምንረዳው ቀሪው ባዶ /0/ ስለሆነ ወይም ምንም ቀሪ ስለሌለው፣ የ1996 ዓ.ም ወንጌላዊው ዘመነ ዮሐንስ ነው ማለት ነው:: 1874 የአንድ ወንጌላዊ ድርሻ ወይም መጠነ ራብዒት ይባላል::

3. መባቻ /መስከረም 1 ቀን/:–

መባቻን ለማወቅ ዓመተ ዓለምን ከአንድ ወንጌላዊ ድርሻ /መጠነ ራብዒት / ጋር ተደምሮ ለሰባቱ ዕለታት ተካፍሎ:–

ቀሪው 1 ከሆነ መባቻው ማክሰኞ ይሆናል
ቀሪው 2 ከሆነ መባቻው ረቡዕ ይሆናል
ቀሪው 3 ከሆነ መባቻው ሐሙስ ይሆናል
ቀሪው 4 ከሆነ መባቻው ዓርብ ይሆናል
ቀሪው 5 ከሆነ መባቻው ቅዳሜ ይሆናል
ቀሪው 6 ከሆነ መባቻው እሑድ ይሆናል

ያለ ቀሪ ቢካፈል መባቻው ሰኞ ይሆናል::

መባቻ =ዓመተ ዓለም + መጠነ ራብዒት / 7

❖ በዚህ ቀመር መሠረት የ1996 ዓ.ም መባቻ /መስከረም 1 ቀን/ መቼ ነው?

መባቻ =7496 + 1874 / 7 =9370 / 7 =1338 ቀሪ 4

ከዚህ የምንረዳው ቀሪው « 4 » ስለሆነ፤ ከላይ በተገለጸው መሠረት የ1996 ዓ.ም መባቻ /መስከረም 1 ቀን/ ዓርብ ዕለት ይውላል ማለት ነው ::

4. ወንበር:–

ዓመተ ዓለምን ለ19 ዓመት /ንዑስ ቀመር / ተካፍሎ ከተረፈው ላይ አንድን ለዘመን አትቶ /ሰጥቶ/ የተረፈው ወንበር ይባላል:: ወንበር ከአንድ እስከ 19 ድረስ በቀጥታ የሚጓዝ የዘመን መስፈርት የሆነ ቁጥር ነው ::ከአገልግሎቱም አበቄትንና መጥቅዕን ለማውጣት የሚያገለግል ቀመር ነው:: ይህ 19ኛው ዓመት ፀሐይና ጨረቃ እንደ ጃንጥላና እንደ ሰው ከላይና ከታች ሆነው ለተወሰኑ ሰዓታት /ጊዜያት/ የሚጓዙበት ወቅት ነው:: ስለዚህ ወንበር ምንጩ ይህ ነው:: ቀመሩም:–

ወንበር = ዓመተ ዓለም / 19 ከቀሪው ላይ 1 መቀነስ

የባሕረ ሐሳብ መምህራን እንደሚገልጹት ከቀሪው ላይ አንድ የምንቀንሰው አንድን ለዘመን መስጠትን ያመለክታል:: በዚህ ቀመር መሠረት የ1996 ዓ. ም ወንበሩ ስንት ነው?

ዓመተ ዓለም የተባለ 1996 + 5500 = 7496 ነው ::

ወንበር = 7496 / 19 = 394 ቀሪ 10

ከቀሪው 10-1=9 ወንበር ወጣ

ከዚህ የምንረዳው የ1996 ዓ.ም ወንበሩ 9 ነው ::

5. አበቅቴ

አበቅቴ ማለት ተረፈ ዘመን ማለት ነው :: ይኸውም የፀሐይ ዐውደ ዓመት 365 የጨረቃ ደግሞ 354 ነው:: የነዚህ ልዩነት 11 /365 -354 =11/ ነው:: ይህ ተረፈ ዘመን /አበቅቴ /ነው:: ጥንተ አበቅቴ የተባለውም ነው:: አበቅቴን ለማግኘት ወንበር በ11 ተባዝቶ ከሠላሳ ቢበልጥ ትርፉ፤ ከሠላሳ ቢያንስ ራሱ ማለትም የተገኘው ቁጥር አበቅቴ ነው:: ቀመሩም:–

አበቅቴ = ወንበር X 11 / 30

❖ በዚህ ቀመር መሠረት የ1996 ዓ.ም አበቅቴው ስንት ነው ?

አበቅቴ =9X11 / 30 = 99 / 30 = 3 ቀሪ 9

ከዚህ የምንረዳው ቀሪው 9 ስለሆነ ፣ አበቅቴ 9 ነው::

የአበቅቴ ጥቅሙ ምንድን ነው ?

የአበቅቴ ጥቅሙ ከሕፀፅ ወርኅ እና ከዕለት ጋር ተደምሮ ሌሊትን ያስገኛል :: ሕፀፅ ማለትም ጉድለት ማለት ነው:: ይኸውም ጨረቃ በአንድ ወር 30፤ በሚቀጥለው ወር 29 ቀን ትጓዛለች:: ይህ በየሁለት ወራት መካከል ያለው ጉድለት /ሕፀፅ/ ይባላል :: በዚህ መሠረትም የመስከረምና የጥቅምት ወራት ሕፀፅ 1፣ የኅዳርና የታኅሣሥ 2፣ የጥርና የየካቲት 3፣ የመጋቢትና የሚያዝያ 4፣ የግንቦትና የሰኔ 5፣ የሐምሌ÷ የነሐሴና የጳጉሜን 6 ነው:: በጠቅላላው በዓመት ውስጥ 6 ሕፀፅ አለ:: ይህም ማለት በ 1 ዓመት ውስጥ 6 ወሮች ሙሉ 30 ቀናት፣ 6 ወሮች ጎዶሎዎች /ሕፀፅ/ ይባላሉ ::

ሌሊትን የምናገኝበት ቀመር

ሌሊት = አበቅቴ + ሕፀፅ + ዕለት

በባሕረ ሐሳብ ትምህርት ሌሊቱም ይቆጠራል::

ለምሳሌ:– የመስከረም 1 ቀን 1996 ዓ.ም ሌሊቱ ስንት ነው?

አበቅቴው 9 ነው:: የመስከረም ወር ሕፀፅ 1 ነው፤ ወቅቱም ያው መስከረም 1 ስለሆነ:: በቀመሩ ስንሠራው እንደሚከተለው ነው::

ሌሊት = 9+1+1

11 ሌሊት ይሆናል ::

4. መጥቅዕ

መጥቅዕ ማለት ደወል ማለት ነው:: መጥቅዕ የሚውልበትን ዕለት መሠረት በማድረግ ለበዓላትና ለአጽዋማት ማውጫነት እንጠቀምበታለን:: መጥቅዕን ለማግኘት የወንበርን ቁጥር በ19 አባዝተን ለ30 በማካፈል እንቀምራለን:: ስለዚህ መልአኩ ለቅዱስ ድሜጥሮስ 19 ጥንተ መጥቅዕ ይሁንህ ብሎታል::

መጥቅዕ ደወል ነው:: ደወል በተደወለ ጊዜ ተማሪ ወደ ክፍሉ እንደሚሰበሰብ ሁሉ መጥቅዕም አጽዋማትንና በዓላትን ያሰባስባልና::

መጥቅዕን የምናገኝበት ቀመር:–

መጥቅዕ = ወንበር X 19 / 30

በዚህ ቀመር መሠረት 1996 ዓ.ም መጥቀዕ ስንት ነው?

መጥቅዕ =9X19 / 30 =171 / 30 =5 ቀሪ 21

የ1996 ዓ.ም መጥቅዕ 21 ነው ::

መጥቅዕ ከ14 በላይ ከሆነ በመስከረም፤ ከ14 በታች ከሆነ ግን በጥቅምት ወር ይውላል:: 14 ራሱ ግን መጥቅዕ አይሆንም:: መጥቅዕ በሁለቱ ወሮች ብቻ ነው የሚውለው:: መጥቅዕ ቢበዛ አበቅቴ ቢያንስ፣ አበቅቴ ቢበዛ መጥቅዕ ቢያንስ ከ30 አይወጣም ከ30 አይወርድም /አበቅቴ + መጥቅዕ = 30/::

ተውሳክ

ተውሳክ ማለት ጭማሪ ማለት ነው:: በዓላቱ የሚውሉበትን ለማወቅ ከመጥቅዕ ጋር አብሮ እየተጨመረ የሚቆጠር ነው:: ሁለት ዓይነት የተውሳክ አቆጣጠር አለ:: ይኸውም:–

1.የዕለት ተውሳክ
2.የአጽዋማትና የበዓላት ተውሳክ ናቸው ::

1. የዕለታት ተውሳክ:– በቅዳሜ ይጀመራል:: የዕለታት ተውሳክን ለማግኘት የሚያስችለን መጥቅዕ ከዋለበት ሳኒታ /ማግሥት/ ጀምረን ነነዌ እስከ ዋለበት ቀን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ስንቆጥር ከ 122 እስከ 128 ቀን ነው የሚሆነው ::

ከመጥቅዕ ሳኒታ ነነዌ እስከ ዋለችበት እየቆጠሩ 120ውን በ30 እየገደፉ /እያካፈሉ/ ቀሪውን በመያዝ ተውሳከ ዕለት ይገኛል:: መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳከ ጋር ተቆጥሮ ጾመ ነነዌን ያስገኛል:: /በሰንጠረዥ ውስጥ የተገለጸውን ይመልከቱ/::

| ዕለት | የቀኑ ብዛት በ 30 ሲገድፍ/ ማካፈል/ | ተውሳከ /ጭማሪ /ቀሪ |
|---|---|---|
| ቅዳሜ | 128÷30 | 8 |
| እሁድ | 127÷30 | 7 |
| ሰኞ | 126÷30 | 6 |
| ማክሰኞ | 125÷30 | 5 |
| ረቡዕ | 124÷30 | 4 |
| ሐሙስ | 123÷30 | 3 |
| ዓርብ | 122÷30 | 2 |

2.<u>የአጽዋማትና የበዓላት ተውሳክ</u>

የአጽዋማትና የበዓላት ቱውሳክ መሠረታቸው ነነዌ ነው:: ከነነዌ ጀምረን አጽዋማት በዓላት እስከ ዋለበት ነው የምንቆጥረው:: በዚህም መሠረት ከነነዌ እስከ ዐቢይ ጾም 14 ቀን ይገኛል:: እስከ ደብረ ዘይት 41 ቀን፣ እስከ ሆሣዕና 62 ቀን፣ እስከ ስቅለት 67 ቀን፣ እስከ ትንሣኤ 69 ቀን፣ እስከ ርክበ ካህናት 93 ቀን፣ እስከ ዕርገት 108 ቀን፣ እስከ ጰራቅሊጦስ 118፣ እስከ ጾመ ሐዋርያት 119 ቀን፣ እስከ ጾመ ድኅነት 121 ቀን ይገኛል:: ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን በዓላት ተውሳካቸውን ለማግኘት በያንዳንዱ ክፍል ያለውን ቁጥር ከ30 በታች ያሉት እንዳሉ ሆነው ከ30 በላይ ያሉትን ሁሉ በ30 እየገደፉ ትርፉን ከመጥቅዕ ጋር እየጨመሩ ሲቆጥሩ በየዓመቱ የሚውሉበትን ቀን ለማግኘት እንችላለን::

| | በዓላትና አጽዋማት | የቀኑ ብዛትና ስሌቱ | ተውሳክ /ቀሪ/ |
|---|---|---|---|
| ከነነዌ ጾም እስከ | ዐቢይ ጾም | 14 | 14 |
| | ደብረ ዘይት | 41÷30 | 11 |
| | ሆሣዕና | 62÷30 | 2 |
| | ስቅለት | 67÷30 | 7 |
| | ትንሣኤ | 69÷30 | 9 |
| | ርክበ ካህናት | 93÷30 | 3 |
| | ዕርገት | 108÷30 | 18 |
| | ጰራቅሊጦስ | 118÷30 | 28 |
| | ጾመ ሐዋርያት | 119÷30 | 29 |
| | ጾመ ድኅነት | 121÷30 | 1 |

<u>በሰንጠረዥ</u>
<u>ውስጥ ስንመለከት</u>

7. ነነዌ

የአጽዋማትና የበዓላት መሠረታቸው ነነዌ ነው:: ነነዌ ተውሳክ የለውም፤ በዓለ መጥቅዕ በመስከረም ሲሆን ጾመ ነነዌ በጥር፣ በዓለ መጥቅዕ በጥቅምት ከዋለ ጾመ ነነዌ በየካቲት ትውላለች :: ነገር ግን በዓለ መጥቅዕ በመስከረም ሆኖ ከዕለታት ተውሳክ ጋር ተደምሮ ከ30 ቢበልጥ በትርፍ ምክንያት ጾመ ነነዌ በየካቲት ትውላለች:: መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋር ተደምሮ ከ30 ቢያንስ ራሱ የተገኘው ቁጥር ነነዌ ይባላል::

ቀመሩም:- ነነዌ = መጥቅዕ + የዕለታት ተውሳክ

❖ በቀመሩም መሠረት የ1996 ዓ.ም ጾም ነነዌ መቼ ትውላለች?

ከላይ እንዳየነው የ1996 ዓ.ም. መጥቅዕ የዋለው መስከረም 21 ቀን ነው:: መስከረም 21 ቀን የዋለበትን ዕለት ስንቆጥር ሐሙስ ዕለት ነው የሚሆነው:: ከላይ በሠንጠረዥ እንደ ተገለጸው የሐሙስ ተውሳክ ሦስት ነው::

ነነዌ = መስከረም 21 + የሐሙስ ተውሳክ 3
= 21+3
= <u>ጥር 24</u>

- ነነዌ በጥር ወር የሆነው መጥቅዕ በመስከረም ስለ ዋለ ነው::

በኢይዓርግና በኢይወርድ /ከዚህ አይወጣም÷ ከዚህ አይወርድም / መካከል የ35 ቀናት ልዩነት ይገኛል:: ይህም የ35ቱ መጻሕፍተ ሐዲሳት ምሳሌ እንደ ሆነ የባሕረ ሐሳብ መምህራን ያስረዳሉ:: ይህንንም የሚቀጥለውን ሠንጠረዥ በመመልከት መረዳት እንችላለን:: በኢ

**የአጽዋማትና የበዓላት ኢይዓርግ ኢይወርድ /ገደብ/**

| አጽዋማት በዓላት | ኢይወርድ /ከዚህ በታች አይወጣም / | ኢይአርግ /ከዚህ በታች አይወርድም/ |
|---|---|---|
| ነነዌ | ጥር 17 | የካቲት 21 |
| ዓቢይ ጾም | የካቲት 1 | መጋቢት 5 |
| ደብረ ዘይት | የካቲት 28 | ሚያዝያ 2 |
| ሆሳዕና | መጋቢት 19 | ሚያዝያ 23 |
| ስቅለት | መጋቢት 24 | ሚያዝያ 28 |
| ትንሣኤ | መጋቢት 26 | ሚያዝያ 30 |
| ርክበ ካህናት | ሚያዝያ 20 | ግንቦት 24 |
| ዕረገት | ግንቦት 5 | ሰኔ 9 |
| ፐራቅሊጦስ | ግንቦት 15 | ሰኔ 19 |
| ጾመ ሐዋርያት | ግንቦት 16 | ሰኔ 20 |
| ጾመ ድኅነት | ግንቦት 18 | ሰኔ 22 |



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

8. <u>አጽዋማት በዓላት</u>

አጽዋማት በዓላት የሚውሉበትን ዕለት ለማወቅ ቀመሩ፡-

አጽዋማት በዓላት = ነነዌ +የአጽዋማት በዓላት ተውሳክ

ዐቢይ ጾም = 14+24= 38 ÷ 30=1 ቀሪ 8

የዐቢይ ጾም /ስምንቱ/ ከነነዌ /24ቱ/ ስላነሰ ፤ ዐቢይ ጾም ነነዌ ከዋለበት ወር ወደ ሚቀጥለው ወር ይሻገራል። በዚህም መሠረት ዐቢይ ጾም የካቲት ስምንት ይውላል። ደብረ ዘይት = ነነዌ + የደብረ ዘይት ተውሳክ = ጥር 24 + 11 = 35

35÷30 = 1 ቀሪ 5

ደብረ ዘይት ቀሪ /5/ ከዐቢይ ጾም ቀሪ /8/ ስላነሰ ደብረ ዘይት ወደ መጋቢት ይሻገራል።

ሆሣዕና = ነነዌ+ የሆሣዕና ተውሳክ

ጥር 24+2 = 26 /ለ30 ስለ ማይከፈል እንዳለ ይያዛል/ የሆሣዕና /26/ ከደብረ ዘይት /5/ ስለሚበልጥ ሆሣዕና ደብረ ዘይት በዋለበት ወር ይውላል። እንዲህ እያለ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ይውላል።

## የ1996 ዓ.ም አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን በዚህ

| አጽዋማት በዓላት | ተውሳክ | ነነዌ | ድምር/ተውሳ ክና ነነዌ/ | ስሌት | የሚውልበትን ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| ዐቢይ ጾም | 14 | ጥር 24 | 38 | 38÷30= 8 ቀሪ | የካቲት 8 |
| ደብረ ዘይት | 11 | 24 | 35 | 35÷30= 5 ቀሪ | መጋቢት 5 |
| ሆሣዕና | 2 | 24 | 26 | 26 | መጋቢት 26 |
| ስቅለት | 7 | 24 | 31 | 31÷30=1 ቀሪ | ሚያዝያ 1 |
| ትንሣኤ | 9 | 24 | 33 | 33÷30=3 ቀሪ | ሚያዝያ 3 |
| ርክበ ካህናት | 3 | 24 | 27 | 27 | ሚያዝያ 27 |
| ዕርገት | 18 | 24 | 42 | 42÷30=12 ቀሪ | ግንቦት 12 |
| ጰራቅሊጦስ | 28 | 24 | 52 | 52÷30=22 ቀሪ | ግንቦት 22 |
| ጾመ ሐዋርያት | 29 | 24 | 53 | 53÷30=23 ቀሪ | ግንቦት 23 |
| ጾመ ድኅነት | 1 | 24 | 25 | 25 | ግንቦት 25 |

ለግንዛቤ ይረዳን ዘንድ ከ1993 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ያለው የዘመን አቆጣጠር እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

ከዚህ ሠንጠረዥ የምንገነዘበው፣

1.የአንዱን ዓ.ም ወንጌላዊ ካገኘን የቀጣዩ ዓመት ተከታታይ ሆኖ ነው የሚጓዘው፤ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ ፣ ዮሐንስ እያለ በቅደም ተከተላቸው መሠረት ወንጌላውያኑ ይውላሉ።

2.መባቻ /መስከረም 1/፡- ተከታታዩን ይዞ ነው የሚጓዘው፤ ሰኞ፣ ማክ ሰኞ፣ .....እያለ። ሆኖም ግን ለምሳሌ በ1995 ዓ.ም ወንጌላዊው ሉቃስ ነው፤ ረቡዕ ነበር የዋለው፤ ቀጣዩ የ 1996 ዓ.ም መባቻው ዓርብ ነው የሚውለው፤ ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ ስንሸጋገር ጳጉሜን 6 በመሆኗ አንድ ቀን ይዘላል። ይህም ስግር በመ ባል ይጠራል።

3.ወንበር፡- ከ1 እስከ 19 ባሉት ቁ ጥሮች መካከል ሲውል ይህም በየዓ መቱ አንድ ቁጥር እየጨመረ የሚሄ ድ ነው። የ1995 ዓ.ም 8 ነበር። የ1996 ደግሞ ዘጠኝ ነው።

4.አበቅቴ፡- በተያዘው ዓመት አበቅቴ ላይ 11 በመደመር የቀጣዩን ዓመት አበቅቴ ማግኘት ይቻላል። በየ19 ዓ መቱ /ባዶ/ ዜሮ ይሆናል። አልቦ አበቅቴ ተብሎ ይጠራል።

5.መጥቅዕ፡- ልክ እንደ አበቅቴ ተከታ ታይ ሲሆን በየዓመቱ መካከል 19 በመደመር የቀጣዩን ዓመት ማግኘት ይቻላል። በየ19 ዓመቱ አልቦ /ባዶ ወይም ዜሮ/ ይሆናል።

በዘመነ ሐዲስ የአጽዋማት በዓላት አወጣጥ በድሜጥሮስ ቀመር ይህን ይመስላል። ይህ ቀመር እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ቤተ ክርስቲያናችን የምትገለገልበት ሀብት ነው። በዚህም መሠረት የ1996 ዓ.ም ዘመን አቆጣጠ ር በድሜጥሮስ ቀመር ሲገለጽ የሚከ ተለው ነው። ይኸውም ወንጌላዊው /ዘመኑ/ ዮሐንስ ነው።

| ዓ.ም | ወን. | መባቻ | ወ. | አበ. | መጥ. | ነነዌ | ዐቢይ ጾም | ደ/ዘይት | ሆሣ. | ስቅ. | ትን. | ር/ካህናት | ዕርገት | ጰራ. | ጾመ ሐዋ | ጾመ ድኅ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1993 | ማቴ | ሰኞ | 6 | 6 | 24 | ጥር 28 | የካ12 | መጋ9 | መጋ 30 | 5 | ሚያ 7 | ግን 1 | ግን 16 | ግን 26 | ግን 27 | ግን 24 |
| 1994 | ማር | ማክ | 7 | 17 | 13 | የካ 18 | መጋ 2 | መጋ 29 | ሚያ 20 | ሚያ 25 | ሚያ 27 | ግን 21 | ሰኔ 6 | ሰኔ 16 | ሰኔ 17 | ሰኔ 19 |
| 1995 | ሉቃ | ረቡዕ | 8 | 28 | 2 | የካ 10 | የካ 24 | መጋ 21 | ሚያ12 | ሚያ 17 | ሚያ 19 | ግን 13 | ግን 28 | ሰኔ 8 | ሰኔ 9 | ሰኔ 11 |
| 1996 | ዮሐ | ዓርብ | 9 | 9 | 21 | ጥር 24 | የካ 8 | መጋ 5 | መጋ 26 | ሚያ 1 | ሚያ 3 | ሚያ 27 | ግን 12 | ግን 22 | ግን 23 | ግን 25 |



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

| አጽዋማት /በዓላት | የሚውሉበት ቀን | ዕለቱ |
|---|---|---|
| ቅዱስ ዮሐንስ | መስከረም 1 | ዓርብ |
| ጾመ ነነዌ | ጥር 24 | ሰኞ |
| ዐቢይ ጾም | የካቲት 8 | ሰኞ |
| ደብረ ዘይት | መጋቢት 5 | እሑድ |
| ሆሣዕና | መጋቢት 26 | እሑድ |
| ስቅለት | ሚያዝያ 1 | ዓርብ |
| ትንሣኤ | ሚያዝያ 3 | እሑድ |
| ርክበ ካህናት | ሚያዝያ 27 | ረቡዕ |
| ዕርገት | ግንቦት 12 | ሐሙስ |
| ጰራቅሊጦስ | ግንቦት 22 | እሑድ |
| ጾመ ሐዋርያት | ግንቦት 23 | ሰኞ |
| ጾመ ድኅነት | ግንቦት 25 | ረቡዕ |

ከዚህ ሠንጠረዥ የምንረዳው በመግቢያው ላይ እንደ ተገለጸው ነነዌ፣ ዐቢይ ጾም፣ጾመ ሐዋርያት የዋሉት ሰኞ፤ ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ እሑድ፤ ርክበ ካህናት፣ ጾመ ድኅነት ረቡዕ፤ ዕርገት ሐሙስ፤ ስቅለት ዓርብ መዋላቸውን ማረጋገጥ እንችላለን።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን ባሕረ ሐሳብ ተቀብላ ስታስተምር ቆይታለች፣ወደፊትም ታስተምራለች። የቅዱስ ድሜጥሮስን ቀመር አጽዋማትና በዓላት የሚገቡበትን፣ የሚውሉበትን ያለፉትንም ዓመታት የአሁኑንም የወደፊቱንም የዘመን አቆጣጠር ለማውጣት እንጠቀምበታለን።

በዚህም መሠረት በአዲስ ዘመን መባቻ /መስከረም 1 ቀን / የቅዱስ ዮሐንስ ዕለት /ርእሰ ዐውደ ዓመት/ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት÷ አባቶችና፣ ምእመናን በተገኙበት በዓላት የሚውሉበትን፣ አጽዋማት የሚያዙበትንና ኢይዓርግ ኢይወርዳቸውን ባሕረ ሐሳብን በማውጣት ያውጃሉ /ይናገራሉ/።

የባሕረ ሐሳብ /አቡ ሻኸር/ ትምህርት ቢቻል ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ በሊቃውንቱ እግር ሥር ሆነን መማር አለብን። የቀሰምነውንም ለትውልድ ልናስተላልፍ ይገባል። ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። አሜን።

## የኑፋቄው መሻ ዙር ...

/ከገጽ ፲፩ የዞረ/

ትክክለኛ ግንዛቤ የሌላቸው ወይም ወላዋይ መሆናቸው በአንድ ጉባኤ ለተላለፉ ትክክለኛ ውሳኔዎች / ከ17ኛው መ.ክ.ዘ ወዲህ ስለ ትምህርተ ሃይማኖታቸው ምንነት በትክክል መረዳት የተሳናቸው ብዙ ግብፃውያን ጳጳሳት ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል/ መጽናት ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል።

የቅብዐትና የጸጋ ልጆች ከሁለት ምእተ ዓመታት በላይ ከተ ዋሕዶ ሊቃውንት ጋር ባካሄዱት ክርክር ከ15 ያላነሱ ጉባኤያት ተሠርተዋል። የአንዳንድ ነገሥታት ፖለቲካዊ አዝማሚያና አድሏዊነት፤ የጥቂት ግብፃውያን ጳጳሳት ሐቁን የመመስከር ቁርጠኝነት ማነስ ከታየ ባቸው በቀር በሁሉም ጉባኤያት የርትዕት ተዋሕዶ ሃይማኖት ሊቃውንት የሚ በይንላቸው ረቺዎች፤ ተቅባትና የጸጋ ልጆች ደግሞ የሚበይንባቸው ተረቺዎች ነበሩ። የቅብዐትና የጸጋ ልጆች በአብ ዛኛው በተናጠል ሲቀርቡ÷ ግንባር ፈጥ ረው የተዋሕዶ ሊቃውንትን ለመቋቋም የሞከሩበትም አጋጣሚ አልጠፋም፤ ያሰቡት አልተሳካም እንጂ።

ከዚህ በመቀጠል በየዘመናቱ ከተሠሩት ጉባኤያት ውስጥ የሚጠቀሱትን ስምንት ያህል ጉባኤያትንና ከእነርሱም ጋር ተጓዳኝ የኾኑ ጠቃሚ ነጥቦችን በማውሳት የጽሑፉን የመጀመሪያ ምዕራፍ ለማጠቃለል እንሞክራለን። በዝርዝሩ ውስጥ የአንዳንድ ቦታዎችን ስም መጥቀስ ቢኖር መንፈሱ ከታሪክ አንጻር ብቻ የቀረበና የወቅቱን ሁኔታ የማይ መለከት መሆኑን መረዳት ያሻል።

### የራሻና የአሪንጎ ጉባኤ

እኒህ ጉባኤያት በዐፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥትና በአቡነ ማርቆስ ዘመነ ጵጵስና /1634–40 ዓ.ም/ በትእዛዝ የተካሄደ ነው፤ ማለትም ከሣስቱ ወገኖች /ተዋሕዶ፣ ጸጋ፣ ቅብዐት/ ማናቸው እውነትን የያዙ መሆኑን ለማረጋገጥ የያውራጃው ሊቃውንት በራሻና በአሪንጎ ላይ ተሰብስበው እንዲከራከሩ ንጉሡ ዐፄ ፋሲልና ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ አዘው ነበር። ይሁንና በጉባኤያቱ ላይ የጳጳሱን ግልጽ አቋም መለየት ባለመቻሉ አቡኑ የሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ጥላቻ አተረፉ። የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስም ፊት ለፊት ተቃወሟቸው። በመጨረሻም በ1640 ዓ.ም ወደ ግብጽ እንዲመለሱ ተደርገው /ግዞት ተልከው የሚሉም አሉ/ በምትካቸው አቡነ ሚካኤል አራተኛ የጵጵስናውን ሥፍራ ይዘዋል። በዘመነ ጵጵስናቸው /1640–60 ዓ.ም/ ሁለት ጊዜ ያህል በተጠቀሱት ሥፍራዎች ጉባኤያት ተካሂደዋል። በጉባኤያቱ ሚናቸው ምን እንደ ነበር የሚጠቁም ምንጭ አልተገኘም። የመጀመሪያው ጉባኤ በዐፄ ፋሲል 22ኛ ዘመነ ንግሥ /1653–54 እ.ኤ.አ/፤ ሁለተኛው ጉባኤ ደግሞ በ33ኛው ዘመነ ንግሥ /1664–65 እ.አ.አ/ እንደ ተካሄደ ይታመናል። የኮፕቶች ዐውደ ጥበብና አንድ ሌላ ምንጭ እንደሚያወሳው ንጉሡ በአባታቸው በዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በኢየሱሳውያን ሚስዮናውያን ተንኮል ተከስቶ በነበረው የሃይማኖት ጦርነት ተረብሾ የነበረውን ሕዝብ ለማረጋጋት ላይ ታች ሲሉ ባልተገኙበት የመጀመሪያው ጉባኤ የቅብዐት ልጆች እንደ ሰደድ እሳት ውስጥ ውስጡን እንደ ተዛመቱ፤ ቅብዐቶች ከተዋሕዶዎች ጋር እንከራከር ቀን ይቀጠርልን ብለው ባመለከቱት፣ ንጉሡ ራሳቸው በተገኙበትና በ1664–65 በአሪንጎ ላይ በተካሄደው ሁለተኛ ጉባኤ ግን ቅብዐቶች እንደ ተረቱ ይገልጻል። /Coptic Encyclopedia, Vol.4.,pp. 1023–1024/፤ /አለቃ አዘዘ ተድላ÷ ነገረ ሃይማኖት /የእጅ ጽሑፍ/።

በአሪንጎ ጉባኤ ከቅባቶች ወገን ዋናው ተከራካሪ ዕውር ዘኢየሱስ የሚባለው ሲሆን የተዋሕዶዎች ወገን ተወካይ ደግሞ አዳም ዘእምፍራዝ ነበር። በመጨረሻም የተዋሕዶዎች ተወካይ አዳም ዘእምፍራዝ አሸነፈና ጉባኤው አበቃ። ይህ ጉባኤ ከአንዳንዶች ዘንድ የታላቁ /ረጅሙ/ ክርክር ውጥን /first phases of the great controversy/ ይባላል።

/ወደ ገጽ 28 ዞሯል/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «እንዲያው ኢትዮጵያዊ ÷ ኢየሩሳሌም ሲሉት ሆዱ እህል አይቀምስም»

ብፁዕ አቡነ አብሳዲ

/ካለፈው የቀጠለ/



*ሐመር፡- ሌሎቹ አይሠሩም እንዴ? አዳዲስ ቤተ ክርስቲያን የሠሩ የሉም እንዴ?*

*ብፁዕ አቡነ አብሳዲ፡-* ብላጤ አይደለ ይሄ ያያችሁት? ከጐልጐታ በ333 እሌኒ ትሠራዋለች:: ሲቃጠል ደግሞ በ614 በፈረንጅ ፐርሺያ ነው የተቃጠለው፤ ፈረስ እንግዲህ በደንብ አልተሠራም ቀስ በቀስ እየሆነ መኖሪያም እያስጠጉ ምን እያደረጉ፤ ቤተ ክርስቲያን በሀገራችን ነው ክብሩ እንጂ እነዚህ ቤተ ክርስቲያን ተጠግተው የማይሠሩበት ነገር የለም:: አሁን እዚያ ጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ወጥ ሠርተው ይበላሉ፣ ሽንት ቤታቸው ከዚያው ከአጠገቡ ነው ያለ:: እዚያ የማይሠሩበት ሥራ የለም:: ቤተ ክርስቲያኑን እንደ ቤት ነው የሚቆጥሩት፤ አይፈሩትም:: የኛ ታቦት አለ፣ እንኳን ካህን ዲያቆን አይቀርበውም:: ግሪክ ታቦት የለውም:: ጣልያኖቹም ታቦት የላቸውም:: በአምሳል÷ በወንጌል ነው የሚያምኑ:: ወንጌል ነው የሚያደርጉበት እንጂ፤ እኛ ነን ኦሪትና ሐዲስ አጣምረን የያዝን እንጂ እነሱ ግድ የላቸውም:: ይሄውሎት እንግዲህ ምኑም ምን የላቸውም::

*ሐመር፡- ስለዚህ በዚህ ምክንያት ነው የኛ የማይሠራው?*

*ብፁዕ አቡነ አብሳዲ፡-* አዎን! እነሱ ጎልጎታ ሲፈርስ እንግሊዝ ኢንጂኒየር አምጥቶ በብረት ጠርቆ ይዞት ነበረ:: በኋላ አርመን፤ ጣልያን፣ ግሪክ ይስማማሉ:: አንዱን ኤሌትሪክ ለማ ሳለፍ ሲፈልግ አያሳልፈውም:: ያ ደግሞ የመጣ እንደሆነ ውኃ ይከለክለዋል:: ምንድር ነው እንደዚህ ያለ ሞኝነት አሉ፤ እግዜር ሲምራቸው ነው ይቅር ሲላቸው፤ አሁን ተሰብስበው ያለበትን እና ሳድስ:: ለመንግሥት ነግረን እናሳድስ እኛ አታሳድሱ ብለናችኋል ወይ? የፈለጋችሁትን አድርጉ አላቸው የጆርዳን መንግሥት:: አምስት ዓመት አፍር ሰው ሠሩ:: አደሱት:: ደኅና አድርገው እንደምታዩት አንድ ነገር የሌለበት የኛን ከሆነ ሰዎች እንጂ እነዚያማ አብረው ተስማምተው እሱን ተላልፈው ሠርተውታል፤ አሳድሰውታል::

*ሐመር፡- ግብፆችስ መሥራት አይችሉም እንዴ?*

*ብፁዕ አቡነ አብሳዲ፡-* አይችሉም! እሱ ለራሳቸው ግብፅ ከእስራኤል ግንኙነቱ ደኅና አይደለም ያለ፤ ስለዚህ ይሄውሎት መንግሥት ነው የሚሠራው::. ያውም የኛንም እኮ መንግሥት ነው የሚያሳድስልን:: እንለምነዋለን፤ የሥራ ሚኒስቴር ይመጣና ሠራተኛ ገምቶ እንዲህ አድርጉ÷ ይህን አታድርጉ አታፍርሱ ይሄ የነበረ ነው:: እንዲዚህ ብለው ጠጋግነን ነው እንጂ ሁሉንም እንዳታስጠርጉ ብለው ነበር:: እንዲያውም መስኮት ያልነበረው ቤት እየሰጠን ነው፤ ከፍተው መስኮት ያወጡልንና በሌሊት ይከፍቱታል:: እንዲህ እያደረጉ ነው የአብዛኛው ቤት አልነበረበትም፤ ብላጥም /ቆሻሻም/ አልነበረም፤ ያ እንጀራ የበላንበትም አባቴ ገ/ማርያም ያ ቡሩክ ሰው እዚያ ቤተ ክርስቲያን አሉ÷ የሳቸው ቤት አለች÷ እሱን አስበልጠነዋል:: መንግሥት እንዳይፈርስ ግን ጠግኑት፤ አፍርሳችሁ መሥራት ግን ክልክል ነው:: ይሄ ነው የሚሉ፤ አሁን እንግዲህ እነ ግብፅ እነ አርመን እነ ግሪክ ወደነሱ እንዳንደርስ በጣም ይገርማችኋል በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፤ አንድ ግሪካዊ አሥመራ ነበረ፤ አንዲት ሐበሻ አግብቶ አንድ ወንድ ይወልዳል:: አገሩ ሲሄድ ይሄን ልጅ ይዞት ሄደ፣ ግን አድጓል ያውቃል፤ ኋላ አድጐ እናቱ መንኩሳ እዚህ ነበረች ይሰማና ሊጠይቃቸው መጣ እዚህ አገር ከአቴና እኛና ግብፅ በዚህ ሚካኤል በር እናልፋለን አታልፉም እንጣላለን:: ስንደባደብ እሱ ጎልጎታ ወዳጅ አለው አንድ ግሪክ መነኩሴ፤ ምንድር ናቸው እነዚህ ሰዎች የሚጣሉት? አልኩት አለ:: አይ ዝምበል እባክህ የነዚህን ነገር ምንድነው ከዚህ ጠብ አለ እንዴ ብለው ሐበሻና ግብፅ ናቸው ምን አጋጥማቸው? እንዲሁ በዚሁ በመኖር የኔ ነው በሚል ተጣልተው:: ታድያ ምን ይመስልሃል አንተ ማነው በደለኛው? በእውነት ለሌላ አይነገርም እንጂ የኢትዮጵያ ነው:: እኛ መጽሐፋቸውን መስቀላቸውን በእናቱ የኛ መሆኑን ስላወቀ እንዲህ አድርገን ወስደነዋል እናቱ አበሻ ስለሆነች አጥብቆ ጠይቆ ወዳጁ ነውና እዚሁ ጌቴሴማኒ እመቤታችን ራይስ ሆኖ ነው ያገኘው ጥሩ ነው ብሎ ወጥቶ እናቱን ሰላም አለና እዚህ መጥቶ:- አባቴ አለኝ ÷ አቤት አልኩት ምንድነው የሚያጣላችሁ? እንደዚህ እንደዚህ ነው ነገርኩት ያለውን፤ ለካስ እውነተኞች ናችሁ÷ ነገረኝ እኮ ይሄ ግሪክ ጓደኛዬ አይነገር እንጂ ዕቃቸውን እኛ ወስደናል ከበሮ ጽናጽል አለኝ፤ ምን ያድርጋችኋል መልሱ ብለው አይ ጊዜ አለን የኛ ንጉሥ ይነግሥና የዚያን ጊዜ በኛ ሃይማኖት አንድ ሲሆኑ ነው የምንመልስላቸው እንጂ ዛሬማ የነሱ የኮፕቶች ሃይማኖት አይደለ ሃይማኖት የላቸውም የግብፅ ሃይማኖት ሃይማኖት አይበልም አለኝ ብሎ ነገረኝ:: ያ ሰውዬ ጥቂት ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ እንዲሉ አጫወተኝ::

ደግሞ አንድ ሰውዬ! አባ ኃይሌ ይሏቸዋል፤ የሐይቅ መምህር አሸከር ነበሩ ውኃ አጠጪ ይዘዋቸው መጡ ሊሳለሙ ብለው ታዲያ ከዚህ የነበሩ መነኮሳት አንተ ገና የአገራችን ሰው ባርያ እየገዛ ያስከትላል ይሏቸዋል:: ከዚህ ነጻ አይደሉ ታድያ ምንድን ነህ? አሽከር ነኝ የት ነህ? ተዘርፌ መጥቼ እኔ እህቴን ግን መምህሩ ደግ ናቸው



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እህቴ ስትዳረስ ድረዋታል እኔ ግን ከሳቸው ዘንድ አሽከር ነኝ:: እዚህ ብናስቀርህ ትወዳለህ? ብለዋቸዋል ደስ ይለኛል በል እሺ ግድየለም ብለው የባቡር መሄጃ አለ እዚህ ወደ ቤተ ልሔም ከዚያ ሲደርሱ አንተ ያ ልጅ ከዚህ አስቀምጠው ብለው ከዚያኛ ደረጃ ሄደው ተቀምጠዋል:: ገና ሳይነሣ ናውጣ ብለው አውጥተውታል:: እኒህን ሰውዬ ወጣት ናቸው ትንሽ ናቸው፤ መነኮሳቱ ከመምህሩ ነጥለው ተሳልመው ሲመለሱ አስቀርተው ወስደው ከዚያ ገዳም ይሸሽጉታል::

እዚህ ማረስ የሚባል የግሪክ ገዳም የኛን ገንዘብ ይወስዱት ዘንድ እና እዚያ ቋንቋቸውን ለምደው ሲወጡ፣ ሲገቡ፣ ሲላላኩ ምን ምን ሲሉ የኢትዮጵያ መስቀል አየሁ አሉ:: እንዴ ጌታዬ አልኩት አሉ÷ በግሪክኛ አቤት ይሄ መስቀላችሁ የኛ መስቀል ይመስላል አልኩት ኸ! ምናልክ አንተ? መቼ አየኸው? በዚህ ሰዓት:: በነጋታው ለአንድ የግሪክ ቄስ አንጠልጥሎ አምጥቶ እንካ ወሮ አናስለቅመውም ብሎ ጥሎኝ ሄደ አሉ፤ እዚያ ደግሞ እሱ ተቀብሎ እንዲ'ያ እንዲያ ሲል የሐበሻ መነኮሳት መጥ ተው ከነዚህ ምን ትሠራለህ ወደኛ ገዳም አስገቡኝ በዓይኔ አይቼዋለሁ እኔም ብሆን ብለው አጫወቱኝ:: ሸምግለው ነው እኔ ያገኘኋቸው ሁለት ሦስት ጊዜ በጅቡቲ በኩል ተመላልሰው መቁጠሪያ የዮርዳኖስ ጠበል እየያዙ አዲስ አበባ ይሄዱ ነበር:: ታድያ ሸምግለው አግኝቻቸው አባቴ ኃይሌ ይኋቸዋል:: ታድያ እንዲህ አድርገው ንገሩን እሳቸውም ቢሆኑ አሁን አርመን ግሪክ የሚጠሉን የወሰድነውን አምጡ ሊሉን አይደለ ብለው ነው እንጂ እኛ በዚህ ቅዱስ ቦታ በጣም ቀዳማውያን ነን በሐዲስ ሳይሆን ከኦሪት ጀመረን እስኪ እግዜር ያሳያችሁ፤ በ4450 ንግሥት መጥታ ከሰሎሞን ተገናኝታ የእግዚአብሔርን ነገር ተረድታ ይሄ ሁሉ ያሰበችው ተነግሮላታል::

በክብር መምጣቷ በጉልህ ተጽፏል:: እነዚህ ርጉማን ናቸውና ብዙ ብዙ ነገር ነበር፤ የነበረ አስተካክላ ተነጋግራ ብሰሉ ስንት እስራኤል ከሆነ ጊዜ ነው ቤተ መቅደስ የምትሄዱ ብለው ጠየቋት፤ እኛ በዓመት ሦስት ጊዜ ልጆቻችንን ይዘን መሳም አለብን አሉ:: እንግዲህ እኔ ከዚህ ለኢትዮጵያ ሦስተ ዓመት ቅርብ ነው ከሆነ ልሞክር ነኝ አለዚያ ደግሞ ከሱ ረዘመ ያለ ሦስት ዓመት ተኩል በየዓመት እጅ መንሻ ለመላክ እችላለሁ ብላ ታመላልስ ነበረች:: ከዚያ እስከ ዳዊት አንድ ሺ ዓመት እንበለው ይህንን ነገር ያንን ሰውዬ መጥቶ ከዚች ከህንደኬ የሚኋት ከዚህ ከሱዳን ክፍል ነበረች አሉ:: ኑቢያ የሚባል አገር አለ፤ ጥቋቁሮች የነበሩ ኢትዮጵያውያን ታሪክም ይናገርላቸዋል:: ኋላ እስላም ወርሷቸው ነው እንጂ ከዚያ ንግሥቷ ነበረች፤ እንደ ተለመደው መጣ ይሄ ሰውዬ ተሳልሞ ወደ ጋዛ ወረደ ሲሄድ መንፈስ ቅዱስ ተከተለው አለው ለፊልጶስ ሄደ በመጽሐፍ እንደምታውቂት ነው እንግዲህ አጠመቀው፤ በዚያ ይዞ ነው አላቋረጥንም ሲጠፉ ይጠፋል ሲመለስ ይመለሳል ባገራችን መንግሥት ካለ ባገራችን መንግሥት ይነግሣል መንግሥት ይጠፋል ነው እንዲያው አገር ይጠፋል አገር ይቀናል በዚህ ዓይነት ተጠምቆ ሄደ ከዚህ በኋላ ካህናት መነኮሳት ወረሱት መንግሥት ነገር ቀረ::

*ሐመር፡- ከመቼ ጀምሮ ነው መነኮሳት ወደዚህ መምጣት የጀመሩት?*

*ብፁዕ አቡነ አብሳዲ፡-* መቼስ ከ350 የሚሉ አሉ ዋናው በታሪክ ተጽፎ የሚገኝ ግን ከ400 አድርገውታል እንጂ ከ350 አለ ግን ይጣላል:: አሁን የኛ ክርስትና ከ400 የሚሉ አሉ የጀመረው የለም ከ300 ነው የጀመረው የሚሉ አሉ:: ታሪኩ ብዙ ስለሆነ የነገሩን ሁኔታ አይቶ ብቻ እንደሚሆን ነገር አድርጎ መሄድ ነው እንጂ አይስተካከልም በሀገራችን ደግሞ ዓመተ ምሕረት የሚባል እንዲህ ብሎ በመጻሕፍት ጽፎ ፀሐይ የመሰለ ይህን ስለመሳሰለ ነገር ትምህርት አናደርግበትም እና እንግዲህ እንደሚያውቁት ጀመሩ:: በ400 ጉልህ ሆኖ ነው÷ ታወቀ:: ያችን ቦታ ጌታ የተሰቀለበትን ድሮ ለንግሥት ማረፊያ ነው ተብሎ የተሰጠን ይሄውሎት ይህ አሁን ያለንበት ምሥራቅ ያያችሁት ቀድሞ የነበረ ነው፤ ጌታ የተሰቀለበት ጎልጎታ::

ከኑቢያ ጀምረን በምሥራቅ አፍሪካ ምን እኛ ነበርን ከጌታ ልደት በፊት ምስር ራሱ አሽአሎጂ የፈረንሳይ መጥቶ በላዕላይ ግብፅ አሥራ ስምንት ኢትዮጵያውያን ምስርን ገዝተውታል:: ገና አረማውያን ሳሉ ነው እንግዲህ በጣም አገራችን የታወቀ፤ በወዲያ ቀይ ባሕር ነው በወዲያ በኩል ሶማሊያን ይዞ ውቅያኖስ ነው ማዳጋካስካር ነው ይህንን ሁሉ የኢትዮጵያ የነበረ ነው:: ደኅና አድርጎ ነው በጉልህ የተጻፈ:: አሁን ሱዳን በጐንደር አድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመን ድረስ በየዓመቱ እየመጡ ግብር ይሰጡ ነበር:: እምቢ ያለ እንደሆነ እየሄዱ ያስገብሩታል፤ የከዳ እንደሆነ ለወንድሙ ይሰጡታል:: ይህን ለማድረግ የዓመት የሁለት ዓመት መንገድ ነበር የሚያደርጉት ባላባቱ ነበር የሚሾመው:: ገብር ይሉታል ይገብራል:: እምቢ ያሉ እንደሆነ ሄደው ያስተካክሉታል:: ለአንዱ የነፋው ለአንዱ እያሉ ትልቅ መንግሥት ነበረን ይሄ ቅኝ ሀገር የሚባል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ያውሎት ይሄ ኬንያ ÷ዐጋንዳ ታንዛኒያ የለውም ነበር:: ድንበር አሁን እኮ ፈረንጆች ተካፍለው አፍሪካን÷ ጣሊያን ፈረንሳይ እንግሊዝ ሆነው ያውሎት ደግሞ በወዲያ በበርበራ በሞቃዲሾ ጣልያን በጅቡቲ ፈረንሳይ በሞላ ያዙ:: በሱዳን ደግሞ እንግሊዝ መጣ፤ ሱዳንን ወስዶ ከምስር ጨመረው፤ ሱዳን አይባልም ነበር:: ፊት ምድሩ ምስር ነው የጥንት ስማቸው ማሕዲ ወይም ባዲ ይባል ነበር:: ከጥንቱ ሱዳን ማለት ጥቁር ማለት ነው፤ ምስሮች ያወጡት ስም ነው::

ይሄንን ኬንያን ሁሉ ይዘው እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ማንም አልነበረም፤ እየራሱ ቀስ በቀስ ወደቀ:: ነቢዩ ኤርምያስ ለቤተ እስራኤል አልቅሶላታል:: ለሀገራችን ደግሞ እንደሷ የሚለቀስላት ሀገር ናት:: ይኸን ሁላ ይዛ የነበረች ሀገር አሁንማ በጣም በጣም የሚያሳዝን ነገር እኔ ሳስበው ደግሞ እኔ በእውነት ወንድሞቼ ያለኝ የሀገር ፍቅር ለእናት ለአባቶቼ እንኳን የለኝም:: ታድያ እዚያ ደርሼ ተሳልሜ አልመጣም ወይ በሚል ነው እንጂ ይሄ ሁሉ አገኛለሁ ብዬ አላሰብኩትም ነበር:: ግን ቅናት ያዘኝ:: ኋላማ በጣም የሚገርማችሁ ነገር ግብፆች ሶርያውያንና ግሪኮች የኛ እንዴት እንደ ወሰዱት ሳውቀው በጣም ቃጠሎ አሳደረብኝ:: እንግዲህ እግዜር አለ÷ እንግዲህ ለፈጣሪ ወይ ግደለኝ ወይ እንደ ጣና ያሉ ደሴቶች ቤተ ክርስቲያን አሉ በዚያ ሂጄ ጭቅጭቅ የሌለበት ምንኩስናውም ቢሆን እንዲያው በእውነት ቢያዩት አያስፈልግም÷ እንዲሁ ነው እኮ ÷ ምን ኩስናው ያለው መሬት ይዞ ነገሥታቱም ተሳስተው ነው እንጂ መሬት አለመስጠት ነበረ::

አንዳንድ ነገር ሲሰጧት አርሰው እንዲበሉ፣ ቆፍረው እንዲበሉ፣ ዳባ እንዲለብሉ ነበር እንጂ ሄዱ ነገሥታት አድርገዋቸው ቁጭ አሉ:: ይፈርዱ ይሰቅሉ ጀመሩ:: ላዩ ቆብ ነው፤ ሥራው የዓለም ነው የባሰ ነገር መጥቶ አዋረደው እንጂ ትክክል አልነበረም እንዴ:: መነኩሴ ማለት ከዋልድባ እንዳይወጣ ከማኅበረ ሥላሴ እንዳይወጣ እዚያ ቁጭ ብሎ ለነፍስ መለመን ነበር እንጂ::

እግዜር ያሳዮት÷ ጉድ ነው÷ ትክክል አልነበረም:: አሁን ጣ፴ መጣና ወሰደ ወሰደ ተባለ:: አርሶ አያርስ ወይም በገዳም አይቀመጥ እየተነሣ ወደ ከተማ:: ታድያ እንግዲህ ምንድን ነው? ትክክል አይደለም ብንመለከተው ምንኩስና ከሆነ ከገዳሙ ሳይወጣ ደኻ ምስኪን መሆን፤ ሰውነቱን አድክሞ ፍቅርና ሰላም ይዞ ስለ ሀገር ምህላ ማድረግ ነበር:: ሥራችን ይሄ ነበር ካህናት የግድ በዓለም ነው ያሉ በእውነት እንግዲህ እነሱም ቢሆን በዓለም ላይ ትዳራቸውን ይዘው በእውነት ቢያቃኑ ቢሠሩና ቢቀመጡ ይህ ሁሉ አይጠፋም ነበር:: በእውነቱ የምንኩስና ሥራ ከገዳም አለመውጣት ከሁከት ከጭቅጭቅ አለመግባት ማስታረቅ መጸለይ ነበረ::

/ይቆየን/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የዘመን መለወጫ በዓል

የዘመን መለወጫ በዓል የታወቀው ሦስት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛ እስራኤል በብሉይ ኪዳን ያከብሩት የነበረው ሚያዝያ 1 ቀን፣ ሁለተኛ የዓለም ክርስቲያን የክርስቶስን ልደት ተቀዳሚ በማድረግ የሚያከብሩት ጥር 1 ቀን፣ ሦስተኛ ኢትዮጵያ ጥንተ መሠረትነቱን ዐውቃ የምታከብረው መስከረም 1 ቀን ነው፡፡ እስራኤል የዘመን መለወጫ በዓልን በሚያዝያ ማድረጋቸው፣ በዚሁ ወር ከግብፅ ባርነት ነጻ ስለ ወጡና እግዚአብሔር ይህንን የነጻነት በዓል በየዓመቱ እንዲያከብሩት ስለ አዘዛቸው ነው፡፡ የዓለም ክርስቲያን ጥር 1 ቀን ማክበራቸው የክርስቶስን ልደት ምክንያት በማድረግ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡

ኢትዮጵያ መስከረም 1 ቀን የምታከብረውን የዘመን መለወጫ የተቀበለችው ከካም ነው፡፡ የተጀመረበትም ካምና ልጁ ኩሳ ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት፣አክሱም በኩሳ ስም የተመሠረተችበት ጊዜ ነው፡፡ ዘመኑም በኢትዮጵያ ላይ ከ4900 በላይ ሲኾን፣ ከጥፋት ውኃ በኋላ በኖኅ ዕድሜ 601 ጀምሮ ሲከበር 5552 ዓመት አሳልፎ እነሆ ደርሰንበታል፡፡ ኖኅም ሲያከብረው ጥንቱን ዓለም የተፈጠረበት ወር እንደ መኾኑ መጠን፤ ከአዳም ጀምሮ የወረደ፣ በአበው እየተላለፈ እስከ እርሱ የደረሰ እንደ መኾኑና ኋላም የቀላይ አፎች የተከፈቱበት፤ የጥፋት ውኃ መጉደል የተጀመረበት ለመጀመሪያ ጊዜ ከጥፋት ውኃ ወዲህ ክረምትና በጋ መፈራረቅ የጀመሩበት ምድር የፍሬ ጽንስ የአበባ መልክ ያሳየችበት ስለ ኾነ ነው፡፡

የፊተኛው ሲጨመር 7452 /አሁን 7496 ዓመት/ ዘመኖችን ማሳለፉ ነው፡፡ ስሙም በግእዝ ርእሰ ዐውደ ዓመት፤ በአማርኛ የዘመን መለወጫ ዕንቁጣጣሽ፣ ቅዱስ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል፡፡ ርእሰ ዐውደ ዓመት ማለት የዘመን መለወጫ መጀመሪያ፤ ዕንቁጣጣሽ ማለት፤ ዕንቁ -ዕፅ -አወጣሽ ብሎ የአበባውን መፈንዳት ወይም ዕንቁ -ዕጣ -ወጣሽ ብሎ መልካሚቱ ምድር ኢትዮጵያ በዕጣ ለካም መድረሷን የሚያመለክት፣ ቅዱስ ዮሐንስ ማለት በዓሉ ከመጥምቁ ዮሐንስ ዕረፍት ጋራ የተደጋገፈ መኾኑን የሚገልጥ ነው፡፡

በዕብራውያን ቁጥር በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር መስከረም 1 ቀን የነበረው ጥቅምትን ይነካል፡፡ እግዚአብሔርም በሰባተኛው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ለእግዚአብሔር የተቀደሰች በዓል አድርጉ፤ በዓሉም ተዝካረ /በዓለ/ መጥቅዕ ይባላል ሲል ሙሴን ያዘዘው ስለዚሁ ነው፡፡ ይህም በዓል ለዓመት ጥንት እንደ መኾኑ መጠን የአውራኃም ጥንታቸው ነውና በዓመት ወሮች በመጀመሪያ በመጀመሪያ ቀን ይከበራል፡፡ ምክንያቱም፤ ለወር ለዓመት ጥንት መጀመሪያ ስለ ኾነ ነው፡፡ በዓለ መጥቅዕ÷ ተዝካረ መጥቅዕ መባሉም መጥቅዕ /ደወል/ በተደወለ ጊዜ ኹሉን እንዲሰበስብ፤ ይህም ልዑል እግዚአብሔር የሐልዮ፣ የነቢብ ቃሉን ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ዕለትን፣ ሰዓትን፣ ወርንና ዓመትን ሰብስቦ የሚያስገኝ ስለ ኾነ ነው፡፡ ስለ አቆጣጠሩ ፊትና ኋላ መሆን ግን ጌታችን የተሰቀለበት፣ አይሁድ ሚያዝያ 14 ቀን ያከበሩት የፋሲካ በዓል በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር መጋቢት 27 ቀን እንደ ኾነ መመልከት ብቻ ሊያስረዳን ይችላል፡፡ /ዘሌ.23÷23-24/፡፡

አባቶቻችን ጥንተ ፍጥረትን መጋቢት፤ ጥንተ ቀመርን ሚያዝያ ሲያደርጉ ስምተናል፤ ማስረጃም ያደረጉት ቃል፣ እግዚአብሔር ሚያዝያ የወሮች መጀመሪያ ይሁናችሁ ያለውን ነው፡፡ እግዚአብሔር ሚያዝያ የወሮች መጀመሪያ ይሁናችሁ ብሎ ሲያዝዝ፣ ምክንያቱ ለጊዜው እስራኤል ከግብፅ ስለ ወጡበት፤ ኋላም የሰው ልጆች ከሲኦል ስለ ወጡበት፤ እንደ ሆነ ግልጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚያዝያ ወር ለእስራኤል የወሮች መጀመሪያ እንዲኾን ሲያዝዝ፣ ለእስራኤል የነጻነት መጀመሪያቸው በመኾኑ እንጂ፣ ጥንተ ፍጥረት በመኾኑ አይደለም፡፡ ይህስ ባይኾን ቀዳማዊውን ቀዳማዊ ባላለው ነበር፣ ስለ በዓልም ሚያዝያ በገባ በ14 ቀን በዓለ ፋሲካን አክብሩ ብሎ በዓለ መጥቅዕን ሠርቀ ወርኃ /መባቻ/ በጥቅምት እንዲያከብሩ ባላዘዛቸውም ነበር፡፡/ዘጸ.14÷2/፡፡

እግዚአብሔር የፋሲካን በዓል እስራኤል በሚያዝያ እንዲያከብሩ ሲያዝዛቸው የመባቻን በዓል ደግሞ በሰባተኛው ወር መጀመሪያ እንዲያከብሩ ይኸውም በዓለ መጥቅዕን ለፍጡራን ያይደለ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ በዓል መኾኑን ዐውቀው እንዲጠብቁት በማዘዙ፤ ጥንተ ፍጥረት፣ ጥንተ ወር፣ ጥንተ ዓመት ያው በዕብራውያን አቆጣጠር ጥቅምት፣ በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ግን መስከረም ተብሎ የሚጠራው መኾኑ ግልጥ ነው፡፡ ሚያዝያ ቀዳማዊ በኾነስ ኖሮ የመባቻን በዓል ሚያዝያ 1 ቀን፣ ፋሲካንም በ14ኛው ቀን አክብሩ በማለት ፈንታ ከሚያዝያ ሌላ ወር ባልሰጠውም ነበር፡፡

መስከረም ማለትም እግዚአብሔር ከዚህ እስከ ብሩህ ሰማይ ድረስ መልቶ የነበረውን ውኃ ከሦስት ከፍሎ፤ በጠፈር፣ በሐኖስ፣ በውቅያኖስ ከወሰነ በኋላ፤ ደረቁ ይገለጥ ባለ ጊዜ፤ ምድር ገበሬ አርሶ አለስልሶ እንዳከረማት ኹሉ ለዘር የተመቸች ኾና ተገኝታ ነበርና መሐሰ ቆፈረ፣ ከረመ÷ ከረመ የሚሉትን ኹለቱን ግሶች በማቀነባበርና በማስተባበር መስከረም አጥብቆ ታርሶ ከረመ እንደ ማለት ስሙን ከግብሩ ነሥቶ የሚጠራበት ነው፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም አታሚን አታኒም የተባለውን ቃል ሲተረጉሙ አታን ወይም ኤታን ማለት ጥንተ ፍጥረት እንደ ኾነ ዕብራይስጢውን በማዋሐድ ገልጠው ይኸውም በዕብራውያን ሰባተኛው ወር ጥቅምት በኢትዮጵያውያን በፀሐይ አቆጣጠርና በአቡሻኽር ጠንቃቃ ቁጥር ግን መስከረም መኾኑን አስረድተዋል፡፡ /የግእዝ መዝገበ ቃላት÷ ገጽ 249/፡፡

ኢትዮጵያ በአክሱም መዲናነት የተቀበለችውና ስታከብረው የምትኖረው መስከረም 1 ቀን የሚውለው ርእሰ ዐውደ ዓመቷ የኩሽ÷ ኩሳ መዲናና መቃብር በመኾኗ፣ አኵሱም ርእሰ አህጉረ ኩሺ /ኩሳ/ እሞን ለአህጉረ ኩሺ /ኩሳ/ ተብላ የምትጠራውን አኵስምን /አኩሺምን/ ያኽል ጥንታዊነቷን ሲመሰክር የሚኖር ነው፡፡

በዓመተ ዓለም÷ በዓመተ ኩነኔ፣ በዓመተ ምሕረት ደምራ፣ ዘርዝራ፣ ዐጥፋ፣ ነጥላ፣ ጠቅልላ ከፍላ የምትሰጠው የዘመን ቁጥርም የጥንትነቷ ፍሬ ነው፡፡ መስከረም 1 ቀን በዓል ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ለክብራችን፣ ለታሪካችን ጥንት መሠረት ነውና ዐውቀን እንጠቀምበት፡፡ /ኩፋ.7÷19-30/፡፡

*ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ÷*
*የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት÷*
*አዲስ አበባ÷ ገጽ 233- 235፡፡*

## ቅዱስ ዮሐንስ

ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ፡- ካህን፣ ነቢይና ሰማዕት ነው፡፡ ቅዱስ ወንጌል የወንድሙን ሚስት ሄሮድያዳን በማግባቱ ዮሐንስ ተቃወመው ይላል፡፡ /ማር. 6÷1-14/፡፡ በገጸ ንባቡ ፊልጶስ ስለ ሞተ በአይሁድ ሕግ መሠረት የወንድሙን ሚስት በመውረሱ የተቃወመው መስሎ ይነበባል፡፡ ነገር ግን የሄሮድያዳ ባል÷ የሄሮድስ ወንድም ፊልጶስ÷ በሕይወት እያለ ንጉሡ ሄሮድስ ሚስቱን ስለ ቀማው ነው፡፡ ፊተኛው ሄሮድስ የገሊላንና የናዝሬትን ሕፃናት ሲፈጅ እመቤታችን ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብፅ በተሰደደች ጊዜ የካህኑ ዘካርያስ ሚስት ኤልሳቤጥ በእርጅና ዘመኗ የወለደችው ዮሐንስ እንዳ ይገደልባት እጅግ ተጨነቀች፡፡ ሕፃኑን ዮሐንስንም ይዛ ካህኑ ዘካርያስ ካለበት ቤተ መቅደስ ሄደችና «የዚህን የውድ ልጄን ሕይወት ለማትረፍ የት ልድረስ?» ስትል ዘካርያስን አማከረችው፡፡ ዘካርያስም «አንተ ሕፃን የልዑል ነቢይ ትባላለህ . . .» ብሎ ትንቢት የተናገረለትን ልጁን ከናቱ ከኤልሳቤጥ እቅፍ ተቀብሎ ሳመውና «ወደ ሲናይ በረሃ ሽሺ እሱን ፈልገው ሲመጡ በምትኩ እኔን ይገድሉኛል» አላት፡፡ እንደ ቃሉም የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ አባት፣ ካህንና ነቢይ ዘካርያስ ሰማዕትነት መስከረም ስምንት ቀን ተፈጸመ፡፡ ኤልሳቤጥ ብቻዋን ለዕለት የሚቀመስ ምንም ነገር ሳይኖራት ልጇ ዮሐንስን ይዛ ወደ ሲናይ በረሃ ገሠገሠች፡፡ ኤልሳቤጥ ከዮሐንስ ጋር ለአምስት ዓመት ያህል በበረሃ ኑራ መስከረም ሰባት ቀን ዐረፈች፡፡ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ዮሐንስ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» እያለ ማስተማር እስከ ጀመረበት ድረስ በምድረ በዳ ኖረ፡፡ ዮሐንስ አንገቱን መስከረም ሁለት ቀን በተቆረጠ ጊዜ የዮሐንስ ራስ በመጀመሪያ ወደ ሄሮድስ ቀጥሎ ወደ ሄሮድያዳ ቤት ተወሰደች፡፡ ዐይኖቹ ግን እያበሩ ፊቱም ከመልካም መዓዛ ጋር ነበር፡፡ ከሄሮድያዳም ቤት ጠጉሯ እንደ ክንፍ ሆነላትና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለበት ደብረ ዘይት ሂዳ ሰገደች፡፡ ጌታችንም ክንፍ አውጥታ እየበረረች የሄሮድስንም ኃጢአት እያጋለጠች እስከ አሥራ አምስት ዓመት ድረስ እንድታስተምር አዘዛት፡፡ እርሷም ከአገር አገር እየዞረች ለ15 ዓመታት ያህል ስታስተምር ኖራ በጢባርዮስ ቄሣር ዘመነ መንግሥት ሚያዝያ 15 ቀን ዐረፈች፡፡ ሄሮድያዳም እስከ አንገቷ ያለውን አካሏን ወደ ምድር ሰጥሞ ዕመቅ ዕመቃት ወረደ፡፡ ከአንገቷ በላይ ያለውንና በመሬት ላይ የተተከለውን ራሷንም ሄሮድስ በሰይፍ አስመታው፡፡ ልጅዋም ዐብዳ ስታውክ በሰይፍ መታት፡፡

*ምንጭ፡- የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ታሪክና ሰማዕትነት*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የደቡብ ኦሞ አባቶች ተስፋ እውን ሲሆን

የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ከአዲስ አበባ 705 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በጂንካ ከተማ ይገኛል:: ሀገረ ስብከቱ የሚገኝበት የደቡብ ኦሞ ዞን ካሉት ስድስት ወረዳዎች አራቱ ቆላማ የአየር ንብረት ያላቸውና ሕዝቡም በከብት ርባታ የሚተዳደር ነው:: በሀገረ ስብከቱ በአጠቃላይ ሃያ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም አብዛኛው ሕዝብ ግን አርብቶ አደር በመሆኑ በአንድ ቦታ ተወስኖ የማይኖርና የወንጌል ትምህርት በአግባቡ ያልተሰበከለት በተለይም በቆላው አካባቢ አብያተ ክርስቲያናት ያልተቋቋሙበት ሲሆን ከክርስትናው እምነት ይልቅ በባዕድ አምልኮ የተጠመደ ነው::

ካህናት አገልጋዮችና ሰባክያነ ወንጌልን ከተለያየ ቦታ በማምጣት ችግሩን መቅረፍ እንደማይቻል ያዩ ብፁዓን አባቶች በሀገረ ስብከቱ አንድ የካህናት ማሠልጠኛ ማቋቋም፣ የአካባቢውም ምእመናን ልጆቻቸውን በተቋሙ እንዲያስተምሩና ዲያቆናትን፣ ቀሳውስትንና ጳጳሳትን ማፍራት፣ ወንጌል ያልተሰበከለትን ሕዝብ አስተምሮ ማጥመቅና የቤተ ክርስቲያን ልጅ ማድረግ ምኞታቸውና ተስፋቸውም ነበር:: በ1984 ዓ.ም የነበሩት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቶማስ «እዚህ አካባቢ ያሉትን ስመለከት ያሳዝኑኛል:: ሀገሩ ግን ቅዱሳን ያሉበትና የእግዚአብሔር ጸጋ የበዛበት ነው:: ለወደፊት አንድ ትልቅ መንፈሳዊ ተቋም አሠርተን እንኳን ዲያቆን ቄስና ጳጳስ እንዲወጣ እናደርጋለን» በማለት ምእመኑን ያበረታቱ ነበር::

እግዚአብሔር ፈቃዱ ሲሆን የብፁዓን አባቶቻችን ተስፋ እውን ሆኖ ጸሎታቸውና ምኞታቸው ተሳክቶ ሕዝቡን ያልተወ አምላክ ጥር 27 ቀን 1992 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ በወቅቱ በነበሩት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሉቃስ አማካይነት በአካባቢው ምእመን የተጠቆመውን ቦታ ባርከው የአንቀጸ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ ተቋም በሚል ተሰይሞ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ:: በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ጥረትና በምእመኑ ጠንካራ ተሳትፎ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ፣ ለተማሪዎች መኖሪያ ስድስት ክፍል ቤት፣ የማብሰያ፣ የመመገቢያና ያመጸዳጃ ቤት ተሠርቶ ግንቦት 24 ቀን 1995 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ የወላይታ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ ስምዖን የአሶሳ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ እንዲሁም የየዶ ብሩ አስተዳዳሪዎችና ብዛት ያላቸው ምእመናን በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ የምረቃው በዓል ተከብሮ ውሏል:: በተለይ በገዳሙ ዙሪያ ያሉ ምእመናን ታቦተ ሕጉ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ለሰባት ቀናት በገዳሙ ግቢ በማደር እግዚአብሔ ርን እያመሰገኑ ደስታቸውን ሲገልጹ ሰንብተዋል::

ቀደም ብሎ በቦታው ላይ በነበረ የዋርካ ዛፍ የአካባቢው ሕዝብ የባዕድ አምልኮ ሲፈጽምበት የቆየ ሲሆን ለገዳምነት ከተባረከ ወዲህ ግን የስብከት ኬላ በማቋቋምና ቃለ እግዚአብሔር በማስተማር በተለይ በዙሪያው ያሉትን የአሪ ብሔረሰብ በማጥመቅ ከ150 በላይ የሚሆኑትን ክርስትና በማንሣት ለገዳሙ ምሥረታ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ሆኗል:: ፦አብራካቸው ክፋይ የሆኑ ልጆቻቸው ወላጆቻቸውን ወደ ክርስትና እምነት ለማምጣት ብዙ አስቸጋሪ ፈተናዎች ቢገጥሟቸውም በጻድቁ ርዳታ ዛሬ ገና በጅምር የሚንቀሳቀሰው ገዳም ከ60 በላይ የሚሆኑ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችንና ወደ 20 የሚጠጉ የአካባቢውን ነዋሪዎች በጽዋ ማኅበር ተሰባስበው በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

በገዳሙ የተቋቋመው የካህናት ማሠልጠኛም በሀገረ ስብከቱ ካሉት ወረዳ ቤተ ክህነትና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የአካባቢውን ልጆች በመምረጥ የግብረ ዲቁና ትምህርት ለመስጠት በመዘጋጀት ላይ ነው:: በአሁኑ ሰዓትም ከማሊ፣ ከሐመር፣ ከገታመር፣ ከውብሐመር የተውጣጡ ስምንት ተማሪዎችን የንባብና የውዳሴ ማርያም ትምህርት እየተማሩ ሲሆን ቀሪዎቹ ተማሪዎች በቅርቡ እንደሚገቡ ይጠበቃል:: በሀገረ ስብከቱ ይህ ተቋም መከፈቱ በአገልጋይ እጦት ምክንያት የተዘጉትን አብያተ ክርስቲያናት ለማስከፈትና ወንጌል በአግባቡ ያልተሰበከለትን የከብት አርቢ ነዋሪ በማስተማር ክርስትናን እንዲቀበሉ ማድ ረግ በመሆኑ ለዚህ ገዳምና መንፈሳዊ ት/ቤት ማደግና የበለጠ መስፋፋት ምእመኑ በገንዘቡ፣ በጉልበቱ በዕውቀቱና በአሳቡ የሚጠበቅበትን ድጋፍ እየሰጠ ከጐኑ መሰለፍ እንዳለበት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ አሳስበዋል:: እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤቱ በማስገባት የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ተረካቢ ትውልድ ማፍራት እንዳለባቸው ገልጸዋል::

በማኅበረ ቅዱሳን የሞያ አገልግሎትና ተራድኦ ክፍልም ገዳሙና ት/ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ ለልማት አመቺ በመሆኑ ተማሪዎቹ ከትምህርቱ ጐን ለጐን የልማት ሥራውን እያከናወኑ ራሳቸውን እንዲችሉ የተለያዩ የልማት ሥራዎች ፕሮጀክት አዘጋጅቶ ለበጐ አድራጊዎች በማቅረብ የበረከቱ ተካፋይ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ይገኛል::

በማኅበረ ቅዱሳን የገዳማት፣አድባራትና አብነት ት/ቤቶች መርጃና ማቋቋሚያ ንዑስ ክፍል::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር::*

## ነገር ሁሉ ...

*/ከገጽ ፴፫ የዞረ/*

/ከገጽ ፴፫ የዞረ/

ቀር ፣...ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ማለት አይቻልም: ሶምሶን በብ ሥራተ መልአክ ተወለደ:: ከደሊላ ጋር መጥፎ ጓደኛነትን ፈጠረ:: በስተ መጨረሻም ኃያል የመሆኑ ምስጢር በምኑ እንደሆነ አወጣጣችው:: ፀጉሩን ላጨችው:: ጸጋ እግዚአብሔር ተለየው:: በስተ መጨረሻ ፍልስጥ ኤማውያን ሁለት ዓይኑን በጉጠት አውጥተው እህል ፈጪ አደረጉት:: ይሄ ለበጎ አይደለም:: መሳ. 15÷1–22:: የዝያን ንጉሥ ሥል ጣነ ክህነት ሳይኖረው በድፍረት የካህናትን ሥራ ሊሠራ ተዳፈረ:: እግዚአብሔርም በለምጽ መታው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በጻፈው መልእክቱ ከእነርሱ መካከል አንዳንዶች ሳይገባቸው ማለት ሳያምኑበት ራሳቸውን ለመምህረ ንስሓቸው ሳያስ መረምሩና ቀኖናቸውን ሳይፈጽሙ ከቅዱስ ቁርባን በመቀበላቸው እንደ ታመሙና እንዳንቀላፉ /እንደ ሞቱ/ ነው:: ይህም ለበጎ አይደለም:: 1ቆሮ.11÷27–32::

ይሁንና ከላይ እንደ ተጠቀሰው አንድ ምእመን በመከራና በችግር በተያዘ ጊዜ በመከራው ሳይናወጽ ተስፋም ሳይቆርጥ በበጎ ምግባሩ በሃይማኖቱ ቢጸና ወይም ከኃጢአቱ ቢመለስና ንስሐ ቢገባ መከራውንም በጸጋ ቢቀበልና ነገር ሁሉ ለበጎ ሊደረግለት እንዲችል ማመን ይኖርበታል:: በርግጥ ችግሮች በተከሰቱበት ሰዓት ዋጋቸው ስለማይታይ ለበጎ ነው ብሎ ማለቱ ሊከብድ ይችላል:: ችግሩ በተፈጸመበትና በተከሰተበት ወቅት ነገሮች ሁሉ ጨልመው ቢታዩ በሕይወተ ሥጋ ሳለን አንድ ቀን ወይም በወዲያኛው ዓለም የዛሬውን ሁኔታ ለበጎ እንዲሆን አስበን የሚጠበቅብንን ከተወጣን ለበጎ ሊሆንልን ይችላል:: የዮሴፍ መሸጥ ለበጎ መሆኑ የታወቀው ከብዙ ዓመታት በኋላ በምድር ላይ ረሃብ መጥቶ የአባቱ ቤተሰብ በስደት ወደ ግብፅ በገባ ጊዜ ነው:: ኦ.ዘፍ ጥ.47 እና 48::

በመሆኑም በሃይማኖት ጸንተን የሚጠበቅብንን በመወጣት በሕይወታችንም ውስጥ ስለሚሆ ነውና ስለ ሆነው ነገር በመጽናትና ንስሐ በመግባት መጠበቅ ይገባናል:: ለሁሉም የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን:: አሜን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር::*



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ሮምን እንደ ጎበኘኋት

መምህር ብርሃኑ ጎበና

ሮሙሉስ የጥንትዋ ሮማ መሥራች ነው:: አፈ ታሪክን መሠረት ያደረጉት የሮማ ታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚተርኩት ዘመኑ 753 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው:: ለዛሬዋ ሮም ጥንታዊ ቅርሶችዋ የኢኮኖሚዋ የጀርባ አጥንት በመሆናቸው አክብራና ተከባክባ ይዛቻዋለች:: እነርሱም ጥንተ ታሪኳን ለዘመኑ ትውልድ እያንፀባረቁ ይገኛሉ:: ምንም እንኳን የቀደመ ግርማ ሞገሳቸው በዘመን ብዛት የተነሣ ቢገፈፍም ዛሬም የተመልካችን ልብ የሚመስጥ ገጽታቸው ከእነርሱ ጋር ነው:: የምሕንድስና ባለሞያ በሥነ ሕንፃዎቹ ውበት ቢደመም÷ የታሪኩ ምሁር ደግሞ በሥነ ቃላት ተከሽኖ በወረቀት ላይ አካል ገዝቶ በምናቡ ስሌዳ ላይ ተቀርጾ የነበረው ጥንተ ታሪክ በአካል ሲያየው በተመስጦ ባሕር ጠልቆ ይዋኛል:: በአፍና በመጣፍ ሲሰበክለት የነበረውን የጥንት ክርስቲያኖችን የእምነት ጽናት በተጋድሎው ላይ በአካለ ሥጋ ተገኝቶ በቃል የሰማውን፣ በመጣፍ ተጥፎ ያነበበውን በዓይነ ሥጋ ሲያይ ቤተ ክርስቲያን በስደት ወደ ነበረችበት ወደ ቀደመው ዘመን በአሳብ ይነጉዳል:: በዓይነ ኅሊናው የጥንት ክርስቲያኖች ከዓላውያን ነገሥታት ጋር ያደረጉትን ፍልሚያ ይቃኛል::

ወንጌል በዋዛ እንዳልተሰበከች ክርስትናም ያለ ተጋድሎ እንዳልተስፋፋች የሮም ከተማ በጉያዋ አቅፋ የያዘቻቸው ካታኮምብ /ግበበ ምድር/፣ ኮሎሲየም÷ /ፍላብያን አምፊ ቴአትር/፣ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ሰማዕትነትን የተቀበሉበት ሥፍራ ሕያው ምስክሮች ናቸው::

ሮምን እንደ ቀለበት ከከበባት ጥንታዊ ግንቧ አንሥቶ በውስጥዋ እንደ ፈርጥ እየተንቦገቦጉ የትውልዱን ስሜት በአድናቆት አውታር ወጥረው የያዙት ቅዱሳት መካናትን በጎበኘሁበት ጊዜ፣ ክርስትናን እንደ ምድር ለማጥፋት ያለ የሌለ ኃይላቸውን ከብልሃት ጋር አስተባብረው የተጠቀሙት የሮም ቄሣሮች በዓይነ ኅሊናዬ ተሰለፉ::

## ኔሮን ቄሣር /54- 68 ዓ.ም/

ለሮም የመጀመሪያው ንጉሥ አይደለም:: ዳሩ ግን የመጀመሪያውን ሥቃይና ስደት በቤተ ክርስቲያን ላይ ለማወጅና ብዙ የወንጌል መልእክተኞችን ለማሰቃየት ግንባር ቀደም ነው:: ለነገሩ መነሻ ያደረገው የሮምን ከተማ በእሳት መጋየት ነው:: ክርስቲያኖችን ይጠላ ስለነበር ቃጠሎውን ክርስቲያኖች እንደ ፈጸሙ አድርጎ ለሕዝቡ በማቅረብ ሕዝቡ በክርስቲያኖች ላይ በጥላቻ እንዲነሣሣ አደረገ::

በሮም ያሉ የጣዖት ካህናትም ለአማልክቶቻችን የማይታዘዙ ክርስቲያኖች በመኖራቸው አማልክቶቻቸው በዚህ ተቆጥተው ይህ መቅሰፍት እንደ ደረሰ አድርገው ለሕዝቡ በመናገራቸው የሕዝቡ ጥላቻ እየገፋ እየጠነከረ መጣ:: በዚህ ጊዜ ኔሮን ክርስቲያኖችን ለማጥፋት አመቺ ሁኔታ ተፈጠረለት:: ብዙ ክርስቲያኖች ያለ ፍርድ በጭካኔ ተጨፈጨፉ:: ብርሃናተ ዓለም የተባሉት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ የሰማዕትነት ጽዋቸውን የጨለጡት በዚህ ዘመን ነው::

ሮም የቅዱስ ጴጥሮስ ሃገረ ስብከት ነች፤ ለ25 ዓመታት በሮም አስተምሯል:: በቅዱስ ጴጥሮስና በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት በሮም ክርስቲያኖች እየበዙ መጡ፤ ክርስትናው የሮማ ባለሥልጣናት ቤት ድረስ ገባ:: የኔሮን የቅርብ ባለሥልጣናት የሆኑት የአልግቢኖስና የአግሪጳ ሚስቶች ሳይቀሩ ወደ ክርስትናው ተሳቡ::

በቅድሚያ በሮም አደባባይ ላይ ለክርስትና መሰበክ ሰማዕት የሆነው ቅዱስ ጳውሎስ ነው:: ሐዋርያው አንገቱ በሠይፍ ሲቆረጥ ጭንቅላቱ ሦስት ቦታ ላይ እንደ ኳስ ነጥሮ አርፎ ስለነበረ በነዚያ ሥፍራዎች ላይ ውኃ ፈልቋል፤ ዛሬ በእነዚህ ቦታዎች ላይ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቷል:: ቦታዎቹም ለቱሪስት ዕይታ ተከልለዋል::

በእስር ላይ የነበረውን የቅዱስ ጳውሎስን መሰየፍ የሰሙት የአግቢኖስና የአግሪጳ ሚስቶች ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ የሚሞት ከሆነ ወንጌልን የሚሰብክላቸው ሰው እንደሚያጡ አሳምነው በሮም ከተማ ግንብ /የሮማን ከተማ እንደ ቀለበት የከበበ ግንብ ሲሆን ዛሬም በቱሪስቶች ከሚጎበኙት ጥንታውያን ቅርሶች አንዱ ነው/ በገመድ አሥረው በቅርጫት በማውረድ ቅጽረ ሮማን ለቅቆ እንዲወጣ አደረጉት::

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሮምን ለቆ በአፒየም ጎዳና ጉዞውን ቀጠለ:: የሮምን ግንብ እንደ ወጣ አንድ ቀይ ጎልማሳ ወደ እርሱ ሲመጣ አየ፤ እየቀረበ ሲመጣ ጌታችን መሆኑን ተረዳ:: ወዲያው በግንባሩ ተደፍቶ "ጌታዬ ÷ ወዴት እየሄድክ ነው?" አለና ጠየቀው፤ "ዳግም በሮም ልሰቀል" የሚል መልስ ከጌታ ሲሰማ ቅዱስ ጴጥሮስ አዝኖ በሰማዕትነት ያልፍ ዘንድ የጌታ ፈቃድ መሆኑን ተረድቶ እንደገና ወደ ሮም ተመለሰ:: ጌታና ቅዱስ ጴጥሮስ በተነጋገሩበት ቦታ ላይ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል:: በዚህ ሥፍራ የጌታችን የእግሩ አሻራ ቀርቶ ስለነበር ያ ቦታ በተለየ ሁኔታ ተከልሎ ይጎበኛል::

የኔሮን ወታደሮች ቅዱስ ጴጥሮስን እያሰሱት ስለነበር ወደ ሮም ሲገባ ያዙት:: የፈለጉትን እንዲያደርጉበትም ራሱን አሳልፎ ሰጠ:: የመስቀያውን እንጨት ባቀረቡለት ጊዜ እኔ እንደ ጌታዬ ልሰቀል አይገባኝም በማለት የቁልቁሊት እንዲሰቅሉት ለመነ፤ ያለውንም አደረጉለት:: የቁልቁሊት ተሰቀለ:: ሐምሌ 5 ቀን 67 ዓ.ም በሰማዕትነት ዐረፈ:: ሰማዕትነትን በተቀበለበት ቦታ በስሙ ቤተ ክርስቲያን ታንፆለታል::

አስከሬኑም በኋለኛው ዘመን ከተቀበረበት ወጥቶ በስሙ በታነፀው ሥፍራ በዛሬው ቫቲካን ዐርፏል::

አሠቃቂውና አስደንጋጭ እልቂት በነቅዱስ ጳውሎስ ብቻ አልነበረም የደረሰው፤ በዘመኑ በነበሩ ክርስቲያኖች ላይ ሁሉ እንጂ:: ከሮም ከተማ ውጭ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ሳይቀሩ ከወን ድሞቻቸው ጋር የሰማዕትነት ጽዋቸውን ለመቀበል ከያሉበት ተሰ ብስበው ለሃይማኖታቸው ያላቸውንም ፍቅር በሰማዕትነታቸው አሳይተዋል:: ከሞት የተረፉትም እነሱን ያገኘ ያገኘናል ሳይሉ በግፍ ያለቁ ወገኖቻቸውን ዐጽም ሰብስበው በተሰወረ ዋሻ /ካታኮምብ/ ውስጥ ያኖሩ ነበር::

## ካታኮምብ

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስትነሣ ካታኮምብ /ግበበ ምድር/ አብሮ መነሣቱ አይቀሬ ነው:: ለምን ቢሉ በቀደሙት ዘመናት ቤተ ክርስቲያን ካታኮምብ ገብታ ነበርና:: ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ለነበሩት ሮማውያን ካታኮምብ የምሚለው ስም ሽለቆዋማ ከሆነ ቦታ ጋር የተያያዘ ነበር:: የኋላ





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ኋላ ግን ከመሬት ውስጥ ለተመሠረተው የክርስቲያኖች መካነ መቃብር መጠሪያ ሆኗል::

ቀደምት ክርስቲያኖችን ዋሻ ፈልፍለው መግባትን ምን አስገደዳቸው? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ግልጽና የማያከራክር ነው:: ይኸውም በገጸ ምድር ላይ የመኖር መብት ስለ ተነፈጉ የሚል ነው:: እንኳን የተለየ የመቀበሪያ ቦታ ሊኖራቸው ቀርቶ አስከሬናቸው በአንድ ሕዝብ መካነ መቃብር ውስጥ ለመቀበር እድል የሚያገኙት ጥቂቶቹ ነበሩ:: ቤተ ክርስቲያንን የሮም ቄሣሮች ሲያሳድዱአት ወደ ውጪው ዓለም የምትወጣበት ጊዜው እስኪደርስ ካታኮምብ ገብታለች::

ካታኮምቦች በጥንቷ ሮማ ላይ ብቻ አልነበረም የተሠሩት፤ በሌሎቹ አጎራባች አገሮችም ጭምር እንጂ:: በአሁኑ ጊዜ ከ60 በላይ ካታኮምቦች እንዳሉ ይገመታል:: የብዙ ክርስቲያኖች የመጠለያና የመቀበሪያ ቦታ የነበረው ግን በዛሬዋ ሮም ላይ የሚገኘው ርዝመቱ 20 ኪ.ሜትር የሚሆነው ካታኮምብ ነው::

ከመሬት የላይኛው ክፍል ወደ ታች ብዙ ርቆ የተገነባው ይህ ካታኮምብ የጥንት ክርስቲያኖችን መንፈስ ጠንካራነትንና ጥበብን የምንገነዘብበት ነው:: ለዚህ ሥራ የተለዩት ክርስቲያኖች ፎስርስ /Fossores/ በሚል ስያሜ ይታወቃሉ:: የዛሬዎቹን መሐንዲሶች ስም ይጋራሉ::

በካታኮምብ ልዩ ልዩ ዓይነት መቃብሮች፣ የጸሎት ቤቶች፣ ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን የተውጣጡ ታሪኮችና ሥዕላት /ሲምበል/ የመሳሰሉት ይገኛሉ:: ለዘመነኛው መሐንዲስ እንኳን የሚያስደምም አሠራር ያለው ይህ ካታኮምብ የቀደሙትን ክርስቲያኖች ጥበብና ትጋት እንድናደንቅ ያስገድደናል::

## የመቃብራቱ ዓይነት

የተለያየ ቅርጽና አሠራር ያላቸው መቃብሮች በካታኮምብ ውስጥ ይታያሉ::

❖ ሉክሊ /Loculi/:- ግድግዳው ተቦርቡሮ የአራት ማዕዘን /ሬክታንግል/ ቅርጽ ይዞ የተሠራ፤ ለአንድ ሰው መቀበሪያ ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ሟቹ በጨርቅ ተገንዞ ያለ አስከሬን ሣጥን የሚቀበርበት ነው:: ከተቀበረ በኋላ አፉ በሸክላ ወይም በእምነ በረድ ይዘጋል:: ይህ ዓይነቱ መቃብር በብዛት በጨቅላ እድሜ ሳሉ ለሚሞቱ ሕፃናት የተዘጋጀ ነው:: በብዛትም ከሌሎቹ የመቃብር ዓይነቶች የላቀ ነው:: በወቅቱ የሕፃናት ሞት ከፍተኛ እንደ ነበር ከተሠሩት የመቃብር ቦታዎች መበርከት በመነሣት መገንዘብ ይቻላል::

❖ አርኮሶሊየም /Arcosolium/:- ውብና ለየት ያለ ቅርጽ እንዲኖረው ተደርጎ የተዘጋጀ የመቃብር ዓይነት ነው:: ከላይ የቅስት ወይም የደጋን ዓይነት ቅርጽ አለው:: ለአንድ ሰው ወይም ለመላ ቤተሰብ እንዲበቃ ተደርጎ ይሠራል::

❖ ሳርኮፋገስ /Sarcophagus/:- ከድንጋይ ወይም ከእምነ በረድ የተሠሩ እንደ ሣጥን ያሉ መቀበሪያዎች ሲሆኑ ከዋጋቸው ውድነት የተነሣ የዚህ ዓይነት መቃብሮች በካታኮምብ ብዙም አይታዩም::

❖ ካቢኩለም /Cabiculum/- የካሬ /ስኩዌር/ ወይም ፖሊጎናል ቅርጽ የያዙ አነስተኛ ክፍሎች ናቸው::

❖ ክሪፕት /Crypt/- በካታኮምብ ውስጥ የሚገኙ ሰፋፊ ክፍሎች ናቸው:: ለጸሎት፣ ለመሰብሰቢያና ለተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ይጠቀሙበት እንደ ነበር የሚያሳዩ አንዳንድ መረጃዎች አሉ:: በቅዱሳት ሥዕላት፣ በሞዛ ይክና በሌሎች አርክቴቸክራል ሥራዎች የተጌጡ ናቸው:: በእነዚህ ክፍሎች የአንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ በሰማዕትነት ያለፉ ቅዱሳን መቃብር ይኖራል::

## የካታኮምብ ሥዕላት

ቀደምት ክርስቲያኖች ትምህርታቸውን ያስፋፉት በካታኮምብ ውስጥ ነው:: በዚያ ብዙ አማኞች እየመጡ የማኅበራቸው አባል መሆን ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ የክርስትናን ትምህርት አስፋፍቶ ለመስጠት በቂ መጻሕፍት አልነበሩም:: እንደ ልብ ወጥቶ ለመፈለግና ለማዘጋጀት ነጻነት ስላልነበራቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ምሳሌዎችን በሥዕል እያሠፈሩ ማስተማር ጀመሩ:: ሥዕሎችም የሚሳሉት በምሳሌነት "ሲምበል" ሲሆን የሚሳሉትም በአመድና በከሰል በዋሻው ዙሪያ /በአፈ ጽዮን/ ነው::

በምሳሌ ማስተማር የማይታየውን ረቂቅ ምሥጢረ መለኮት ለሰው አእምሮ እንዲረዳና በአእምሮ ሰሌዳ ላይ እንዲታተም ለማድረግ ጠቃሚ መሆኑ በጥንት ክርስቲያኖች ታምኖበት ነበር:: ትምህርተ ሃይማኖትን በምሳሌነት እንዴት ይገልጹት እንደነበር የሚከተሉትን ለአብነት እጠቅሳለሁ::

❖ እረኛው በትከሻው በግ ተሸክሞ /Good Shephred/- ገና በመግቢያው በር በዋሻው ፊት ለፊት /በአፈ ጽዮን/ ተሥሎ የሚገኝ ሲሆን እረኛው "ቸር እረኛ እኔ ነኝ" ያለው የጌታ ምሳሌ ሲሆን፤ በጉ ደግሞ ጠፍቶ ሳለ የተገኘው የሰው ልጅ ምሳሌ ነው::

❖ ዓሣ - በጥንት ግሪኮች ዓሣ ሲሉ "ኢኽቴስ" ይላሉ:: የዚህ ቃል እያንዳንዱ ፊደል ትንታኔ አለው:: ኢ — ኢየሱስ÷ ኽ — ኽርስቶስ÷ ቴ — ቴውኢዮስ /የእግዚአብሔር ልጅ/ ÷ ስ — ሶቴር /መድኀን/ በተገናኝ ሲነበብ "ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር መድኅን" ማለት ነው::

❖ ሞኖግራም ኦፍ ክራይስት /Monogram of Christ/— የሁለት የግሪክ ፊደላት ጥምር ሲሆን እነዚህ ፊደላት «X» እና «P» ናቸው:: ፊደላቱ አንዱ ባንዱ ላይ ተነባብረው ተሥለዋል:: «X» የሚለው ፊደልና «P» የሚለው ፊደል በተገናኝ ሲነበቡ ክርስቶስ የሚል ትርጉም ይሰጣሉ::

❖ የወይራ ዝንጣፊ የያዘች ርግብ — ርግብ ለክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ የሰላም ተምሳሌት መሆንዋ ይታወቃል:: ጥንት ክርስቲያኖች በክርስቶስ የተገኘውን ሰላምና ዘላለማዊ ሕይወት የወይራ ዝንጣፊ በያዘች ርግብ መስለው ያስተምሩ ነበር:: ይህም ለኖኅ የጥፋት ውኃን መጉደል የምሥራች ይዛለት በመጣችው የወይራ ቀንበጥ እንዳ ሳወቀችው፤ ክርስቲያኖችም የኃጢአት ውኃ መጉደሉንና በክርስቶስ ሰላምን እንዳገኘን ለመግለጥ የኖኅን ርግብ በምሳሌነት ይሥሏት ነበር::

❖ አልፋና ኦሜጋ — የመጀመሪያና የመጨረሻ የግሪክ ፊደላት ሲሆኑ ጌታ ፊተኛና ኋለኛ÷ መጀመሪያና መጨረሻ፤ መሠረቱም ጠፈሩም እርሱ መሆኑን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ምልክት ነበር::

❖ መልሕቅ — የወደፊት ሕይወት ተስፋን የሚያመለክት ነው::

❖ ፒኮክ — የተለያየ ኅብር ያላት የፒኮክ ወፍ የማትሞት የማትፈርስ የሕያዊት ነፍስ አምሳል ተደርጋ ተወስዳለች::

❖ ፎኒክስ /Phoenix/ — በዚያን ዘመን በብዙዎች ዘንድ እንደሚታመነው ፎኒክስ በመባል የምትታወቀው ወፍ መስህብነት ካለው ቀለሟ በተጨማሪ በየሺህ ዘመኑ እየታደሰች የምትኖር መሆንዋ ይነገርላታል:: ሺህ ዘመን ሲሞላት አካልዋን እሳት ውስጥ ትጨምረዋለች:: ከዚያም አመድ ከሆነው አካልዋ እንደ ገና አዲስ ሰውነት ይዛ ትነሣለች:: ይህች ወፍ ለትንሣኤ ሙታን ምሳሌ ሆና ትጠቀስ ነበር::

*ይቆየን::*





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት



*መምህር ኃይለ ማርያም ላቀው*

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየዘመኑ ከደረሱባት የአላውያንና የመናፍቃን ጥቃት የጥንታውያኑ አድባራትና ገዳማት እንዲሁም የንዋያተ ቅድሳት እና መጻሕፍት ውድመትና ምዝበራ ባልተ ናነሰ፣ በጥምቀተ ክርስትና ወልዳ በእናትነት ፍቅር በጉያዋ አቅፋ ዕውቀት መንፈሳዊ ወተቷን እያጠጣች በማሳደግ ለአካለ መጠን ያደረሰቻቸውን ዕንቁ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን አጥታለች:: ከእነዚህ ጉዳቶች ውስጥ ከ1928–1935 ዓ.ም ድረስ ሀገራችንንና ቤተ ክርስቲያንን ሲያውካት የነበረው የፋሽስት ጣልያን ወረራ ተጠቃሽ ነው::

የእሱ ያልሆነውን ሊወስድ ጦሩን አስከትቶ ውቅያኖስ አቋርጦ ወደ ሀገራችን የመጣው የጣልያን ወራሪ ጦር ምንም እንኳ መጨረሻው ባይሠምርለትም በወረራ በቆየባቸው ጥቂት ዓመታት በርካታ ውድመቶችን አድርሷል:: በጠንካራ ሊቃውንቷ አማካይነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለዓመታት በገነባቻቸው አድባራትና ገዳማት እንዲሁም የሀገሪቱን ታሪክና ዕውቀት በወግ ሰንቀው በያዙ ልዩ ልዩ የብራና መጻሕፍትና ንዋያተ ቅድሳት ውድመትና ዝርፊያ ተፈጽሞባታል:: በበለጠም የእነዚህ ሀብታት ጠባቂና ተከባካቢ የነበሩትን አባቶች በተለይም ቤተ ክርስቲያንን ነገ የሚረከቡትን ሕፃናት ከየትምህርት ገበታቸው በማደን ጨፍጭፏል:: የቀሩትንም ወንድነታቸውን በመስለብ የግፍ ሥራን ሠርቷል፤ በአካላቸው ላይ አሰቃቂ ጉዳት አድርሶባቸዋል::

ድሮም ላይሆንለት ሀገረ እግዚአብሔር የሆነች ሀገራችንን ወሮ የነበረው ጣልያን የእግዚአብሔር ኃይል በኢትዮጵያውያኑ አርበኞች ላይ አድሮ ከሀገራችን ተጠራርጐ ወጣ:: ኢትዮጵያኑም ትዕቢተኞችን የሚበታትን፣ ብርቱዎችን ከዙፋናቸው የሚያዋርድ፣ የተዋረዱትን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፣ የተራቡትን በቸርነቱ የሚያጠግብ፣ ባለጠጐችንም ባዶ እጃቸውን የሚሠድ እግዚአብሔር በማን አለብኝነት ሀገራችንን ወሮ የነበረው ጠላት ድል ተመትቶ እንዲወጣ በመደረጉ ደስታቸው ከፍተኛ የነበረ ቢሆንም፤ በአንጻሩ በወረራው በቤተ ክርስቲያኑና በሊቃውንቷ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ ማዘናቸው አልቀረም::

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊት እቴጌ መነን በ1933 ዓ.ም ከስደት ሲመለሱ እቴጌዪቱ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ታቦተ ሕግ በሐዋርያው ስም ስያሜውን ባገኘው የሰዋስወ ብርሃን ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት በስተ ደቡብ ከመንፈሳዊ ተማሪዎች መኖሪያ ቤት በስተ ምዕራብ ለጊዜው በመቃኞ ውስጥ ገብቶ ሥርዓተ ቅዳሴ እና መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጥ አስደረጉ:: ቆይቶም እቴጌ መነን በስደት በነበሩ ጊዜ ይዘውት ለተሰደዱት የቅዱስ ጳውሎስ ታቦት «ለሀገሬ ካበቃኸኝ ቤተ ክርስቲያን አሠርቼ በከፍተኛ ታሪካዊ ቦታ አኖርሃለሁ» ብለው ተስለው ስለነበር በ1935 ዓ.ም ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን በዘመናዊ መልክ አሠርተው፣ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ታቦት ከአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ታቦት ጋር አስገብተው አገልግሎት እንዲሰጥ አድርገዋል:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከግል ገንዘባቸው ባደረጉት ድጋፍ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ቤት እንዲከፈት እንዳደረጉ ግርማዊት እቴጌም በራሳቸው መሬት ላይ ታቦቱን ካስተከሉ በኋላ የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት እንዲታነፅ አደረጉ:: የገንዘብ ድጋፍ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ የት/ቤቱን የሥራ አመራር ለብዙ ጊዜ ከልዩ ጽ/ቤታቸው ተቆጣጣሪ መድበው መሠረት እስኪይዝ ድረስ ከጠበቁ በኋላ ከበቂ ማደሪያ ጋር ለጠቅላይ ቤተ ክህነት አስረከቡ::

ንግሥቲቱ መጀመሪያ ይኽን ት/ቤት ሲያቋቁሙ ዓላማቸው ጠላት በወረራ ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት ያደረጠሰባቸውን ሕፃናትና ወጣቶች ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ሰብስቦ ለመርዳት ነበር:: ቆይቶ ግን የትምህርት ቤቱ ዓላማ እነርሱንም ሆነ ሌላውን ምእመን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማሠልጠን ሆነ::

በዚህ ዓላማ መሠረት የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ለአያሌ ዓመታት የቤተ ክርስቲያንና የቤተ መንግሥት አገልጋዮች ወጥተውበታል:: ግርማዊት እቴጌ መነን ይኽን ትምህርት ቤት የማሳደግና የማስፋፋት ፍላጐት ስለነበራቸው አዳሪ ተማሪዎች ቀን ቀን የአስኳላ /ዘመናዊ/ ትምህርት፣ ማታ ማታ ደግሞ የአብነት ትምህርት እንዲማሩ አስደረጉ:: ዘመናዊው ትምህርት ቢቋቋም ደረጃው ከ1ኛ–5ኛ ክፍል ብቻ ሆኖ ተማሪዎች ከዚህ ሲያልፉ ወደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ቤት ይዛወሩ ነበር:: ት/ቤቱ በዚህ ደረጃ እስከ 1964 ዓ.ም ድረስ ሲያገለግል ቆየ:: ይህም ከ1965– 1968 ዓ.ም ድረስ:: ከተለያዩ አህጉረ ስብከት ለሚመጡ ካህናት የ10ና የ6 ወር ሥልጠና ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በነበረው የመንግሥት ለውጥ ሳቢያ የግልና የሃይማኖት ተቋማት ወደ መንግሥት ይዛወሩ የሚል ዐዋጅ ወጥቶ ስለነበር ት/ቤቱ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ወደቀ::

## የመንፈሳዊ ት/ቤቱ ዳግም መከፈት

ቤተ ክርስቲያን ተተኪ ሊቃውንትን በማፍራት ረገድ የነበራት ደገኛ ተግባር እንዳይቋረጥ በሚል በወቅቱ የነበረው የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አስተዳደር በጉዳዩ ላይ መከረ:: በውይይቱም መንግሥት ሰላም በር አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ት/ቤት ተብሎ የሚጠራውን ት/ቤት ሕንፃዎች ቢወስድባትም ቤተ ክርስቲያ ሰፊ ጥናት አድርጋ ሌሎች አዳዲስ የተማሪዎች መማሪያ ክፍል በመገንባት በጥር ወር 1973 ዓ.ም የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት እንደገና ሥራውን እንዲጀምር አደረገች:: በዚሁ ትምህርት ቤት የበላይ ኃላፊነት በማገልገል ላይ እያሉ ሕይወታቸው ባለፈው በብፁዕ አቡነ በርናባስ የበላይ ጠባቂነት ለአራት ዓመታት ከተለያዩ አህጉረ ስብከት የሚመጡትን ደቀ መዛሙርት ለማሠልጠን ሥርዓተ ትምህርት ቀርፆ የማስተማርና ያማፀልጠን ተግባሩን ጀመረ::

ከብፁዕ አቡነ በርናባስ ህልፈት በኋላ ግቢው እንዲከበርና ውበት እንዲኖረው ለማድረግ በአዳሪው ትምህርት ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞችና የአካባቢው ካህናት በሙሉ ት/ቤቱን እንዲለቁ ተደረገ:: የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢም ያን ጊዜ እንዲከለል የተደረገ ሲሆን በቅጽር ግቢው ውስጥም ለትምህርት ቤቱ ውጫዊ ውበት የሚሠጡ በርካታ የጽድ ዛፎችም በመተከላቸው ዛሬም ቢሆን ለት/ቤቱ ልዩ ውበት ሰጥተውታል::

### የትምህርት መርሐ ግብር

የሰዋስው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት በዲፕሎማ የትምርት መርሐ ግብር በሴሚናርና በመ ጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት ትርጓሜ አያሌ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን በማሠልጠን ላይ ይገኛል:: በከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤቱ በእነዚህ ሦስት መርሐ ግብሮች የሚሠጡት የትምህርት ዓይነቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው

1. <u>የቋንቋ ትምህርት</u>:- ምንም እንኳን ይህ ትምህርት የሐዲሳትና የብሉያት መርሐ ግብር ተማሪዎችን ባይመለከትም በሥሩ አማርኛ፣ እንግሊዝኛ እና ግእዝ ይካተታሉ::
2. <u>ማኅበራዊ ሳይንስ</u> /Social science/:- በዚህ ዘርፍ ፍልስፍና /philosophy/፣ ሥነ ልቡና /Psychology/ እና የዘመናዊ አስተዳደር /Management/ ያካትታል::
3. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት</u> /Biblical studies/:- የብሉያትና የሐዲሳት ትምህርት ይካተታሉ::
4. <u>ታሪክና ዶግማ</u>:- አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ዶግማ፣ ንጽጽራዊ ትምህርተ ሃይማኖት እና የአበው ታሪክ ያካትታል::
5. ትምህርተ ኖሎት /pastoral theology/ እና የስብከት ዘዴ /Homiletics/

ደቀ መዛሙርቱ ከላይ የተዘረዘሩትን የትምህርት መርሐ ግብሮች በማጠናቀቅ የትምህርት ማስረጃ ዲፕሎማ ይቀበላሉ:: ከመደበኛ ትምህርታቸው በተጨማሪም ተማሪዎች በግቢው ቆይታቸው በግቢው ውስጥ በሚገኘው በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ተራ ወጥቶላቸው ይቀድሳሉ:: ማህሌት ይቆማሉ:: ከዚህ ባሻገር የትምህርት ቤቱ መምህራን እና ደቀ መዛሙርቱ ባሉበት በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ውስጥ የተማሩትን የስብከት ዘዴ በተግባር ያሳያሉ:: መምህራንና ደቀ መዛሙርት በጐደለው አሟልተው በጥሩ ሁኔታ የተማረውን ዘዴ በተግባር ያዋለውን ደቀ መዝሙር ያመሰግኑታል:: በዚህ ዓይነት መልኩ እያንዳንዱ ደቀ መዝሙር ልምምድ ያደርጋል::

### የመግቢያ መመዘኛዎች

ወደ መንፈሳዊ ት/ቤት ለመግባት በመመዘኛነት ከሚሰጠው የመግቢያ ፈተና ጋር ሥልጣነ ክህነት፣ ተማሪው የሚመጣበት ሀገረ ስብከት የድጋፍ ደብዳቤ፣ ሙሉ ጤነኞች ለመሆናቸው የጤና መረጋገጫ ሰርተፊኬት፣ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቢያንስ በአንዱ ምስክር /ማስረጃ/ መያዝ ይጠይቃል::

ተማሪዎች ወደ መንፈሳዊ ት/ቤት ገብተው የሚማሩት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል እንደ መሆኑ መጠን በክፍል ውስጥ የቀሰሙትን መንፈሳዊ ዕውቀት ወደ ተግባር እንዲለውጡ ልዩ ልዩ መርሐ ግብሮች ይዘጋጅላቸዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ቅዳሜና እሑድ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሥር በሚተዳደሩ ገዳማትና አድባራት በሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር ተመርቀው እስኪወጡ ድረስ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶችን ያስተምራሉ፣ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን በዓላት በመገኘት ለተሰበሰቡት ምእመናን ትምህርተ ወንጌል ይሰጣሉ፤ ሲመደቡም ወደ ተለያዩ ክፍለ ሀገሮች ሄደው ያገለግላሉ:: በክረምትም ለዕረፍት ሲበተኑ ወደ የመጡበት ሀገረ ስብከት ተመልሰው በቀሰሙት ዕውቀት አገልግሎት ይፈጽማሉ:: ለዚህም የማረጋገጫ ደብዳቤ ከሀገረ ስብከቱ ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል::

### የትምህርት ቤቱ የልማት እንቅስቃሴ

የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት በአሁኑ ሰዓት ባለው ውሱን ሥፍራ ላይ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን ያለማል:: ምርቱም ለመሥሪያ ቤቱም ሠራተኞች ሆነ ለውጭ ለሽያጭ ቀርቦ ገቢው ለት/ቤቱ ይውላል:: ትምህርት ቤቱ በቂ ማሰማሪያ ሥፍራ ባይኖረውም የተወሰኑ የወተት ላሞችን በማርባት ላይ ይገኛል:: ሌላው ለአያሌ ዓመታት በትምህርት ቤቱ ቅጽር ግቢ ያለምንም አገልግሎት ተዘግቶ ይኖር የነበረውን ስድስት ክፍል ቤት በማደስ ዘመናዊ ሙዓለ ሕፃናት ከመገንባት ጐን ለጐን የአካባቢውን ሕፃናት ከመናፍቃን ትምህርት በመታደግ በሃይማኖት እንዲጐለብቱ በሥነ ምግባር እንዲያብቡና በዘመናዊ ዕውቀት እንዲደረጁ ከማድረግ ባሻገር ለቤተ ክርስቲያን ልጆች የሥራ ዕድል ለመፍጠር የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጋር በመሆን ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል:: አጸደ ሕፃናቱም በ1996 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ሥራው ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት እንደሚሆን ይጠበቃል::

### ችግሮች

መንፈሳዊ ት/ቤቱ ያሉበት ችግሮች በርካታ ናቸው:: ከእነዚህም መካከል የበጀት እጥረት ዋነኛው ሲሆን በተለይም ለመጻሕፍት ትርጓሜ ተማሪዎች የተፈቀደው ኮታ ማነስ፤ ከዚህ የተነሣም ት/ቤቱ ከተለያዩ አህጉረ ስብከት የሚመጡትን ደቀ መዛሙርት ለመቀበል መቸገሩ፣ የመምህራን እጥረት፣ የተማሪዎች ማደሪያ ቤቶች አሮጌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ዋና ናቸው::

### መልእክት

በመጀመሪያ ወደዚህ መንፈሳዊ ት/ቤት የሚገቡ ደቀ መዛሙርት አባቶችና ወንድሞች ቤተ ክርስቲያን የምትጥልባቸውን ኃላፊነት በበቂ ሁኔታ ለመወጣት እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በቂ ሥነ ልቡናዊ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል:: የሚሰጣቸውን ትምህርት በአግባቡ በመቅሰም ሳይተርፋቸው ቀንሰውና ከልጆቻቸው አፍ ነጥቀው አሥራቱን በኩራቱን በማውጣት ት/ቤቱ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደረጉትና በማድረግ ላይ ያሉትን ምእመናን በትምህርት ማጽናት፣ ከመናፍቃንም የክህደት ትምህርት መጠበቅ ይኖርባቸዋል::

አህጉረ ስብከቱም ከልጅነት እስከ እውቀት በተለያዩ የአብነት ት/ቤቶች የደከሙትንና በዚህ ት/ቤት የሚሠጠውን ትምህርት በአግባቡ ተከታትለው የሚሄዱትን ምሩቃን በተገቢው መንገድ ተቀብለው የተማሩትን ትምህርት በሥራ ላይ እንዲያውሉ ተገቢውን ክብካቤ አድርገው መመደብ ይኖርባቸዋል::

ምእመናንም ቤተ ክርስቲያናቸው የምታኮራ የመንፈሳዊ ዕውቀት ምንጭ በመሆኗ ኮትኩታ ባስተማረቻቸው ምሁራን መጠቀም ይኖር ባቸዋል:: እነዚህን መምህራንን የሚቀበሉ መንፈሳዊ ት/ቤቶች እንዳይዘጉ መምህራንም እንዳይፈናቀሉ የጐደለውን በማሟላት በገንዘብ በቁሳቁም ሆነስ በሐሳብም ት/ቤቱን ሊረዱት ይገባል::

ይህ አንጋፋ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት ማስተማር ከጀመረበት ዛሬ ለጽጽስና የበቁ በርካታ አባቶችንና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ኮትኩቶ አስተምሮ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን በማስረከቡ ከፍተኛ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማዋል:: ወደፊትም ቤተ ክርስቲያን ዐይኗን የምትጥልባቸው አባቶችና ወንድሞች የሚሠጠውን ትምህርት በአሁኑ ሰዓት በመከታተል ላይ ስለ ሚገኙ ምእመናን፣ ት/ቤቱም ሆነ ቤተ ክርስቲያኑ የእነርሱ መሆኑን ተረድተው በሐሳብ፣ በገንዘብና በቁሳቁስ በመደገፍ ደቀ መዛሙርቱን በሞራል በማበረታታት የበኩላቸውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

<u>ከዝግጅት ክፍሉ</u>:- *በመጨረሻም ስለ ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ከላይ አጠናቅረን ያቀረብነውን መረጃ በመስጠት የተባበሩንን በሙሉ እናመሰግናለን::*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቅድስት እሌኒ

ጌታቸው በቀለ



መስቀሉ ተቀብሮበት የነበረው ቦታ /ዛሬ አርመኖች ቤተ ክርስቲያን አንጸውበታል/

እሌኒ ብሔረ ሙላዷ ጥንተ ነገዷ ወዴት ነው? ቢሉ ከኢየሩሳሌም አምስት ኪ.ሜ ርቃ በምትገኘው በቢታንያ በ247 ዓ.ም ተወለደች:: «እሌኒ» የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ሲሆን ትርጓሜው ቆንጆ ማለት ነው:: አንድም ችቦ፣ መብራት ማለት ነው::

እሌኒ ተርቢኖስ የሚባል ነጋዴ ባል ነበራት:: ተርቢኖስ አረማዊ ሲሆን እሌኒ ግን አይሁዳዊት ናት:: ባለቤቷ ለንግድ ወደ ሩቅ ሀገር ሲሄድ ሰው እንዳያያት፣ፀሐይ እንዳይመታት ቤት ሠርቶላት፤ ወጥታ ወርዳ የምታገለግላት ሠራተኛ ቀጥሮላት እሱ ተነሥቶ ወደ ንግዱ ሄደ:: ነጋዴዎቹ ወደ ሀገራቸው የሚመለሱት ሦስትና አራት ዓመታትን ያህል ኑረው ነው:: ነጋዴዎቹ እርስ በርሳቸው ከባሕር ወጥተን የብስ ረግጠን ከማዕበል፣ ከሞገዱ ድነን እንደ ወጣን ሚስቶቻችን ሌላ ሳይለምዱ ከሌላ ሳይወልዱ ብናገኛቸው መልካም ነበር ይባባሉ ጀመር:: በዚህ ጊዜ ተርቢኖስ እኔስ እግዚአብሔር ስንኳን ከማዕበል ከሞገድ አድኖን ከባሕር በወጣሁ የብስ በረገጥኩ እንጂ ሚስቴን አምናታለሁ በዚህ አልጠረጥራትም አለ::

እሌኒም ባለቤቷ ለንግድ ከተለያት ወዲህ ስለ ባሏ ተግታ ከመጸለይና ከማሰብ በስተቀር ከቤቷ ወደ የትም ንቅንቅ አትልም ነበር:: ከጓደኞቹ አንዱ ያንተ ሚስት ከሔዋን ልጆች ልዩ ናትን? ሴቶች ሥፍራ ከተመቻቸው አጋዥ ካገኙ ምን ቁም ነገር አላቸው አለው፤ ተርቢኖስ በፍጹም በምትሉት አልስማማም ሚስቴን አልጠረጥራትም አላቸው::

ጓደኛው በድጋሚ ተርቢኖስን ጠየቀው:: ያንተ ሚስት ከማን ትበልጣለችና ነው ይህን መልስ የምት መልስልን? አሁን እኔ ሄጄ ከሚስትህ ጋር ለምዳኝ ለምጃት እርሷም ወዳኝ እኔም ወድጃት ብመለስ ምን ትቀጣለህ? አለው:: ተርቢኖስም ሚስቱን ተማምኖ ይህን ብታደርግ ይህን ያህል ዓመት የደከምኩበትን፣ የወጣሁበትን፣ የወረድኩበትን፣ የለፋሁበትን ሀብት ከነትርፉ እኔ እወስደዋለሁ ብሎ ተርቢኖስ ተናገረ:: ይሁን ተባብለው ተወራርደው ተለያዩ::

ያም ተንኮለኛ ነጋዴ በተወራረዱት ቃል መሠረት ወደ ተርቢኖስ ቤት ሄዶ በአጠገብ ያሉትን ሰዎች ከተርቢኖስ ሚስት አገናኙኝ አላቸው:: እሷንስ እንኳን ሰው ፀሐይ አይቷት አያውቅም አሉት:: ሠራተኛዋን ጥሩልኝ አላቸው፣ እሷንስ እንጠራልሃለን ብለው ጠሩለት:: ለእሌኒ መልእክት ሰደደላት:: «ዜናሽን ሰምቶ ከሩቅ ሀገር የመጣ ሰው ልይሽ ይላል ብለሽ ለእመቤትሽ ንገሪልኝ» አላት:: ሠራተኛዋም «ኧረ ግብሯም አይደለ» ብላ መለሰችለት:: «ግድ የለሽም ንገሪልኝ» አላት:: ገብታ ብትነግራት ፊት ነሳቻት:: ተመልሳ «ወንድሜ አልሆነልኝም» አለችው::

ያም ተንኮለኛ ነጋዴ ሠራተኛዋን በድጋሚ ላካት፤ «ብዙ ገንዘብ እሰጥሻለሁ» ይላል ብለሽ ንገሪልኝ አላት:: ይህንንም ገብታ ነገረቻት:: እሌኒም በንግግሯ አዘነች:: እኔን የተርቢኖስን ሚስት በገንዘብ የሚያታልለኝ ብላ፤ ትሰፋ ነበር ቢሉ በወስፌ ትፈትል ነበር ቢሉ በእንዝርት መታቻት:: ደማች:: ደሟን እያዘራች ወጥታ ሄዳ «አይሆንም ስልህ አስመታኸኝ፤ አሁንም አልሆነልህምና ሂድ» አለችው:: ነጋዴውም እንደምን እሆናለሁ ብሎ ሠራተኛዋን የሚያታልልበትን ዘዴ ዐቀደና «ይህን ገንዘብ ላንቺ ልስጥሽ? ሌላ ሰው የማያውቀው ተርቢኖስና እሌኒ ብቻ የሚያውቁትን ዕቃ ካለ እንደምንም ብለሽ ፈልገሽ አምጪልኝ» አላት:: «ይህንንስ አደርግልሃለሁ» አለችው::

ሠራተኛዋም ቃል ገባችለት፣ «እሌኒና ተርቢኖስ ብቻ የሚያውቁትን የእመቤቴ ዕንቁ /ሀብል/ አለ:: ያንን አመጣልሃለሁ» አለችው:: ነጋዴውንም መከረችው «በከተማ ውስጥ እየዞርክ ነጋዴዎች መጡ፣ የብስ ረገጡ እያልክ አውራ፤ ከዚያም ተመልሰህ ና» አለችው:: እርሱም እንደ ተመከረው የነጋዴዎቹን መምጣት በከተማይቱ እንዳወራ የነጋዴ ዎቹ ቤተሰቦች፣ ነጋዴዎቹን ለመቀበል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ:: ሠራተኛዋ ወደ እሌኒ ገብታ «እመቤቴ ነጋዴዎች መጡ፤ የብስ ረገጡ እየተባለ ይወራል:: ባለቤትዎ በሰላም ስለ መጡ ይዘገጃጁ:: ገላዎትን ይታጠቡ፣ ሽቶ ተቀቡ» አለች:: እሌኒም «ይህ ሁሉ ቀድሞ የምታደርጊልኝ አንቺ አልነበርሽም?» ብላት ገላዋን ልትታጠብ ወደ እልፍኝ ገባች::

ገላዋን ስትታጠብ ከደረቷ ላይ እንደ ጉሽ ጠጉር /ሐር/ ባለ ዕንቁ አስሮላት ነበር:: ባልና ሚስት ተድላ ደስታ ሲያደርጉ የሚተያዩበት ነው:: እሌኒም እውነት መስሏት ሰውነቷን ስትታጠብ የአንገቷን ዕንቁ /ሀብል/ ረስታው ገባች:: ሠራተኛዋም ያን አንሥታ ወስዳ ለነጋዴው በተቃጠሩበት ቦታ ሰጠችው:: ነጋዴውም ዕቅዱ ተሳካለት:: የሚፈልገውን አገኘ:: የልቡ ስለ ደረሰለት ለውለታዋ /ሰርቃ አምጥታ ስለ ሰጠችው/ ገንዘብ ሰጥቷት፣ ደስ እያለው ወደ ጓደኞቹ ሄደ:: ተርቢኖስም «እንደምን ሆነህ መጣህ?» አለው፤ «ሚስትህ ለምዳኝ ለምጃት፤ ወዳኝ ወድጃት መጣሁ» አለው:: «ስትዋሽ ነው እንጂ እሷስ አታደርገውም፣ አምናታለሁ» አለው:: ያ ተንኮለኛ ነጋዴም «ኧረ ይሄ ሞኝ፤ ሴት አምኖ» እያለ ያፌዝበት ጀመር፤ የወሰደውን ዕንቁ /ሀብል/ አውጥቶ አሳይቶ «ለዚህ ምን ምላሽ አለህ? ይህ ዕንቁ የሚስትህ አይደለም?» ብሎ ሰጠው:: ተርቢኖስም ደነገጠ፣ የሚናገረውን አጣ::





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ቢሆን ነው እንጂ፣ ካልሆነማ ይህን ማን ይሰጠው ነበር? ብሎ ልመርምር አላለም፤ ተረታሁ ብሎ በተጨራረዱት መሠረት ዕለቱኑ ንብረቱን፣ ሀብቱን ሁሉ ለዚያ ተንኮለኛ ነጋዴ አስረክቦ ባዶ እጁን ወደ ቤቱ እያዘነ፣ እየተበሳጨ ሄደ::

እሌኒ ባለቤቷን በናፍቆት፣ በታማኝነት ስትጠብቅ ነው የኖረች ው:: ነገር ግን በተርቢኖስ ያልተለመደ ኀዘንና ብስጭት ግራ ተጋብታ «ወንድሜ ሆይ÷ ምን ሆነሃል? ለወትሮው እንኳን ይህን ያህል ዘመን ተለያይተን ቀርቶ፤ ለጥቂት ቀናትም ቢሆን እንኳን ተለያይተን ስንገናኝ እንነፋፈቃለን:: አሁን ግን ከመጣህ ጊዜ ጀምሮ አዝነህ ተክዘህ አይሃለሁ» ብላ ደንግጣ ጠየቀችው:: «ቀድሞ ወጥተህ ስትገባ ብዙ ጨዋታ ትጫወት ነበር? ባልንጀሮችህ ተድላ ሥጋ ሲያደርጉ፣ ተድላ ሥጋ አታደርግ፤ ሲጫወቱ አትጫወት ምን ሆነሃል?» አለችው:: እርሱም «እነዚህ ቢጫወቱ ተድላ ሥጋ ቢያደርጉ ከንንብረታቸው፣ ከነወረታቸው ገብተው ነው:: እኔ ግን አራት ዓመት የደከምኩበትን ወረቴ፣ ከባሕር ሰጥሞብኝ ማዕበል አጠፋብኝ:: ምነው አላዝን? እኔ ያላዘንኩ ማን ይዘን?» አላት:: የተማረች ናትና ትመክረው ጀመር:: «እግዚአብሔር ወሃበ እግዚአብሔር ነስዐ» ይላል:: «ያየነውን ቢነሳን ያላየነውን ይሰጠናል:: አንተ እንኳን ደኅና መጣህ እንጂ ሀብቱ ውሎ አድሮ ይመጣል» እያለች አጽናናችው:: «ለአንተ ኀምሳ፣ ስድሳ ዘመድ ቢኖርህ ከነዚያ ተበድረህ እኔም ኀምሳ፣ ስድሳ ዘመዶች ቢኖሩኝ ከነዚያ ተበድረን ነግደህ ወጥተህ ወርደህ እንደ ቀድሟችን ሆነን እንኖራለን አትዘን» አለችው::

ተርቢኖስም የሆዱን በሆዱ ይዞ፤ «በኖርኩበት ሀገር ተዋርጄ፣ በሰጠሁበት ሀገር ለምኜ አልኖርም:: ወደ ሌላ ሀገር፤ ሰው ወደማያውቀኝ እሄዳለሁ፤ አንቺ ግን ሁሉ ይወድሻል፣ ሁሉ ያከብርሻል ከወደድሽው ጋር ኑሪ» ብሎ በነገር ይነካታል:: «እኔስ ብእሲ ወብእሲት አሐዱ አካል እሙንቱ ይላል:: እኔስ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ በደስታህ ጊዜ አብሬ ኖርኩ፤ በችግርህም ጊዜ አልለይህም:: የእኔንና የአንተን አንድነት ችግር አይፈታውም::» እርሱም «ከወደድሽማ መልካም ነው» ብሎ ቤታቸውን ጥለው ሄዱ:: በቁመቷ ልክ ሣጥን አስጠፍሮ በግመል ጭኖ ይዟት ሄደ:: በሀገራቸው ከየብሱ ባሕሩ፤ በየብስ ከሚሄዱት በባሕር የሚሄዱት፤ በእግር ከሚሄዱት በመርከብ የሚሄዱት ይበልጣልና ከታላቅ ባሕር ደረሱ፤ መርከብ ተከራይቶ በመርከብ ተጫኑ:: ከማዕከለ ባሕር ሲደርሱ መንፈስ ቅንዓት ተነሣበት፤ ይዞት የነበረውን የሚከነክነውን ምሥጢር አወጣው:: «እኅቴ ምነው? ሳምንሽ ከዳሽኝ፤ ስወድሽ ጠላሽኝ፤ ምን በድዬሽ ነው?» አላት:: እሌኒም ደንግጣ «አንተን ባለቤቴን እንዴት እጠላሃለሁ? አልጠላሁህም፣ አልከዳሁህም፤ አንተን ከድቼ ማንን ላምን? አን ተንስ ጠልቼ ማንን ልወድ?» አለ ችው::

ቢዚህን ጊዜ ከዚያ ተንኮለኛ ነጋዴ የተቀበለውን ደብቆ የያዘውን ዕንቁ አውጥቶ አሳይቷት «ይህን ማን ሰጠው?» አላት:: ያጋጠመውን ሁሉ ዘርዝሮ ነገራት:: እሌኒም ያልጠበቀችው ነገር ስለተፈጸመ አዝና እውነተኛውን ታሪክ ነገረችው፤ «ይህን ታገልግልሽ ብለህ የሰጠኸኝ ሠራተኛችን ነገሩን መጥታ ነገረችኝ፤ አይሆንም አልኳት፣ ገላዬን ስታጠብ ረስቼው ገብቼ ነበር:: እሷ ወስዳ ሰጥታው እንደሆነ ነው እንጂ እኔስ ሰውዬውን፣ ስንኳን ግብሩን መልኩንም አላየሁትም» አለችው:: ተርቢኖስ ግን የምትለውን አላመነም:: «አድርገሽም እንደሆነ ሥራሽ ያጥፋሽ:: አላደረግሽም እንደሆን ሥራሽ ያውጣሽ፤» ብሎ አንሥቶ ከባሕር ጣላት:: ማዕበለ ሞገድ እያማታ ወስዶ በበራንጥያ በኩል አውጥቶ ከዳር ጣላት:: በዚያ ወደብ አካባቢ የመክስምያኖስ ቄሣር ሆኖ ምዕራብ ሮምን ያስተዳድር የነበረው የበራንጥያ ንጉሥ ቁንስጣ /ኮንስታንዲዮስ/ ይባል ነበር::

ዓሣ ለማስገር፣ ዋና ለመዋኘት አንድም ቀረጥ ለማስቀረጥ አንድም የወደቀ የነጋድያን ገንዘብ ማዕበል ሞገድ እያመጣ ከዚያ ይጥለው ነበር፤ ያን እያነሣ መጠቀም ለምዶ ነበርና ከወንዝ ወርዶ ሳለ አሻግሮ አይቶ ማዕበል የወሰደው የነጋድያን ወርቅ ይሆናል አምጡት ብሎ አስመጥቶ ቢከፍተው እንደ ፀሐይ ስታበራ አገኛት::

ያላዋቂ አነጋገር «የክርስቲያን እመቤት ማርያም» የምትባል አለች አንቺ ነሽ? አላት:: እኔስ እንኳን፤ ቀን የጣለኝ ችግረኛ፣ ሆድ የባሰኝ ነኝ እንጂ የማርያምንስ የእግሯን እጣቢም አልሆንም አለችው:: አሕዛብ ለፈቲው እጅግ አይቸኩሉምና መንፈቅ፤ የውስጥ ገላዋን የሚያጠራ ምግብ እየመገበ፤ የአፍዓ ገላዋን የሚያጠራ ሽቱ እየቀባ አቆይቶ ከመንፈቅ በኋላ ደረሰባት:: እሌኒም ጸነሰች:: በ258 ዓ.ም ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ተወለደ:: በአባቱ ቁንስጣ፣ ቆስጠንጢኖስ ተብሏል:: አንድም ሐመልማል ማለት ነው፤ እናቱ ውኃ ዳር ስለ ተገኘች::

የቆስጠንጢኖስ አባቱ አረማዊ፣ እናቱ አይሁዳዊት ናቸውና አንድም ኅብረ ጥበቡ ብዙ ነውና እስከ አራት ዓመት ድረስ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር እያስተማረች አሳድጋዋለች:: ቁንስጣ አረማዊ በመሆኑ እንዳይቆጣቸው ብላ የልጅነት ጥምቀት ግን አላስጠመቀችውም::

ዲዮቅልጥያኖስ «አብያተ ጣዖታት ይትረሃዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትአጸዋ፤ አብያተ ጣዖታት ይከፈቱ፤ አብያተ ክርስቲያናት ይዘጉ ÷ ይጥፉ» ብሎ ዐዋጅ ነገረ:: ምእመናንም ሰውነታቸው እንደ ላም ታረደ፤ ሥጋቸው እንደ ሽንኩርት ተቀረደደ፣ ደማቸው እንደ ውኃ ወረደ፣ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ መጻሕፍት ተቆነጻጸሉ፣ አብያተ ክርስቲያናት ተተኮሱ፣ መጻሕፍት ፈለሱ፣ ምእመናን የሚሞቱ ሞቱ:: የሚሰደዱም ተሰደዱ:: ዲዮቅልጥያኖስ ከሞተ በኋላ ክርስቲያኖች የቆስጠንጢኖስን ፍርድ ማወቁን፣ ድኻ መጠበቁን እየሰሙ ለአንተ እንገዛለን፤ መጥተህ እርዳን ሲሉት ያንን እያየ ያዝን ነበር:: በጸፍጸፈ ሰማይ የብርሃን መስቀል ተቀርጾ «በዝ ትእምርተ መስቀል ትመውዕ ፀረከ ወጸላእተከ፤ በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ድል ታደርጋለህ» የሚል አየ:: በ312 ዓ.ም ከጠላቱ ከማክሴንዲዮስ /መክስምያኖስ/ ጋር ለመዋጋት ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብሎ በዘመቻ እንደ ተሰለፉ በራእይ በሰማይ «በዚህ መስቀል ምልክት ጠላትህን ድል ታደርጋለህ» የሚል መስቀለኛ ጽሑፍ ስላየ ለሠራዊቱ የመስቀል ምልክት በመሣሪያቸው፣ በፈረሱ አንገት፣ በጦሩ አንደበት፣ በጋሻው እንብርት ላይ ትእምርተ መስቀል እንዲያደርጉ አዘዘ:: ከዚያም ጦርነት ቢገጥም ድል አድርጎ ሮምን ጠቅልሎ ያዘ::

በዚህ ጊዜ ምእመናን፤ የጳሕሉን፣ የጽዋውን፣ የመስቀሉን ስባሪ ይዘው መስቀል ኃይልነ፣ መስቀል ጽንዕነ፣ መስቀል ቤዛነ፣ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ እያሉ ተቀብለውታል:: ቀድሞ እናቱ የነገረችው፣ ኋላም ምእመናን የላኩለት በጸፍጸፈ ሰማይ ተቀርጾ ያየው ከድል በኋላም ምእመናኑ ይዘው የተቀበሉት ተመሳስሎ ቢያገኘው አመንኩ ብሎ የኒቆሜድያ ኤጲስ ቆጶስ አውሳብዮስ አጥምቆታል:: ከዚህ በኋላ ሰኔ 10 ቀን «አብያተ ክርስቲያናት ይትረሃዋ አብያተ ጣዖታት ይትአጸዋ» ብሎ ዐዋጁን በዐዋጅ መለሰው::





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ቤተ ክርስቲያን ከ300 የመከራና የስደት ዓመታት በኋላ እረፍት ያገኘችው በታላቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ነው:: ለአርባ ዓመታት ያህል ከአራት ተከፍላ ትገዛ የነበረችው የሮም ግዛት ባንድ ቆስጠንጢኖስ ሥልጣን ሥር ሆነች:: በክርስቲያኖች ላይ ይፈጸም የነበረው ግፍ ቀነሰ:: ለቤተ ክርስቲያን ያስተዳደርና ትምህርቷን የማስፋፋት ነጻነት ሰጣት:: ቆስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን ከሰጣቸው መብቶች ዋና ዋናዎቹ:–

- በ315 እና በ316 በወጣው ሕግ ቤተ ክርስቲያን ከግብር ነጻ ናት
- ከመንግሥት ገቢ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነ ድርሻ አላት
- ዕለተ እሑድ የክርስቲያኖች የበዓል ቀን እንድትሆን
- ንብረቴን ለቤተ ክርስቲያን አወርሳለሁ የሚል ምእመን ቢኖር ቤተ ክርስቲያን ኑዛዜ የመቀበል፣ ውርስ የመውረስ መብት አላት
- የክርስትና ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን የሚሉት ናቸው::
- ቆስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ውለታ ውሏል:: ቤተ ክርስቲያንም ስለ ብዙ ውለታው ስታስታውሰው ትኖራለች::

ቅድስት እሌኒ የጌታችን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት በ327 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች:: ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ ከሞተ በኋላ በመስቀሉ እየታሹ በሽተኞች ሁሉ ይፈወሱ ነበር:: ክርስቶስን ጠልተው የገደሉ ሰዎች በመስቀል የሚታየውን፣ የሚሠራውን ተአምር እንደ ጥቃት መስሏቸው በቆሻሻ ማፍሰሻ ቦታ ጣሉት:: ከጊዜ ብዛት የተነሣ በሙሉ የከተማው ሕዝብ የሚጥለው ቆሻሻ እንደ ኮረብታ ሆኖ ቆየ:: ከ300 ዓመት ያላነሰ የቆሻሻ መጣያ ሆኖ ሲኖር ክርስቲያኖች እየተጠናከሩ ሄዱ:: በዚህ ምክንያት የንጉሡ ቆስጠንጢኖስ እናት ቅድስት እሌኒ በ327 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ተሻግራ ወጥታለች፣ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ስትጠይቅ ከጊዜው ብዛት የተነሣ የሚነግራት አላገኘችም:: በኋላም ኪራኮስ የተባለ አረጋዊ «አባቶቻችን እንደ ነገሩን ከሆነ ከእነዚህ ኮረብታዎች በአንዱ ነው:: ግን የትኛው እንደሆነ አላውቅም» በማለት ከኢየሩሳሌም ወጣ ብለው ያሉትን ኮረብታዎች አሳያት:: ደመራ አስደምራ ዕጣን አስጨምራ ብዙ ጸሎትና ምህላ ተደርጐ መስከረም 16 ቀን አስለኮሰችው:: የደመራው ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ መስቀሉ ካለበት ኮረብታ ላይ እንደ ቀስተ ደመና አመለከተ::

ንግሥት እሌኒም በዚህ ምልክት መስቀሉ ያለበትን ቦታ ዐውቃ መስከረም 17 ቁፋሮ አስጀመረች:: በእግዚአብሔር ቸርነት መጋቢት 10 ቀን ከተቀበረበት ወጣ:: የጌታችንም መስቀል በወጣ ጊዜ ብዙ ተአምራት አድርጓል:: በቁ ፋሮ ከወጡት ሦስት መስቀሎች ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት የትኛው መስቀል እንደ ሆነ ለማወቅ አንዱንም መስቀል አምጥተው በሞተው ሰው ላይ አኖሩት፤ አልተነሣም:: ደግሞ ሌላውን መስቀል አምጥተው በሙቱ ላይ አኖሩ አሁንም አልተነሣም:: ከዚህ በኋላ ሦስተኛዋን መስቀል አምጥተው በሙቱ ላይ አደረጉት፣ ያን ጊዜ የሞተው ሰው ተነሣ:: ቅድስት እሌኒም የክርስቶስ መስቀል እንደ ሆነ ዐውቃ ሰገደችለት:: የክርስቲያን ወገኖችም ሁሉ ሰገዱለት::

ንግሥት እሌኒም መስቀሉን በክብር አስይዛ በጐልጐታ ቤተ መቅደስ አሠርታ በዚያ አስቀመጠችው:: ለዚህ ትልቅ ዕድል የበቃችው ቅድስት እሌኒም መስቀሉን ባወጣች በዓመቱ ግንቦት 9 ቀን 328 ዓ.ም በ80 ዓመቷ ዐረፈች:: ልጇ ታላቁ ቆስጠንጢኖስም በ337 ዓ.ም ግንቦት 22 ቀን የጰራቅሊጦስ ዕለት እሑድ በ54 ዓመቱ የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን በያዘ በ31 ዓመቱ ዐረፈ:: እናትና ልጅ በሠሩት ክርስቲያናዊና ሐዋርያዊ ተግባር ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ስታስታውሳቸው ትኖራለች::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት እሌኒ መስቀሉን በማውጣት ደመራ አስደምራ ቁፋሮ ያስጀመረችበት ዕለት መስከረም 16 ቀን በየዓመቱ በታላቅ ድምቀት በመላው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በድምቀት ይከበራል:: እግዚአብሔር ንጹሐንን አይጥላቸውም ክፉዎች፣ ተንኮለኞችን ግን በተንኮላቸው ይይዛቸዋል:: ሥራሽ ያውጣሽ ተብላ በባሏ ወደ ባሕር የተጣለችው ቅድስት እሌኒ ንጽሕናዋ፣ ቅድስናዋ፣ ታማኝነቷ አይሁድ የቀበሩትን መስቀል ለማውጣት አበቃት::

*የቅድስት እሌኒ በረከቷ አይለየን፣ ፈጣሪያችን ከመስቀሉ በረከት ያድለን:: አሜን::*

## የኑፋቄው መሻ ዙር /ከገጽ ፲፯ የዞረ/

### ጉባኤ ዘጎንደር ቀዳማዊ

የሱስንዮስ የዘጠኝ ዓመት ጦርነት ብዙ ሰዎች እምነታቸውን ለውጠው የካቶሊክን እምነት ተቀብለው ነበር:: ብዙዎቹ የካቶሊክ እምነት ተከታይነታቸውን ደብቀው እስከ ጻድቁ ዮሐንስ ድረስ ሊቆዩ ችለዋል አንዳንዶቹ ደግሞ ሱስንዮስ ከሥ ልጣን እንደ ወረደ የፋሲል ዘመን በይፋ የካቶሊክ እመነት ተከታዮች መሆናቸውን ራሳቸው ስለተናገሩ ካሉበት ደብር እንዲባረሩ ተደርገዋል:: በዚሁ ምክንያት ከአዘዞ ተክለ ሃይማኖትና ከሌሎችም የጎንደር አካ ባቢ አድባራት የተባረሩ ካህናት ብዙ ናቸው::

የሱስንዮስ የልጅ ልጅ አእላፍ ሰገድ ዮሐንስ /ጻድቁ ዮሐንስ/ በነገሠ በሁለተኛው ፖመቱ የካቶሊክን እምነት ስለ ተቀበሉ ኢትዮጵያውያን ጎንደር ላይ ጉባኤ ከፈተ ጉባአው በሚያዝያ ወር 1661 ዓ.ም. ነው የተደረገው ይህም ጉባኤ የፓርቱጋል ወታደሮች ቤተሰቦች የኾኑ ምዕራባውያን አንድም ሳይቀሩ ከኢትዮጵያ እንዲውጡ ወሰነ::

በሃ ክርስቶስ የተባለ ካህን ደግሞ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ሆኖ ስለተገኘ ንጉሡ የገዳማትንና የአድባራትን ካህናት ጠርቶ ጉባኤ ከፈተ:: የጉባኤው ተካፋዮች ክርስቶስ ከተዋሕዶ በኋላ አንድ ባሕርይ እንጂ ሁለት ባሕር አይደለም በማለት ማስረጃ እያቀረቡ አስረዱ:: እርሱ ግን በማስረጃው፣ በምክሩና በተግሣጹ ለመመለስ ፈቃደኛ አልኾነም:: ስለ ሆነም «አሪንጎ» ወደ ተባለው ቦታ ተወስዶ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ::

ጉባኤ ዘጎንደር ቀዳማዊ ጉባኤ በዐፄ ዮሐንስ አንደኛ ወይም ጻድቁ ዮሐንስ /አእላፍ ሰገድ/ ዘመነ መንግሥት /1667–82 እ.አ.አ/፣ በአቡነ ሲኖዳ ዘመነ ጵጵስና /1671– 1685 እ.አ.አ/ በእጨጌ አባ ቃለ ዐዋዲ ጊዜ በ1681 ጥቅምት ወር በጎንደር የተካሄደ ጉባኤ ነው:: ዐፄ ዮሐንስ እምነታቸው ቅብዐት በመሆኑ ለእነርሱ ያደሉ ስለ ነበር በርሳቸው ዘመነ መንግሥት የቅብዐት ልጆች እንደ ልባቸው ኖረዋል ማለትም በንጉሡና በቤተ መንግሥታቸው ተሰሚነት (Political upper hand) ነበራቸው ይባላል:: በሌላ በኩል በዘመኑ የጎጃም ቅባቶች በጣም በዝተው ስለ ተገኙ ሕዝቡን አሳምነውና አስተባብረው ያስገለብጡናል በሚል አንዳንድ ነገሥታት በቅባቶች ይመሩ ነበር፤ የጻድቁ ዮሐንስ ቅባቶችን መደገፍና የቅባት ተከታይ መሆን ከዚሁ የተለየ ላይሆን ይችላል:: ከአቡነ ሲኖዳ በፊት በጵጵስናው ሥፍራ የነበሩት አቡነ ክርስቶዶሉ ሁለተኛ /1663–1671 እ.አ.አ በመንበረ ጵጵስናው የነበሩ/ ወደ ግብጽ ተመልሰው የተላኩት ንጉሡ የሚደግፉትን የቅብዐት እምነት ስላልወደዱላቸው ነው::

*ይቆየን*





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «የግእዝ ሥነ ጽሑፍ እኛ "እኛ" የሆንበት፣ እኛነታችን የታወቀበት መለያችን ነው።»

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ

ኢትዮጵያን የሚመለከቱ የተለያዩ ዐውደ ጥናቶችና ጉባኤያት በየጊዜው በተለያዩ ሀገራት ይካሄዳሉ። ከእነዚህም ውስጥ በየአራት ዓመቱ የሚከናወነው «ዓለም ዐቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ» (International Conference of Ethiopian Studies) አንዱ ነው። በዚህ ዓለም አቀፍ ጥናት በኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባሕልና እምነት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ የተለያዩ ጥናቶች ከዓለም ዙሪያ በሚሰባሰቡ ምሁራን ቀርበው ውይይት ይደረግባቸዋል።

በዚህ መሠረት 15ኛው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ ዘንድሮ ከሐምሌ 12–16 ቀን 1995 ዓ.ም በሀገረ ጀርመን ሐምቡርግ ከተማ ተካሂዶ ነበር። ምንም እንኳን በመዠመሪያዎቹ የጥናቱ ዘመናት የሚቀርቡትን ባያክልም በዘንድሮውም ዐውደ ጥናት በተለይ "Religion" በሚለው ምድብ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶች ለውይይት ቀርበው ነበር። የቤተ ክርስቲያኗ ነቅዕ የሌለው ትምህርት፣ ሥርዓትና ትውፊት ወዘተ በሚገባ የሚያቀርቡ በርካታ ጥናቶች የመኖራቸወን ያህል ካለ ግብሯ ግብር፣ ካለ ስሟ ስም ሰጥተው የሚያብጠለጥኗት ጥቂት ጥናቶችም አልታጡም።

በዘንድሮው ዐውደ ጥናት ዲ/ን መርሻ አለኸኝ በቦታው ተገኝቶ በጉባኤው ላይ ተሳትፎ ነበር። እግረ መንገዱንም ካነጋገራቸው የጉባኤው ተሳታፊ ምሁራን መካከል የኦርየንታል ጥናት (Oriental Studies) ተብሎ በሚታወቀው የሥነ ጽሑፍ የጥናት ዘርፍ አብነት /ተጠያቂ/ የሆኑት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ አንዱ ናቸው። ፕሮፌሰር ጌታቸው ከጥናት ዘርፉ አንዱና ዋናው በሆነው በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ዙሪያ ብዙዎችን ወደ ዘርፉ እንዲሳቡ ያደረጉ በርካታ ሥራዎችን አሳትመዋል። ከእነዚህም ውስጥ ስምንት ያህል ቅጽ ያለውና በግእዝ የተጻፉ መጻሕፍትን ዝርዝር የሚያስተዋውቀው <u>A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, [EMML], Addis Ababa & for the Hill Monastic Manuscripts Library, [HMML], Collegeville</u>. አንዱና ዋናው ነው። እኚህ አንጋፋ ምሁር በዚህ ዐቢይ ሥራቸው አማካይነት በርካታ ገድላትንና የነገረ ሃይማት መጻሕፍትን አገላብጠዋል። ሌሎች ሊያውቋቸው ይገባል የሚሏቸውንም ከጥልቅ ትንታኔ ጋር ወደ እንግሊዝኛ እየተረጐሙ አሳትመዋል። አሁንም በማሳተም ላይ ይገኛሉ። ፕሮፌሰር ጌታቸው ዲ/ን መርሻ የቀረበላቸውን ግብዣ ጥያቄ ለመመለስ ፈቃዳቸውን ገልጸው ውይይታቸውን ቢጀምሩም ምሁሩ በኢትዮጵያ ጥናት ከደረሱበት ከፍተኛ ደረጃ የተነሣ የጉባኤው ታዳሚ በመላ በሚያደርጉበት ጣልቃ ገብ ወይይትና ሰላምታ ሰንቋቸው ለሄዳቸው ጥያቄዎች ሙሉ መልስ ሊያገኝ አልቻለም። ለሦስት ተከታታይ ቀናት ያህል ተወያይቶ ቃለ መጠይቁን ሊያጠናቅቅ ቢሞክርም ከላይ በተገለጠው ምክንያት የተነሣ አልቻለም። ለማንኛውም ፕሮፌሰር ጌታቸው ላደረጉለት ትብብር በአንባብያን ስም እያመሰገንን ባላቸው ጊዜ የተካሄደውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።



ሐመር፡- የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ምንድን ነው?

ፕሮፌሰር ጌታቸው፡- አንድ ሲልቨር ማን የሚባል (እንግሊዛዊ ይመስለኛል) ሲጽፍ "ምዕራባውያን ቅኝ አገር የሚይዙት ወንጌልን ልንሰብክ ነው፣ የሥልጣኔን ብርሃን ለማብራት ነው፣ ሥነ ጽሑፍን ለመስጠት ነው፣ የዕውቀት ብርሃን እንዲበራላቸው ለማድረግ ነው፤ በእንግሊዝኛው «civilizing mission» (ዘመናዊ የማድረግ ተልእኮ) እያሉ ነው። ይህን በማለትም ገንዘብ ከተለያዩ አካላት ያገኛሉ። ነገር ግን ይህንን ሁሉ ምክንያት ይዘው ኢትዮጵያ ሲደርሱ ተቸገሩ። ውጤታማም አልሆኑም። ምክንያቱም ወንጌልን እንሰበክ እንዳይሉ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል ወንጌልን ተቀብለው ተምረውና አምነውበት ክርስቶስን ተቀብለዋል፤ ወንጌሉንም ያስተምራሉ፤ ሥነ ጽሑፍን እንስጣችሁ እንዳይሉ ጥንታዊ ፊደልና በወግ ተሰናድቶ የዳበረ፣ ማንንም የሚስብ ሥነ ጽሑፍ አላቸው፤ የዕውቀት ብርሃን እናብራላችሁ እንዳይሉ ኢትዮጵያውያን ከእነሱ አልፎ ለዓለም የሚጠቅም ዕውቀት በውስጣቸው አለ" ብሏል። ስለዚህ (እኛ ኢትዮጵያውያን ልብ አላ ልነውም እንጂ) የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ባለቤት መሆናችን እንደ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በቅኝ ግዛት እንዳንወረር ካደረጉን ነገሮች አንዱና ዋናው ኃይል ነው። ዛሬ አደጉ ከሚባሉት ሀገሮች ጋር የሚያወዳድረን ፊደልም ሆነ ሥነ ጽሑፍ አለን። ይህ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ ከሌሎች ሦስተኛ ዓለም ሀገሮች ፊንጠር ብለን እንድንገኝ ያደረገን ነው።

የላቲኑ ሥነ ጽሑፍ በተገኘበት ቦታ የግእዙም ተጽፎ ይገኛል። የሶሪያው ሥነ ጽሑፍ ተጽፎ በሚገኝበት ቦታ የግእዙም ሥነ ጽሑፍ ተደርድሮ ይገኛል። የግሪኩ ሥነ ጽሑፍ ባለበት የግእዙም አለ።

በዚህ ሁሉ የተነሣ የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ራሳችንን በራሳችን እንድንፈጥር፣ ከሌላው ጋር በእኩልነት እንድንሰለፍ ያደረገን ቅርስ ነው። የግእዝ ሥነ ጽሑፍ እኛ "እኛ"



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሆንበት፣ እኛነታችን የታወቀበት መለያችን ነው።

*ሐመር፡- ከታወቀው ለመጀመር የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ሰፊና ለጥናትና ምርምር የሚጋብዝ ነው። ይሁን እንጂ ብዙ ኢትዮጵያውያን አንጋፋም ይሁኑ ወጣት ምሁራን ወደ ዘርፉ ሲሳቡ አናይም። ለምን ይመስለዎታል?*

*ፕሮፌሰር ጌታቸው፡-* እኔ እንደ ሚመስለኝ ለዚህ ችግር መከሰት ምክንያቱ የዘመናዊው ትምህርት ወደ ሀገራችን በገባ ጊዜ ካለፈው የኢትዮጵያ የትምህርት ጥበብ ጋር ሳይዛመድ በመሆኑ ነው። ሲወርድ ሲወራረድ የመጣው የሀገራችን ትምህርት ሙሉ በሙሉ ወደ ጎን ተብሎ ነው ዘመናዊው ትምህርት የገባው። በሌላው ሀገር የሆነ እንደሆነ ዘመ ናዊው ትምህርት ከጥንት ሲያያዝ ከመጣው የሀገራቸው ትምህርት ጋራ እየተወራረሰና እያደገ መጥቶ ነው እዚህ የደረሰው። በእኛ ሀገር ግን ለረጅም ዘመናት ሲያገለግል የነበረውን ትምህርት ወደ ጎን ብለን በቦታው የምዕራባውያኑን ትምህርት ነው ያስገባ ነው። በዚህ የተነሣ እንግዲህ የግእዝ ቋንቋ በውስጡ ከያዘው ትምህርት ጋር ቆመ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ዳዊት እንኳ ሳንደግም ሆነ ወደ ዘመናዊው ትምህርት የምንገባው። ስለዚህ ከግእዝ ጋር ተለያየን። ሌላው ቢቀር የግእዝን ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት በሥርዓተ ትምህርታችን ማስገባት ነበረብን። ግን አላደረግንም። ምዕራባውያን የግእዝን ቋንቋ ተምረው ነው ሥነ ጽሑፉን እያዳበሩ እየነገሩን ከእነሱ ጽሑፍ ላይ የምናነበው። የሀገራቸውን ቋንቋ ይማራሉ፣ የጎረቤት ሀገሮችን ቋንቋ ይማራሉ። ከዚያ በኋላ ነው ውቅያኖስ አቋርጠው መጥተው ግእዝን የሚማሩት። እኛ ግን አይደለም የጎረቤቶቻችንን ልናጠና የራሳችንንም ለማጥናት የተሳነን ይመስለኛል።

በእውነቱ በጥንቱ የትምህርት ይት በሃል ጀምረን ወደ ዘመናዊው መም ጣት እንኳን ቢያቅተን ግእዝን እንደ ቋንቋ አድርገን መማር እንችል ነበረ። እንግዲህ ለዚህ ቤተ ክህነቱም ይሁን ቤተ መንግሥቱ የየራሳቸውን ጥረት አድርገው ቢሆን ኖሮ ይህ ክፍተት አይፈጠርም ነበር።

*ሐመር፡- ምን ማድረግ ይገባቸው ነበር?*

*ፕሮፌሰር ጌታቸው፡-* በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያናችን ቋንቋውንም ሆነ ሥነ ጽሑፉን ተከባክባ ያቆየች፣ በእነሱም የሀገርን ታሪክ፣ ትምህርት ወዘተ ስታ ሰናዳ የቆየች መሆኗ ሊዘነጋ አይገባም። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ባለውለታ ናት። ነገር ግን ይህ ለዘመናት ይዘሽውና ስታገለግይበት የነበረው ትምህርት ለሀገር ዕድገት አያስፈልግም ስትባል ያላትን ተቀባይነት በመጠቀም ምእመናን ልጆቻቸውን የግእዝን ቋንቋ እንዲያስተምሩ ዳዊት እንዲደግሙ ብታደርግ ኖሮ ጥሩ ነበር። መንግሥት ደግሞ እንደው እንደ መጣ ለዘመናዊው ትምህርት ሙሉ ቦታ ሰጥቶ ሕዝቡን ተማሩ ሲል ቢያንስ ጥንታዊው የሀገራችን ትምህ ርት የተወሰነ ቦታ እንዲይዝ፣ ዘመና ዊውንም ከጥንታዊው ጋር እንዲገናዘብ ቢያደርግ መልካም ነበር።

*ሐመር፡- ከላይ ላነሣነው ችግር የሚሰጡት መፍትሔ ካለ?*

*ፕሮፌሰር ጌታቸው ፡-* ይኸ ጉዳይ ማለትም የግእዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ብሔራዊ ጉዳይ ነው። ባሕልና ታሪክ ብሔራዊ አጀንዳ ነው። ስለዚህ መንግሥት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተከባካቢነትና አስፈጻሚነት ሀገርን ሲያገለግል ለነበረው የግእዝ ቋንቋ አሁን ባለው ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ቦታ እንዲያገኝና ትውልዱ ያንን ቋንቋ ተጠቅሞ የቀደመውን ታሪኩንና ባሕሉን እንዲሁም ዕውቀቱን እንዲመረምር ማድረግ አለበት። ምናልባት ይኸ አልሆን ካለ ትውልዱ ራሱ ቋንቋችንን አስተምሩን ብሎ መንግሥትን መጠየቅ አለበት። ወላጆችም ልጆቻችን ጥንታዊውን ቋንቋችንን ይማሩልን ብለው መጠየቅ አለባቸው። ይኸ ደግሞ የሁሉም ኢትዮጵያዊ መብት ነው። ስለዚህ እኛው ራሳችን ማኅበር አቋቁመንም ሆነ ሀገር አቀፍ እንቅስቃሴ አድርገን ልጆቻችን የግእዝን ቋንቋ እንዲማሩ ማድረግ አለብን። እኛም ለመማር ልንተጋ ይገባል።

ምዕራባውያን እኮ ግእዝን በአጭር ጊዜ ተምረው ነው መጻሕፍትን ሲያሳትሙ የምናገኛቸው። እነሱ በቀላሉ ያጠኑት ደግሞ ለእኛ የበለጠ ይቀላል። እኔ እንደተገነዘብኩት ግእዝ እስኪጀምሩት ነው እንጂ ከጀመሩት በኋላ በእጅጉ የሚስብ ነው። ትጉኃን አባቶቻችን ያሰናዱልን መዛግብተ ቃላት አሉ። የቋንቋውን መሠረታዊ መዋቅር ይዘን ስናበቃ በእነዚህ መዛግብተ ቃላት እየተጠቀምን ዕውቀታችንን ማስፋፋት ነው።

*ሐመር፡- እኛ እንደምንለው ሳይሆን አንዳንድ ሰዎች የግእዝ ሥነ ጽሑፍ የሚባል ነገር የለም ከሚል ይነሱና ምናልባት አለ እንኳን ቢሉ ጥቅም የለውም ይላሉ። በእነዚህ ነጥቦች ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?*

*ፕሮፌሰር ጌታቸው፡-* የግእዝ ሥነ ጽሑፍ የለም ማለት ምን ማለት ነው? መጻሕፍቱ የሉም ማለት ነው? ነው÷ በግእዝ የተጻፉ አይደሉም ማለት ነው? ምን ማለት ነው የግእዝ ሥነ ጽሑፍ የለም ማለት? ሥነ ጽሑፍ ማለት ምንም እንኳን ሰፋ ተደርጎ መበየን የሚቻል ቢሆንም በአጭሩ የተጻፈ ነገር ማለት ነው። የተጻፈው ነገር አይጠቅምም ማለት ሌላ ነገር ነው። ነገር ግን የእኛ ሥነ ጽሑፍ ለዘመናት የተገለገልንበት አሁንም እየተገለገልንበት ያለ ሥነ ጽሑፍ ነው። አንድን ሥነ ጽሑፍ በምናይበት ጊዜ ግጥም አለው፣ እኛም በሥነ ጽሑፋችን ውስጥ በወግ የተቀመረ ግጥም አለን። መልክአ መልክኡን፣ ሰላሙን ወዘተ እንጽፍበታለን። ቅኔው በራሱ ግሩም ግጥም ነው። በአንድ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሕይወት ታሪክ አለ። በእኛም ውስጥ የአባቶቻችን የሕይወት ታሪክ በወግ የተጻፈበት ገድል የተባለ የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ አለን። በዚህ ዓይነት ሌሎችም አሉ። ታዲያ እነዚህን የመሳሰሉ ሥነ ጽሑፎች ባሉበት ሁኔታ እንዴት ነው የግእዝ ሥነ ጽሑፍ የለም የሚባለው። ምናልባት ልብ ወለድን እንደ አንድ የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ በውስጡ አልያዘም የሚባል ከሆነ ሥነ ጽሑፋችን ጥንታዊ ስለሆነ የቅርብ ጊዜውን የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ አልያዘም። ልብ ወለድ እኮ እንኳን በእኛ በአውሮፓውያኑም የመጣው አሁን ከነገር በኋላ ነው። እሱን ስላልያዘ ሥነ ጽሑፍ አይደለም ማለት አላዋቂነት ነው።

መኖሩን አምነው ጥቅም የለውም ወደሚሉት ስመጣ ደግሞ እንደተባለው በተለይ ቀደም ባሉት ጊዜያት እኔም የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ጥቅም የለውም የሚሉ ሰዎች ያጋጥሙኛል። ይህንን ለማለት መጀመሪያ ወኔን አስተባብሮ በውስጡ ምን አለ ብሎ መርምሮ ማየት ይገባል። ይህ ባልሆነበት ሁናቴ እንዴት ነው ጥቅም የለውም የሚባለው። አንድ ተሸፍኖ ያለን ነገር ውስጡን ሳያዩ እኔ ይኸንን አልፈልገውም ብሎ መወርወር ተገቢ ነው እንዴ? አይደለም። ምናልባት ተጠንቅቆና ዘዴውን አውቆ መክፈት ይገባል። በዘዴ ከከፈቱ በኋላ ይጠቅመኛል፣ አይጠቅመኝም ብሎ መወሰንና መናገር ይቻላል። በጥንቃቄ ከፈት አድርገን ስናየው በግእዝ ውስጥ ታሪካችን ተመዝግቦ እናገኘዋለን። ሥልጣኔያችን ተጽፎ እናገኘዋለን፣ ፍልስፍናችን ተጽፎ እናገኘዋለን፣ ጥበባችን ተጽፎ እናገኘዋለን፤ ስለዚህ ይኸ ሁሉ ቢጠና ሰፊና ጥልቅ የጥናትና ምርምር ዘርፍ እንጂ እንዲሁ አይጠቅምም ብለን የምንተወው አይደለም።

*ሐመር፡- በነገራችን ላይ እነዚህ ሰዎች የግእዝን ሥነ ጽሑፍ ብቻ ሳይሆን ቋንቋውንም ሞቷል ይላሉ። ለመሆኑ የግእዝ ቋንቋ ሞቷል?*

*ፕሮፌሰር ጌታቸው፡-* /ከጥቂት ዝምታ በኋላ/ ግእዝ ሞቷል ማለት'ኮ ብቻውን አይሆንም። እንደዚህ ሲባል እየሰማሁ ብዙ ጊዜ አዝናለሁ። ግእዝ በፍጹም አልሞተም። በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሕብሮን ነው ያለው።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል»

/ዘዳ. 32 ÷ 7/



ዕድሜ ከመደበኛው ትምህርት ቤት ባላነሰ በርካታ ቁም ነገሮችን የሚማሩበት ሌላው ት/ቤት ነው:: አባቶቻችን በሕይወት ዘመናቸው ከመምህሮቻቸው ከመጻሕፍት፣ ከቀደምት አበው ዕውቀትን ሰንቀዋል፤ ጠግበዋል፤ ረስርሰዋል:: እኛ እንዲህ እንበላቸው እንጂ እነርሱ ተምረው እንዳልተማሩ የዕውቀት ምንጭ ሆነው ምንም እንደሌላቸው ይመስላሉ:: ጠጋ ብሎ ላዳመጣቸውና ጆሮውን ላዋሳቸው ከማያልቀውና ባሕር ከሆነ የዕውቀት ሀብታቸው እየጠለቀ ያስጎነጩታል፤ ያረኩታል:: የአእምሮአቸውን ስፉህነት – ጠሊቅነት ያሳዩታል::

በዚህ ጽሑፍ ተቀድቶ ስለማያልቀው የአባቶቻችን ዕውቀት ብዙ ልናቀርብላችሁ አይደለም፤ ነገር ግን ቀርባችሁ እንድታደምጧቸውና ጥበብን፣ ማስተዋልንና ዕውቀትን እንድትቀስሙላቸው ለመጋበዝ አንድም ለመጠቆም ያህል ብቻ ነው:: ለአሁኑ የትላንት ሕይወታቸውን የወጣትነት ዘመናቸውን በመጠኑ ያስቃኙን ዘንድ ሁለት አባቶችን መርጠናል:: እነዚህ አባቶቻችን ጥያቄያችንን በአባታዊ ትኅትና ተቀብለው ለዛሬዎቹ ወጣቶች ትምህርት የሚሆኑንን የወጣትነት ትጋታቸውንና ጽናታቸውን በሚያስገርም ሁኔታ እያስታወሱ ከዲ/ን ያሬድ ገ/መድኅንና ከተስፋዬ ሽብሩ ጋር ተወያይተዋል:: እንደሚከተለው ይቀርባል::

የመጀመሪያው ብፁዕ አቡነ ቶማስ የቅዱስ ሲኖዶስ አባልና የአዊና የመተከል ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ናቸው:: ብፁዕነታቸው ገና ፊደል ከቆጠሩበት የልጅነት ዕድሜአቸው ጀምሮ ዛሬ በከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እስካሉበት ድረስ የቤተ ክርስቲያንን ዕውቀት እንደ ምግብ ተመግበዋል፤ እንደ ውኃ ጠጥተዋል:: አሁንም እየተመገቡና እየጠጡ እንዲሁም ሕዝበ ክርስቲያኑን እየመገቡና እያጠጡ ነው:: ለተጠየቁት ከመመለስ በፊት በወግ ማዳመጥን በተግባር የሚያስተምሩት ብፁዕነታቸው ላቀረብንላቸው ጥያቄዎች በሙሉ ሊቅነታቸውን በሚመሰክር የረጋ አንደበት አጫውተውናል::

ብፁዕ አቡነ ቶማስ የተወለዱት መጋቢት 14 ቀን 1934 ዓ.ም ነው:: ብፁዕነታቸው ስለ ወጣትነት ጊዜያቸውና በምን ሁኔታ እንዳሳለፉት ጠይቀናቸው እንዲህ አሉን:: «የወጣትነት ጊዜዬን በቆሎ ተማሪ ቤት እየተማርኩ በእንተ ስማ ለማርያም እያልኩ በብዙ ቦታ እየተዘዋወርኩ ነበር የተማርኩት:: የዚያን ጊዜውን ሕይወት ሳስታውሰው ከምበላው የማድርበት፣ ጦሜን የማድርበት ጊዜ ይበልጥ ነበረ:: በትምህርቱ በኩል ግን ብዙ ዕውቀት ያገኘሁበት ጊዜ እንደነበር አስታውሳለሁ:: ወደ ታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ሄጄ እንጨት እየተሸከም ኩና እየፈለጥኩ፤ እየወጣሁ እየወረድኩ አባቶችን አገለግል ነበር:: በዚያን ወቅት በወር ስምንት ብር እየተከፈለኝ ነበር የምኖረው:: ታድያ ብሩ ሳይሆን እኔን የሚያስደስተኝ ከአባቶች የምናገኘው ትምህርትና በረከት ነበር::

የወጣትነት ዘመን ሁሉን ልያዝ ሁሉን ልጨብጥ የሚባልበት፣ ከማስተዋል ይልቅ በአብዛኛው ስሜት የሚያይልበት የዕድሜ እርከን እንደ መሆኑ እኔም ያገኘኋቸውን መጻሕፍት ሁሉ ለማንበብ የምጥርበት፣ 150ውንም ዳዊት የምደግምበት፣ ድርሳኑንም መልክኡንም የማገላብጥበት ጊዜ ነበር:: ውዳሴ ከንቱ እንዳይሆንብኝ እንጂ:: በርግጥ ጊዜው አልፏል:: ምላሴ እስኪታሰር ድረስ በጸሎት እጸመድ ነበር:: በኋላ ላይ ከትምህርቱ /ከቅጸላው/ ጋር አልሄድ ስላለኝ ከጸሎቱ እየቀነስኩ መጣሁ:: ይህንን አደርግ የነበረው ከአባቶቼ በረከትን፣ ጸጋ እግዚአብሔርን ለማግኘት እንጂ ሹመት ·ሽልማት የማግኘት ፍላጎት ኖሮኝ አልነበረም:: በወቅቱ ለኔ እንዲህ መሆን ታላቅ ብርታት የሰጡኝ መምህራን የነበሩት አባቶቼ ናቸው::

ብፁዕነታቸው ያን ጊዜ ከአባቶች ጋር ስለ ነበራቸው ግንኙነት ሲያስታውሱ «ብዙውን ትምህርት ያገኘሁት ከአባቶች ነው:: አባቶቻችን በዕውቀት የበለጸጉ፣ ጸጋ እግዚአብሔር ያደረባቸው፣ ተቀድተው የማያልቁ የዕውቀት ምንጮች ናቸው:: እኔም በዚያን ጊዜ አጋምና ቀጋ እየተመገቡ የሚኖሩ አንድ አባት ነበሩ:: ወደ እርሳቸው ቀርቤ የሚተኙበት ስሌንና አኩፋዳ ሰጠኋቸው፤ እርሳቸውም መልክአ ማርያም ደግመው መርቀው አስናበቱኝ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው የመጽሐፍ መምህር እንደምሆን ያወቅሁት:: ያኔ ገና ዐሥራ ስድስት ዓመቴ ነበር:: አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው የመጻሕፍት መምህር እንደ ሆንኩ ብቀጥል ኖሮ ብዙ በረከትና ጸጋ ከእግዚአብሔር አገኝ ነበር እላለሁ::

ስለ ተማሩት ትምህርት ቢያጫውቱን? አልናቸው::

«ደግሞ ይሄ ምን ሊያደር ግላችሁ ነው? ምንም አልተማር ኩም፤» በማለት ጥያቄያችንን ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆን ብለው ብዙ አንገራገሩ:: እዚህ ላይ አንድ የተገነዘብነው ነገር አለ:: አባቶቻችን ዕውቀታቸውን ሀብታቸውን ለጠየቋቸው ያለ ንፍገት ያካፍላሉ እንጂ እንዲህ ተምሬያለሁ ዐዋቂ ነኝ፤ ሊቅ ነኝ፤ በማለት ራሳቸውን ከፍ ከፍ እንደማያደርጉ ለማየት ያስችለናል:: እንዲህ የሚያደርጉት እውነት ዐላዋቂዎች ሆነው አይደለም:: እንደ ቅዱስ ቃሉ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ለማቅረብ/ ነው:: ዞሮ ዞሮ ግድ ስንላቸው ፈቃደኛ ሆኑና ቅር እያላቸው ነገሩን:: «ቅኔን፣ ብሉያትን፣ ሐዲሳትን፣ ሃይማኖተ አበውን፣ አቡሻኽርን፣ ዘራቸውን ከነ ትርጓሜያቸው ይዤያለሁ:: እነዚህን የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች ተምሬ ለማጠናቀቅ ስምንት ዓመት ያህል ፈጅቶብኛል:: መማር ብቻ ዋጋ የለውም፤ የተማሩትን ማስተማር ለሌሎችም ማሳወቅ እንጂ:: እኔ በዚህ በኩል የምፈልገውን ያህልም ባይሆን የተማርኩትን ለማስተማር ሞክሬያለሁ»::

ብፁዕነታቸውን የትውልድ ቦታቸውን እንዲነግሩን በጠየቅናቸው ጊዜ አስገራሚ መልስ ነበር የሰጡን «የጳጳስ ሀገሩ ኢትዮጵያ፣ መንደሩም ኢትዮጵያ ነው:: ወንዙ ሁሉ ወንዛችን፤





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org



ኮረብታው ኮረብታችን ነው:: ለንዲህ ነው የምናምነው፤ ማመንም አለብን» ካሉን በኋላ አሳባቸውን እንዲህ በማለት ጠቅልለውታል:: «ወጣቱ ዘመናዊውን ከጥንታዊው አስተባብሮ የአባቶቹን ወግና ሥርዓት ጠብቆ ቢሄድ እርሱም ተጠቅሞ ሀገሩንም ቤተ ክርስቲያንንም ይጠቅማል:: ሀገራችን ዛሬ ከኋላ ቀር ሀገሮች የመጨረሻው ተርታ ላይ ትገኛለች:: ሕዝባችንም እጅግ አሳዛኝ ወደ ሆነ የድህነት አዘቅት እየወረደ ነው:: ይህ ለኛ በእውነት የሚያሳዝን ነው:: ለሀገራችንም ለራሳችንም መሥራት መትጋት ይኖርብናል:: በተለያየ ምክንያት ወደ ውጭ ሀገር የሚሄደው ወጣት ሲመለስ ዕውቀትን ይዞ መመለስ እንጂ ባሕልና ሥርዓቱን መለወጥ አይገባውም:: በሰው ሀገር ተሰዶም ክብሩንም ጥሎ መኖር የለበትም::»

በመቀጠል ያነጋገርነው ደግሞ በዚህ ትውልድ እና በግእዝ ቋንቋ መካከል ያለው ክፍተት እንዲጠብ በሚችሉት ሁሉ እየጣሩ ያሉትን መምህር ዜና ማርቆስ እንዳለውን ነው:: መምህር ዜና ማርቆስ እንዳለው ያስመሰከሩበትን ቅኔን ለማስተማር ወንበር አልዘረጉም:: በአንጻሩ ግን ላይ ታች ብለው ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የሠነቁትን የቅኔ ዕውቀትና የግእዝ ቋንቋ አንድ አራት ያህል መጻሕፍትን በማዘጋጀት ትውልዱን ከግእዝ ጋር አስተዋውቀዋል:: አሁንም በማስተዋወቅ ላይ ይገኛሉ:: እንዲሁም ግእዝን በተለያዩ ቦታዎች ለረጅም ጊዜ አስተምረዋል:: አሁንም እያስተማሩ ነው::

መምህር ዜና ማርቆስ እንዳለው በ1925 ዓ.ም ምዕራብ ጎጃም ባሕር ዳር አካባቢ ጉታ ከተባለው ቦታ ተወለዱ:: በዚያ ይወለዱበት እንጂ አሳደጉበትም፤ ዕድገታቸው በቅኔ ቤት ነው::

መምህር የትምህርት አጀማመራቸውን ሲያስታውሱ «በልጅነቴ በዚያው በትውልድ መንደሬ ፊደልና ንባብ ቆጥሬያለሁ:: ዳዊትም ደግሜያለሁ:: ከዜማውም በመጠኑ ቀሳስሜአለሁ:: በመቀጠል ከመንፈሳዊውና ከትጉቱ መምህር ከመሪጌታ ጌቴ ዘንድ እዚያው ጉታ እያለሁ የቅኔን መሠረት ተምሬያለሁ:: የጀመርኩት የቅኔ ትምህርት ስሜቴን ኮርኩሮት ልቤን መስጦት ኖሮ ወደ ስመ ጥሩው የቅኔ ቤት ዋሸራ ዘልቄ ከየኔታ ፈንቴ ዘንድ ቀጽያለሁ:: በመጨረሻም በደንቢያ ከመሪ ጌታ ዐምደ ሚካኤል፣ በደብረ መዊዕ ከመሪጌታ ነቅዐ ጥበብ ዘንድ የቅኔን ማዕድ ሳጣ ጥም ቆይቻለሁ:: በ1943 ዓ.ም የብሉይ ኪዳንን ትርጓሜ ለማሄድ ቅኔዬንም የበለጠ ለማስፋፋት ወደ አዲስ አበባ መጣሁ::»

ወደ አዲስ አበባ የመጡት መምህር ዜና ማርቆስ ሕይወት አቅጣጫዋ ተለውጦ ያሰቡት ሳይሳካ ውጥናቸው ሳይሰምር ቀረ:: ከዚያስ? መምህር ዜና ማርቆስ ይቀጥላሉ:: «በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ወደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ አዳሪ ት/ቤት የመግባት ዕድሉ ገጠመኝ:: ያን ጊዜ ት/ቤቱ 1ኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ነበር የሚ ያስተም ረው:: እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ተማርኩና 11ኛ እና 12ኛ ክፍልን በካቴድራል ት/ቤት አጠናቀቅሁ:: ከዚያ በኋላ በእቴጌ መነን ት/ቤት ተቀጥሬ የቋንቋ ትምህርት ማስተማር ጀመርኩ:: በተለያዩ ት/ቤቶችም ግእዝና አማርኛ ሳስተምር ቆይቻለሁ:: በመጨረሻም ዛሬ አሜሪካን ሀገር ከሚገኘው ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ጋር በመሆን ያን ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር በነበረው በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ግእዝን በስፋት ስናጠናና ስንመረምር ቆይተናል::

በወጣትነት ጊዜያቸው ስለነበረው የትምህርት ሁኔታ ሲገልጹም ለቅኔ ትምህርት ከፍተኛ የሆነ ጉጉት ነበረኝ፤ ትምህርቱ ራሱ የሚስብ ነው:: በውስጡ ብዙ ነገር እናገኛለን:: ባሕሉ፣ ታሪኩ፣ ሃይማኖቱ፣ ምሥጢሩና ምርምሩ የሚስብ ነው:: በዚህ የተነሣ ተግቼ ነበር የምማረው:: ቋንቋውንም በሚገባ ለማወቅ ችያለሁ:: ይሄ ሁሉ የሆነው ለትምህርቱ ፍቅርና ጉጉት ስላደረብኝ ነው::

እንዲያውም ለግእዝ ቋንቋ ባለኝ ከፍተኛ ፍቅር መጻሕፍትን ለማሳተም ችያለሁ:: መጻሕፍቱም <u>የግእዝ ቋንቋ መግቢያ</u>፣ <u>የግእዝ ቋንቋ በዘመናዊ አቀራረብ</u>፣ <u>የግጥም እፍታ እንገናኝ ማታ</u>፣ <u>ከልጆች ወደ ልጆች</u>፣ <u>ቅኔ ለወጣቶች ቁጥር አንድ</u> ይባላሉ:: አሁን ደግሞ ሁለተኛ ክፍል በሚል የግእዝ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ እያዘጋጀሁ እገኛለሁ::

እነዚህን የግእዝ መጻሕፍት ለመጻፍ ያነሣሣኝ ቋንቋውን ለማያውቀው ለማሳወቅና በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን ብዙው መጽሐፍ የተጻፈው በግእዝ ቋንቋ በመሆኑ ማወቅ የሚፈልግ ሁሉ የአባቶችን ሥርዓትና ትምህርት በቋንቋው እንዲረዳበትም በማሰብ ነው:: ቀድሞ በማስተምርበት ት/ቤትም አንዳንዶቹ ግእዝ አስተምረን እያሉ ይጠይቁኝም ስለነበር ለእነርሱም ስል ነው:: ደግሞም ሰው ሁሉ ዐቅሙ የፈቀደለትን ያህል ዕውቀቱን በመጽሐፍ መልክ እያዘጋጀ ለሌላው ማድረስ የሚችልበት ልምድ ቢዳብር መልካም ነው::

ረሃብተኛ ለሆነ ሰው በቀላሉ የሚበላውና የሚስማማው ነገር ሳናቀርብለት ልንተቸው አንችልም:: በሚገባውና ዘመናዊ በሆነ አቀራረብ የአባቶቻችንን ለዛ ያለው ትምህርት ልናስተምረው እንችላለን:: ወጣቱ አሁን ዐይኑ ተከፍቷል:: ስሕተቱ የኛ ነው፤ ውኃ ከላይ ወደ ታች ነውና የሚፈሰው እኛ ነን መቀስቀስ፣ ማነሣሣት ያለብን:: እንዲህ ሲሆን ወጣቱም በቀላሉ ዕውቀቱን ሊያጎለብት ይችላል::

በወጣትነት ዘመኔ የተለያዩ መጻሕፍትን እመረምር ነበር:: ከዚህም በተጨማሪ ከአባቶች እግር ሥር ሆነን የምንማረው ትምህርት በራሱ ልዩ ነው:: አባቶቻችን ሕያው ወይም ተንቀሳቃሽ ቤተ መጻሕፍት ናቸው»::

እስከ አሁን ካነበቧቸው መጻሕፍት መካከል ልዩ ቦታ የሚሰጡት ይኖር ይሆን? አልናቸው::

«የቤተ ክርስቲያንን መጽሐፍ እርስ በርሳቸው ማበላለጥ ባይገባም እስከ አሁን ከተመለከትኳቸው መጻሕፍት ውስጥ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የጻፏቸው አርጋኖንና መጽሐፈ ምስጢር በጣም እወዳቸዋለሁ፤ ሃይማኖተ አበውም ልዩ ነው::»

በመጨረሻም መምህር ዜና ማርቆስን የሚያስታውሱትን አንድ ቅኔ ይስጡን አልናቸው:: አላንገራገሩም:: ተማሪ ቤት ሆነን መምህርና ተማሪ እንደ ቀልድ የሚዘራረፉት ነገር አለ:: እንዲህ ይላል ተሜ:-

*አዕበይክዎ አነ ለአቡየ እዝን፤*
*በድኅሬሁ ዘበቆልኩ ቀርን፣*

ትርጉም:- አባቴ ጆሮን በኋላ የበቀልኩት ቀንድ በለጥኩት

ሁለት ሦስት ጊዜ ሲጠሩት አቤት የማይል ተማሪ በኋላ ነቃሁ ብሎ /ሠልጥኖ/ ከመምህሩ በላይ ሲንጠራራ የሚያሳይ ነው:: መምህሩም ለዚህች መልስ የሚያጡ አልነበሩምና ነጠቅ አድርገው:-

ወልድየሂ እቡየ ልብ
ዘአሠለጠከ ጊዜ
ተዘከር ዘቀዳሚ
ወኢትርአይ ዘይእዜ፤

ትርጉም:- ጊዜ የሰጠህ /ያሠለጠነህ/ ትዕቢተኛው ልጄ፣የድሮውን እንጂ የዛሬውን አትይ በማለት ይመልሱለታል:: ይህ እንግዲህ ለቀልድ /ቡሽት/ ነው እንጂ መምህሩና ተማሪው ቂም በቀል የሚያያዙ ሆነው አይደለም::

እኛም ከብፁዕ አቡነ ቶማስና ከመምህር ዜና ማርቆስ ጋር ያደረግነውን አጭር ቆይታ በዚህ ስናጠቃልል ልጆችና ወጣቶች ከአባቶቻቸው ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተጠግተው በትኅትና ያለ ትዕቢት በመቅረብ ታታሪዋ ንብ ከመልካሙ አበባ መዓዛውን ቀስማ ጣፋጩን ማር እንደ ምትጋግር ሁሉ እነርሱም ከታላላቆቹ አባቶች ዕውቀትን መቅሰም እንደሚጠበቅባቸው በመጠቆም ነው:: ጠቢቡስ «አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል» አይደል ያለው:: /ዘዳ. 32 ÷ 8/::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*





©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ነገር ሁሉ ለበጎ ነው፡፡ እንዴት?

*<u>መነሻ ሀሳብ፡</u>- አንባብያን የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ ግላዊና ማኅበራዊ ችግሮች «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» /ሮሜ.8÷28/ ከሚለው ቃለ ኃይል ጋር በማያያዝ የሚያነሧቸውን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ፡፡*

ቀሲስ ስንታየሁ አባተ

ሰውዬው ባለትዳር ነው፡፡ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጥራ የምትሠራ ሚስቱ ድንገት ወደ ገጠር ተዛውራ ትሄዳለች፡፡ መሄጃ ሳያንስ የሄደችበት ሥፍራ በረሃ ከመሆኑ የተነሣ አደገኛ የሚባል የወባ በሽታ ያለበት ቦታ ነው፡፡ በዚህ ላይ ገና የምትጠባ ልጅ ይዛለች፡፡ ይህ ጉዳይ ባልን በጣም ያናድደዋል፡፡ ያሳስበዋል፡፡ መናደዱን ያወቀ ወዳጁ መጥቶ በብዙ ምክር ካጽናናው በኋላ «ነገር ሁሉ ለበጎ ነው» ብሎት ሄደ፡፡ ትንሽ እንደ ቆየ ከእናቷ ጋር የሄደችው ልጅ በጠና ትታመምና ሆስፒታል ትገባለች፡፡ አሁንም ያ ወዳጅ ጭብጦ ኩርምት ብለው ልጃቸውን የሚያስታምሙ ወላጆችን «ነገር ሁሉ ለበጎ ነው» ይላቸዋል፡፡ ውሎ ሳያድር ልጅቷ ዐረፈች፡፡ አባት ክፉኛ በኀዘን ተወጋ፤ ለልጁ ሞት ምክንያት ናቸው ያላቸውን የሚስቱ መሥሪያ ቤት ኃላፊዎችንም መኰነን ሥራው ሆነ፡፡ ወዳጁም በብዙ ምክር ሊያጽናናው ፈለገ፡፡ እንደ ተለመደው ነገር ሁሉ ለበጎ ነው አለ፡፡ ኀዘንተኛው አባትም «አሁንስ ይኼ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው የሚለው ቃልህ ነው ያስጠላኝ፡፡ ሁለተኛ ልሰማው አልሻም» ብሎ ጮኸበት፡፡ ለመሆኑ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ሲባል እንዴት ነው ሊሆን የሚችለው?

«ነገር ሁሉ ለበጎ ነው» የሚለውን ቃል የተናገረው ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ከሮም ሀገር ከአሕዛብነት እግዚአብሔርን በማወቅ ወደ ክርስትናው ለመጡት ምእመናን ክርስቲያን በመሆናቸው፣ ፈቃደ እግዚአብሔር ያለበትን መልካም ሥራ ሁሉ በመሥራታቸው ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡባቸውን ፈተናዎችና ችግሮች እንዳይሰቀቁና ከሃይማኖታቸው ወደ ኋላ እንዳይሉ በዚህ ቃል መከሯቸዋል፡፡ «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» ሮሜ.8÷28፡፡ ይህንኑ በሚመስል መልኩ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «ወዳጆች ሆይ÷ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደ መጣባችሁ አትደነቁ፤ ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሴት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ» ብሏል፡፡ 1ጴጥ. 4÷12-13፡፡ ሐዋርያው በክርስቶስ መከራ የሚካፈሉትን ማለት የክርስቶስ በመሆናቸው ፈቃዱን በመፈጸማቸው መከራ መስቀል የተፈራረቀባቸውን ደስ ይበላችሁ ማለቱ ለእንዲህ ዓይነቱ ነገር ሁሉ ለበጎ ስለሚደረግ ነው፡፡

እግዚአብሔር በጎ አድራጊ ነው፡፡ በባሕርይው በጎነት እንጂ ሌላ አይስማማውም፡፡ ጨለማው ብርሃን ይሁን ያለ እግዚአብሔር ለሚወዱትና እንደ አሳቡም ለተጠሩት ሁሉን ነገር የሚያደርግላቸው ለበጎ ነው፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ «ለእኛ በጎ ነገርን ያደረገ ይቅር ባይ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፡፡...ሰውሮናልና፣ረድቶናልና፣ ጠብቆ አቅርቦናልና፣ ወደ እርሱም ተቀብሎናልና እስከዚህችም ሰዓት አድርሶናልና» በማለት በጎ አድራጊ እግዚአብሔርን አመስግኗል፡፡

የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ሲኖር ከራሱም ሆነ ከሌላ ወገን የሚያገኙት ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ዓይነቱና መጠኑ ይለያይ እንጂ መደሰት ማዘን ፣መታመም መዳን ፣ ማግኘት ማጣት፣ መራብ መጥገብ፣ መሰደድ መመለስ፣ መበልጠግ መደኽየት... በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚፈራረቁ ክስተቶች ናቸው፡፡ ከዚህም በተለየ ደግሞ በሥጋ ፈቃድ ተይዞ በኃጢአት መውደቅ፣ ለተለያዩ የኃጢአት ሥራዎች መዳረግ በሰው ላይ ይከሰታል፡፡ «እግዚአብሔር በጎ አድራጊ ነው፤ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው» ከተባለ እነዚህስ? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ ለዚህ መልስ ለመስጠት ቢያንስ ከሁለት ነጥቦች አንጻር ማየት ይጠቅማል፡፡

«ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ»፤ «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው» ብሎ እንደ ተናገረው በዐቂበ ሕግ የጸኑትንና ሕገ እግዚአብሔር እንዳይፈርስባቸው ለመንፈሳዊ ተጋድሎ ሰውነታቸውን የሚጎስሙትን፣ ነፍሳቸውን ላለማጣት ሲሉ ሰውነታቸውን ለእሳት፣ ለስለት፣ ለመንኮራኩር አሳልፈው የሰጡትን ነው፡፡ ዮሐ.14÷15 - 21፣ማቴ. 10÷39፡፡

እነዚህ ሰዎች በፍቅረ እግዚአብሔር ጸንተው፣ ከሥጋ ፈቃድ ርቀው፣ ከኃጢአት ተጠብቀው፡ ሳለ በደዌ ሥጋ ቢሰቃዩ፣ከዚህ ዓለም ሀብት ቢራቆቱ፣ሌሎች ሰዎች በሰንሰለት አስረው ከወኅኒ ቤት ቢወረውሯቸው፣ ወደ እሳት ቢጥሏቸው፣ ከሀገር ሀገር ቢያሳድዷቸው ለበጎ ነው፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደ ተገለጠው ድንቅ ነገር እንደ መጣባቸው ሳይደነቁ በመከራው እየተደሰቱ ከተቀበሉት በመከራው ጸጋ እግዚአብሔር፣ በረከተ እግዚአብሔር ሊጨመርላቸው፣ ክብራቸው ሊገለጥ ወይም ከንቱ ኀሊና ከተባለች ከትዕቢት ሊያርቃቸው ይሆናል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአሕዛብ መካከል ስመ እግዚአብሔርን ሊያስጠራ የተመረጠ፣ በልብሱ እራፊ አጋንንት ከሰው የሚወጡለት ከዚያም በላይ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ያረገ አባት ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ያህል ታላቅ ቢሆንም እርሱ ግን ሌሊት ዕረፍት በሚነሣ የጎን ውጋት ይሰቃይ ነበር፡፡ ይህም ለበጎ የተሰጠው ነው፡፡ እርሱም መታመሙ ለበጎ የተሰጠው መሆኑን «ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፡፡ ይኸውም እንዳልታበይ ነው፡፡ ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ፡፡ እርሱም፡- ጸጋዬ ይበቃሃል፡፡ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ፡፡ እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ፡፡ ...ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና» በማለት ገልጧል፡፡ 2ቆሮ. 12÷7-10፡፡

የኢዮብና የአብርሃም መፈተን፣ የዮሴፍ ተሽጦ ግብጽ መውረድ፣ የሠለስቱ ደቂቅ ወደ እሳት መጣል፣የዳንኤል ለተራቡ አናብስት መሰጠት፣የተሰዓቱ ቅዱሳን መሰደድ፣የሙሴ በሕፃንነቱ መጣል፣ የቅዱስ ጳውሎስና የቅዱስ ሲላስ መታሰር፣የቅዱስ ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ደሴት መጋዝ ...ለበጎ ነው፡፡



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

2. በኃጥአን ላይ የሚሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ፤ ይህን በሁለት መንገድ እናየዋለን:-

ሀ. የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑለት ነው:: «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» ዮሐ.3÷16:: በመሆኑም የኃጥኡን ሕይወቱን እንጂ ሞቱን ስለማይሻ ዕድሜ ለንስሐ ይሰጠዋል:: «የሚቼን ሞት አልፈ ቅድም ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ» እንዲል /ሕዝ. 18÷32/:: የሰውን ድኅነት መሻትና ዕድሜ ለንስሐ መስጠት ብቻም ሳይሆን ኃጥኡን ወደ ራሱ ለመመለስ የተለያዩ ነገሮችን በኃጥኡ ሕይወት ውስጥ ይፈጽማል:: ኃጥኡን በደዌ ይመታዋል፣ በመከራ ጅራፍ ይገርፈዋል:: ይህም ወደ ልቡናው ተመልሶ ካናወዘው የኃጢአት እንቅልፍ ለማንቃት፣የሥጋውን ፈቃድ ተከትሎ ከእግዚአብሐር የተለየውን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ነው:: ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነ ቅኸኝ መልካም ሆነልኝ» በማለት እንደ ተናገረው ኃጥኡን ወደ ራሱ ለመመለስ በተለያዩ መከራዎች ያስጨንቀዋል:: መዝ.118÷71:: ቤተ ክርስቲያንን ያሳድድ የነበረ ውን ሳውልን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊመልሰው ሲሻ በደማስቆ በር ከሰማይ የበረቀ ብርሃን ዓይኑን አሳወ ረው:: የሐዋ. 9÷1–9:: የእግዚአብሔርን መልእክት አላደርስ ብሎ ከፊቱ የኮበለለ ዮናስን ከባሕር ተጥሎ በዓሣ አንበሪ እንዲዋጥ አደ ረገው:: ትን.ዮናስ 2÷1– ፍጻሜ፤3÷1–ፍጻሜ :: ምናሴ በ12 ዓመቱ ነገሠ:: «በእሥራኤልና በእግዚአብሔር ላይ ከአሕዛብ ይልቅ ክፉ ነገርን አደረገ:: ሰሎሞን በሠራው በታላቁ ቤተ መቅደስ ውስጥ ያሠራውን የተቀረጸ ምስል ጣዖት አቆመ:: እግዚአብሔር ምናሴን ለአሦራውያን አሳልፎ ሰጠ:: በሰንሰለት አስረው ከብረት ቀፎ ከተቱት:: ወደ ባቢሎንም እያሰቃዩ ወሰዱት:: ምናሴ ያን ያህል ከበደለ መከራም ከተቀበለ በኋላ በብረት ቀፎ ተከትቶ ሣለ በተጨነቀ ጊዜ ንስሐ ገባ:: ነገር ሁሉ ለበጎ ስለሆነ እግዚአብሔር ተለመነው:: ወደ መንግሥቱም ወደ ኢየሩሳሌም መለሰው:: 2ዜና.33÷1–13:: ንጉሡ ሕዝቅያስ ሐሰተኞች ነቢያት ለእግዚአብሕር የተነገረው የትንቢት ቃል ለእርሱ እንደሆነ አድርገው የነገሩትን ቃል ተቀበለ:: በዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት በደለ:: እርሱም በደዌ መታው:: ሊሞትም እንደ ሆነ ነገረው:: ነገር ሁሉ ለበጎ ነውና ሕዝቅያስ በደዌ ተይዞ ሣለ ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር ማረው:: ትሞታለህ ካለውም በኋላ በዕድሜው ላይ አሥራ አምስት ዓመት ጨመረለት:: ኢሳ. 38÷1–22:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ልጄ ሆይ÷ የጌታን ቅጣት አታቃልል፤ በሚገ ሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል::» እንዳለው ኃጥአንን ከኃጢአት ሊመልስ ለንስሐ ሊያበቃ ሲሻ እግዚአብሔር ቅጣትን ያመጣል:: ያ ለበጎ የተደረገ ነውና በምስጋና ሊቀበሉት ያስፈልጋል:: ዕብ. 12÷5–6::

አንዳንድ ሰዎች ካሉበቱ የኃጢአት ሕይወት ተላቅቀው ወደ እግዚአብሔር ይመለሱ ዘንድ የሚመጣባቸውን መከራ ለበጎ ነው ብለው ተቀብለው ለንስሐ መብቃት ሲገባቸው በመከራው ዝለው፣ ተደናግጠውና ተስፋ ቆርጠው ይጠፋሉ:: እግዚአብሔር ኃጥኡን እስከ መጨረሻው ይታገሠዋል:: ከቸርነቱም ብዛት የተነሣ ለኃጥኡ ÷ ዕድሜ ለንስሐ በመስጠት በሰጠው ዕድሜ ዘመን ውስጥ ለበጎ በሆነው ተግሣጹ ይገሥጸዋል:: ከጌታ በስተ ግራ የተሰቀለው ወንበዴ ዘመኑን በኃጢአት የጨረሰ ክፉ አድራጊ ሰው ነበር:: በክፋት የኖረውን ወንበዴ ይቅር ሊለው ለንስሐ ሊያበቃው ሲፈልግ በቀራንዮ ከጎኑ እንዲሰቀል አደረገው:: በቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ ዐውቆ ተሰቅሎ መከራ በመቀበሉ ተስፋ ሳይ ቆርጥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ሲል በግራ የተሰቀለው ግን ለበጎ የቀረበለትን ተግሣጽ ፈጣሪውን ከአይሁድ ጋር ለመንቀፍ አደረገው:: በማንኛውም የኃጢአት ኑሮ ውስጥ ሳለን መከራ ባገኘን ጊዜ ከኃጢአታችን ሊመልሰን እግዚአብሔር ከልቡናችን ደጅ ቆሞ እያንኳኳ እንደ ሆነ ሊታሰበን ይገባል::

በሌላ በኩልም አንድ ሰው ባለው ኃይል ሁሉ የሚጠበቅበትን ሥራ እየሠራ፣ ተማሪውም እያጠና ሌላ ውም እንዲሁ የበኩሉን እያደረገ ባይሳ ካለት እግዚአብሔር እንደ ተለየው፣ ከአሁን በኋላ ሌላ ተስፋ እንደሌለው አድርጎ መገመት የለ በትም:: ጊዜው ባይደርስ፣ በዚያ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ሊያጣላን ከእርሱም ሊያስታርቀን የሚችል ነገር የሚያጋ ጥመን ከሆነ እግዚአብሐር የሚጎዳንን ነገር አይሰጠንም:: ይህም ለበጎ ነው:: ሰው ግን የራሱን ድርሻ ሳይወጣ መሥራት የሚገባውን ሳይሠራ እንዲረዳውም ፈጣሪውን ሳይለ ምን እጅና እግሩን አጣጥፎ በመቀመጥ ጊዜውን ቢጨርስና መከራ ድንገት ቢደርስበት የራሱን ስንፍና ለበጎ ነው ማለት አይገባም::

ከዚህም በተጨማሪ በጽኑ ደዌ ተይዘው መከራን የሚቀበሉ ሰዎች አሉ:: በደዌ ስለ ተያዙት ሰዎች የሚኖረውም አመለካከት የተለያየ ይሆናል:: ይህም በኃጢአት እንደ መጣባቸው፣ የሕይወታቸው መጨረሻና እንደ ሆነም አድርገው የሚገምቱ ሰዎች አሉ:: በመሠረቱ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጣዊ ደዌ ያት በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰቱ ይችላሉ:: ለአብነትም ደዌ ዘመቅ ሰፍት እንደ ሄሮድስ፣ ደዌ ዘኃጢአት እንደ መፃጉዕ፣ ደዌ ዘእሴት እንደ ኢዮብ፣ ደዌ ዘንጽሕ እንደ ጢሞቴዎስ በተጨማሪም ከሰውነት ባሕርያዊ /ተፈጥሯዊ/ ድክመት ደግሞ የተነሣ የሚከሰት ደዌ አለ:: መቅሰፍት ጊዜ አይሰጥም:: በኃጢአት የተነሣ የሚያገኝን ደዌ ግን «ለአሁኑ ንስሐ ግባ፤ ለወደፊቱ ግን ደግመህ አትበድል» የሚል መልእክት ያለው ነው::

በአጠቃላይ አንድ ሰው በእግዚአብሔር አምኖ ፈቃዱን እየፈጸመ በነፍሱም በሥጋውም የተቻለውን በጎ ሥራ ሁሉ እየሠራ እግዚአብሔር ባወቀው የሚያገኘው መከራና ችግር ለበጎ ይሆናል:: ዋናው ነገር ግን በሕይወቱ ውስጥ ሁሉ ስለ ተከሰተው ችግር ለበጎ ነው በማለት ሳይታበዩ በትኅትና ሆኖ እግዚአብሔር መከራውን እንዲያቀልለት ኃጢአቱን ይቅር እንዲለው መለመን ነው:: በሌላ በኩልም በኃጢአት የተነሣ መከራ ቢመ ጣብንም እግዚአብሔር የሚቀጣን ሊያጠፋን ሳይሆን ከስሕተታችን ሊያርመን ወደርሱ ሊመልሰን ስለሆነ ተስፋ ሳንቆርጥ ንስሐ ገብተን ከሚመጣው ቁጣ ለመዳን ራስን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ይገባል:: ከዚህ ውጪ ግን በኃጢአት ባሕር እየዋኙ የኃጢአት ዋጋ÷ መከራና ችግር÷ ሲከፈለን ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ማለት ስሕተት ነው::

ለዚህ ነው ቅዱስ ጴጥሮስ «ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበልም» ያለው:: 1ጴጥ.4÷15:: ምክንያቱም ክፉ ሥራ ሠርተን ብንፈተን ለበጎ ስለማይቆጠርልን ነው:: አንድ ሰው መሥራት በሚገባው ሰዓት ጊዜውን በከንቱ ቢያሳልፍና ቢደኸይ፣ተማሪው በሰዓቱ ክፍል ገብቶ መማር ማጥናት ሲገባው ችላ ቢልና ለጥሩ ውጤት ሳይበቃ ቢ

/ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል/





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የኑፋቄው መሻ ዙር ከኬልቄዶን እስከ ቅብዐት

አሉላ ጥላሁን

*ካቶሊካውያን በነጻ አውጭነት፣ በመከላከያ ርዳታ፣ በቅኝ አገዛዝ ሥርዓትና በ«ሚስዮናዊነት» ስም በገቡባቸው አገሮች ሁሉ በሦስት መንገድ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን በድለዋል። አንድም በአገርኛ የአነዋወር ሥርዓት፣ቋንቋና ባሕል (Vernacular liturgy and Contextualized theology) ኦርቶዶክሳውያን መሰል የእምነት ተቋማትን (Uniat Churches) ከጥንታውያን የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት በተቀሰጡ «ምእመናን» ማቋቋም፣ አለያም ዓይነተኛ ካቶሊካዊ ሥርዓትን (Latin rite) የሚከተል ተቋም መመሥረት በዚህም ሳቢያ የቤተ ክርስቲያንን ማዕከላዊ አሠራር መናድ ናቸው።*

*በሀገራችን የተከሰቱት የቅብዐትና የጸጋ እምነቶችም ከእዚህ የተለየ መንሥኤ፣ ሂደትና ውጤት የላቸውም። በዚህ ዝግጅታችን በተለይም የቅብዐት እምነትን ዝርዝር ታሪክ፣ ምንነት፣ ዛሬ ያለበትን ሁኔታና የመፍትሔ ሐሳቦችን በተከታታይ እናቀርባለን።*

*/ካለፈው የቀጠለ/*

የቅብዐትና የጸጋ እምነት በኢትዮጵያ እንደ እሾህ የተተከለውና እንደ ሰደድ እሳት የተያያዘው አልፎንሱ ሜንዴዝ በተጠቀሰው ሁኔታ ለሁለቱ ሰዎች ካስተማረና እርሱ ከአገር ከተባረረ በኋላ ይሁን እንጂ ከታሪከ ነገሥቱና ከሌሎች ጽሑፎች እንደም ንመለከተው ውስጥ ውስጡን በካቶሊክ ሚስዮናውያን ሲፋፋም የኖረ ነው።

«ፖድረ አንቶንዮ ፈርናንደዝ የተባለው ኢየሱሳዊ ሰባኪ በ1620 ዓ.ም ግንቦት ወር ደንቢያ ላይ ሳለ ወደ ማኅበር ጠቅላይ አለቃ ሲጽፍ ንጉሥ ሱስንዮስ ስለ ክርስቶስ ቅባት ክርክር ተነሥቷልና መርምሬ እንድፈርድበት ስለ ጉዳዩ መጽሐፍ ጽፊህ እንድ ትልክልኝ ሲሉ እንደለመኑት ይተርካል።

ከዚህም ላይ ሊቀ ጳጳሳቱ አልፎንሱ ሜንዴዝ ካገሩ ተባሮ ሲሄድ በመንገድ ላይ ሳለ ወደ ንጉሥ ፋሲል ወይም ሡልጣን ሰገድ ሁለተኛ /1632–62/ በጻፈው ደብዳቤው ውስጥ ከቅባት ክርክር ጋር የተያያዘውን ሌላ ክርክር ያመለክ ትበታል። ክርክሩም ክርስቶስ በጸጋና በባሕርይ የአብ ልጅ የሚል ነበር። እንግዲህ የቅባቱ ክርክር የተጀመረው የፖርቱጌዝ መልእክተኞች በነበሩበት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ነው » /አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት÷ 1951 ዓ.ም/ <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ባሕርያት አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምህርት</u>።

- ክርክሩ በዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ጠንክሮ ያልወጣው ንጉሡ የተቀበላቸውና የሚደግፋቸው የካቶሊካውያን ሚስዮናውያን ስብከት በማናቸውም የሃይማኖት ወገን እንዳይሰናከል፣ ሊፈጠር በሚችለው ሁከትም ተቃውሞ እንዳይገጥመው በጽኑ ዐዋጅ ከልክሎ ስለ ነበር÷ አንድም በነጻነት መከራከር ስላልተቻለ ነው። ዐፄ ሱስንዮስ ቅብዐቶችና ጸጐች ከ1621 – 23 ዓ.ም /ቢያንስ ሁለት ጉባኤ ያህል/ ሲያካሂዱት የነበረውን ክርክር በዐዋጅ የከለከለው በጴጥሮስ ፖኤዝ ምክር እንደ ኾነ አንዳንድ ምንጮች ይጠቁማሉ። (Merid Wolde Aregay, in <u>The Missionary factor in Ethiopia</u>, p.51)]

ይህ በእንዲህ እንዳለ የዐፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ክርክሩ የጀመረው አልፎንሱ ከመምጣቱ በፊት እንደ ኾነ ይናገራል። ንጉሡ በ23ኛው ዘመነ መንግሥት ማለት 1623 ዓ.ም ለጦርነት ከመነሣቱ በፊት ሁለቱ ወገኖች /የተዋሕዶና የቅብዐት ወገኖች/ ቀርበው እንዲያከራክራቸው ጠይቀውት እርሱም ወደ ዘመቻ መሔዱን ገልጾ ሲመለስ እንደሚያከራክራቸው ተስፋ ሰጣቸው። በተመለሱም ጊዜ ጉባኤ ሠርቶ እንዲከራከሩ አደረገ። የንጉሡ ጸሐፊ ትእዛዝ አዛዥ ጢኖ /ተክለ ሥላሴ/ በዜና መዋዕሉ እንደ ተወልን በቅብዐቶች በኩል የቆሙትን በርከት ያሉ ስሞች ሲጠራ በተዋሕዶዎች በኩል ግን ሁለት ስሞችን ብቻ ያነሣል። ቅብዐቶች (1) አባ ፈትለ ሥላሴ (2) አባ አስካለ ዘአትካና (3) አባ ልብሰ ዘጐንጅ (4) አባ በትሮ (5) አባ እስጢፋኖስ ሲሆኑ ተዋሕዶዎች ደግሞ አዛዥ ዘድንግልና አባ ክፍለ ክርስቶስ ነበሩ። በወርኃ ዐቢይ ጾም ክርክሩ ተጀምሮ ቀኙ ለቅብዐቶች ተሰጠና በእዚሁ ለቅብዐት እምነት ወገኖች ብይን ተሰጠ። ይህም ዐዋጅ እስከ ዐፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ጸንቶ ቆየ። (ሥርግው ሐብለ ሥላሴ /ዶ/ር/÷ <u>የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት</u>÷ ቅጽ 6÷ገጽ 134)።

አልፎንሱ ሜንዴዝ ከእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ጋር ተከራክሮ ከተረታና ከአገር ከተባረረ በኋላ በአምሳያው ያስገኛቸው በግብር ያስከተላቸው ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ (የቅብዐት ልጅ ኤዎስጣቴዎስ ዘሳንኳ ጊዮርጊስና የጸጋ ልጅ ቆረንጮ መናፍቅ ተክለ ሃይማኖት) በሌላ ጉባኤ ቀርበው በእጨጌው እንደ ተጠየቁ መምህር ደጉ ዓለም ካሣና መጋቤ ብሉይ ወሐዲስ ኃይለ ሚካኤል ያደረሱን ምንጭ ያስረዳል፦

«... መናፍቁ አውፋንዮስ ተረቶ ወደ አገሩ ሲሄድ በአበሻ እሾኽ ዘርቸባት መጣሁ አለ ይባላል። ከዚህ በኋላ የእርሱን ተማሪ መናፍቅ ኤዎስጣቴዎስን (የሳንኳው ሰው) ሃይማኖትህ ምንድን ነው ቢሉት ቅባት ነው፤ በቅባት የባሕርይ ልጅ እላለሁ አላቸው። ትርጓሜውን ንገረኝ ቢሉት ኀድረት፣ ንስአት ነው አላቸው። ኀዳሪው ማን ነው? ቢሉት መንፈስ ቅዱስ ነው አላቸው። ተቀቢው ማን ነው ቢሉት ወልድ በለበሰው ሥጋ አላቸው። እጨጌውም በኀድረተ መንፈስ ቅዱስ የተወለደው የጸጋ ልጅ ይሆናል እንጂ የባሕርይ ልጅ ይሆናልን? እንዲህማ እንዳትል ቆረንጮ ተክለ ሃይማኖት ወንድምህ ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ አለ ቢሉት ምላሽ አጣ።

ከዚህ በኋላም ቅባት ማለት ክብር ነው አለ። ማንን አከበረ ቢሉት ወልድ ሥግውን አለ። በኀድረት ነው በተዋሕዶ ቢሉት በኀድረት እንዳይል የጸጋ ልጅ ሆኖ፣ በተዋሕዶ እንዳይል መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ሥግው ጋር ሞተ የሚል ሆኖበት ሲሽመደመድ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ እርሱ ባለቤቱ በወንጌል «አነ እቄድስ ርእስየ፤ እኔ ራሴን እቀድሳለሁ» /ዮሐ.17÷19/ ብሎብሃል፤ ሊቁ ዲዮስቆሮስም «እመቦ ዘይቤ ከብረ በመንፈስ ቅዱስ ከመ አሐዱ እምነቢያት ውጉዘ ለይኩን» ብሎብህ የለም? ብለው ረተው፣ አውግዘው፣ ለይተው አሳደውታል። ከዚህ በኋላ አገሩ ሳንኳ ጊዮርጊስ የቅባት ሃይማኖትን ማስተማር ጀምሮ አል። ከሳንኳ ጀምሮ ጐጃም ውስጥ ሜጫን፣ ሞጣን ከዲማ ከዲቦ በቀር ሁሉን አስተማረ።...

እንዲሁም እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ቆረንጮ መናፍቅ ተክለ ሃይማኖትን ሃይማኖትህ ምንድር ነው አሉት። ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ እላለሁ አለ። አንዱ ልደት ከአብ እም ቅድመ ዓለም፣





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ሁለተኛው ልደት ከእመቤታችን በጊዜ ፣ ሦስተ ኛው ልደት በዮርዳኖስ ሲጠመቅ ከመ ንፈስ ቅዱስ በቅብዐት የተወለደው ነው አለ። እርሳቸውም ሐዋርያት ነአምን ክልኤተ ልደታተ አሉ እንጂ ሠለስተ ልደታተ አላሉም ብለው ረተቱ ። ከዚያ በኋላ ተወግዞ አገሩ ጀር ገብርኤል ገብቶ በድብቅ ማስፋፋት ይዞአል። ልጆ ቹም አማራ ሳይንት ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ብለው አስተምረዋል። በተድባበ ማርያም ሠልጥነዋል።...»

## የአልፎንሱ ንግር ስለ መድረሱ

የአሕመድ ግራኝ የወረራ ኃይል ተሸንፎ ከተወገደ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጠፋባትን ምእመናን ፈልጋ ለማግኘትና ወደ ሕጽኗ ለመመለስ ብዙ ደክማለች፥ ድካሟም በከንቱ አልቀረም። ብዙዎቹ ተመልሰዋል። የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ ዕንባቆም ፈርቶ ወደ እስልምና የገባውን ክርስቲያን ሁሉ መጽሐፈ ቄድር እየተደገመ ጠበል እንዲረጭና ወደ ሃይማኖቱ እንዲመለስ አድርገው ብዙው ተመልሷል። ነገሥታቱ እነ ዐፄ ገላውዴዎስ፣ ዐፄ ሚናስ፣ ዐፄ ሠርፀ ድንግልና ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ግራኝ ያፈረሳቸውንና ያቃጠላቸውን ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተመልሰው እንዲሠሩ በያለበት ትእዛዝ አስተላልፈዋል። ይሁንና ከአንዱ የመከራ ቀንበር ወደሌላው ስትዛወር የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ፈተና አላጣትም። ይኸውም ከግራኝ ወረራ በማስከተል የላቲኖች የተንኰል መልእክተኞች የጠላትነት ሥራቸውን ለመቀጠል ያስገኟቸው የቅብዐትና የጸጋ እምነቶች ከነገሥታቱ፣ ከመሳፍንቱና ከሊቃውንቱ ተከታዮችን አግኝተው፤ እንደ ሰደድ እሳት ተያይዘው በሃይማኖት የርስ በርስ መለያየት መጀመራቸው ነው። የቅብዐቶችና የጸጐች አዲስ ትምህርት ሆነ ተብሎ ለማለያየት የተተከለ እሾህ ስለሆነ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ካህናትንና ሊቃውንትን ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን ከመንግሥት፤ መንግሥትንም ከሕዝቡ ማለያየቱን ቀጠለ። ከሁለት ምእተ ዓመታት በላይም /ከዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት /1607 – 32/ እስከ ቦሩ ሜዳ ጉባኤ /1878/ መካሄድ ድረስ) ዘለቀ። ከዐፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት በኋላ የቅብዐቶችና የጸጐች አዲስ ትምህርት ከሥነ መለኮታዊ ይዘቱ (theological issue) ይልቅ ፖለቲካዊ መሣሪያነቱ ጐልቶ የወጣበትን፣ የኖረውን የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት መልካም ግንኙነት የጐዳበትን፣ የጳጳሳቱ ክብር የሊቃውንቱ አንድነትና ዝና የጐደለበትን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በተለይም ቤተ ክርስቲያን ለበዳዩም ለተበዳዩም መሸሻ፣ አምባ መጠጊያ የምትሆንበት ትውፊታዊውና ማኅበራዊው የተማኅፅኖ አገልግሎቷ (Right of Asylum) የተጣሰበትን፣ ሥነ ጥበባዊና ኪነ ጥበባዊ ዕድገታችን የተዳከመበትን፣ ሃይማኖተ አበውን ይመስሰሉ የመሠረተ እምነታችን መድብልና እርሱን የሚያስተምሩ ሊቃውንትን ለማጥፋት ጉባኤያቱንም ለመበተን ጥረት የተደረገበትን ሌላው ቀርቶ ከሰባት ዐሥርተ ዓመታት በላይ /1769 – 1855 እ.አ.አ/ በጸናው ዘመነ መሳፍንት የውስጥ ብጥብጥን በማባባስ ረገድ ቀንደኛ ሚና ስለነበረውና በየዓመቱ ለትንሣኤ ወደ ኢየሩሳሌም ይደረግ የነበረው ጉዞ በመቋረጡ እዚያ የሚኖሩት መነኮሳት በችግርና በሕመም ያለቁበትን፥ ወዲያውም ደግሞ ዐፅመ ርስታችን የጠፍ ንብረት ሆኖ በሌሎች የተወሰደበትን ሁኔታ እናስተውላለን። በተጨማሪም ከ1634 ዓ.ም ጀምሮ ከጀርመን፣ ከስኮትላንድ፣ ከስዊዘርላንድ፣ ከስዊድን፣ ከኖርዌይና ከሆላንድ እየተነሡ የመጡት የፕሮቴስታንት /ፀረ ማርያም/ እና የካቶሊክ ሚስዮናውያን ቡድኖች በሃይማኖት ስም ያስፈጽሙ ለነበሩት ፖለቲካዊ ጉዳያቸው የሀገራችንን ገበና በርግዶ በማሳየት ረገድ የራሱ ድርሻ ነበረው። የሚከተሉትም ጥቅሶች ይህንን ያረጋግጣሉ።[*«However, his /Fasiledes/ effort to restore the former cooperation and interdependence between church and state was nullified from the start by the vehement antagonism which had developed between the followers of the compromise ideas of Unction and Grace and the mainstream Unionists.»* *(Merid Wolde Aregay, in The Missionary factor in Ethiopia, pp.55)]*

*«ነገር ግን የሚስዮኖች አሳብ እርስ በርስ አለያይተው ዘወር ለማለትና ኋላም እነሱ በዘሩት ልዩነት ወንድማማቾች ሲጋደሉ ለመሣቅ ከተቻለም አስታራቂ መስሎ ገብቶ አገርን ለመያዝ ስለሆነ፤ ከገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ባንድነት ሁነው ከውጭ የመጣ የሃይማኖትም ሆነ የሀገር ጠላታቸውን ድል ሲያደርጉ የኖሩ ኢትዮጵያውያን እዚህ ላይ በአልፎንሱ ተንኰል በተመረዙ ሁለት ሰዎች ስብከት መለያየታቸውና እርስ በርስ ደም መፋሰሳቸው ያሳዝናል። በቤተ መንግሥትም በየጊዜው የሚነግሡ ነገሥታት አንዱ አንዱን ሲደግፍ አንዱ አንዱን ሲነቅፍ ከባድ ችግር ተፈጥሮ ነበር።... መናፍቅ ኤዎስጣቴዎስ በሀገሩ በጐጃም ቅብዐትን አስፋፍቶ ስለነበር የጐጃም ባላባቶችና ከሊቃውንቱም ብዙዎቹ ቅብዐቶች ነበሩ። በጐንደርና በሸዋም ርጉም /ቀረንጮ/ መናፍቅ ተክለ ሃይማኖት የጸጋን እምነት ስላስተማረ ሊቃውንቱ ሁሉ ይተማመሙ ነበር።» /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ገጽ 63–65 እና 122–123/*

*«የቅባቶችም ወገን ከጐጃም በተለይ ደብረ ወርቆች ናቸው። ተዋሕዶ ግን በደብረ ሊባኖስ፤ በሸዋ፤ በጐንደር፤ በትግሬ ነው። ጸጋዎች ግን ይበልጥ የሚኙት በሸዋ ነው ይባላል።» /ተ.ጸ.መ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፥ /1953 ዓ.ም ገጽ 269/።*

ለጐንደር መንግሥት (Gonderine dynasty) እና ከተማ እንደ መጀመሪያ መሥራችና ቆርቋሪ ከሚቆጠሩት ዐፄ ሠርፀ ድንግል /1556 – 1590 ዓ.ም/ በኋላ የተከተሏቸው ነገሥታት መቀመጫቸውን በደንቀዝ፣ በጎንደርና በአካባቢው እንዳደረጉ፤ ከዐፄ ፋሲል /1632–67/ እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ /1855–68/ ደግሞ ጎንደር ቀዋሚ መንበረ መንግሥት እንደ ኾነች ይታወቃል። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከግብፃዊው ጳጳስ ቀጥሎ አስተዳደራዊ ሁኔታውን በመከታተል ሁለተኛ ሰው የነበረው የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ መቀመጫም አዘዞ እንዲሆን ተደርጓል። በዚህ በ17ኛው መ.ክ.ዘ የደብረ ሊባኖስን ገዳም የሚወክል ደብር በጎንደር አቅራቢያ የተመሠረተው ደብረ ሊባኖስ ለጐንደር ርቀት ስላለው ይመስላል፤ ይኸውም አዘዞ ተክለ ሃይማኖት ነው። የዜጋመሉ /ሸዋ/ ደብረ ሊባኖስ እና የአዘዞ /ጐንደር/ ደብረ ለባኖሊ የሚለው አጠራር በዚህ ሳቢያ የመጣ ይመስላል። የአዘዞዎችና የደብረ ሊባኖስ ሊቃውንት በአንድነት ተጠቃለው ቤተ ተክለ ሃይማኖት በመባል ይታወቃሉ። ቤተ ተክለ ሃይማኖት ከ17–19 መ/ክ/ዘ ከዲማ ጊዮርጊስ ሊቃውንት ጋር ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሕልውና ተጋድሎ አድርገዋል።

ስለሆነም የቅብዐትና የጸጋ ልጆች ከተዋሕዶ ሊቃውንት ጋር ክርክር ያካሄዱባቸው አብዛኞቹ ጉባኤያት የተሠሩት በጎንደር ከተማና በአካባቢዋ /ደንቀዝ፣ ይባባ፣ ራሻ፣ አሪንጎ፣ አዘዞ፣ ከይላ ሜዳ፣ አምባ ጫራ፣ ደብረ ማርያም /ጣና ደሴት/ ወዘተ ናቸው። ክርክሮቹ በተደረጉባቸው ጉባኤያት ሁሉ ዳኛው ንጉሡ ምስክር ጳጳሱ ነበሩ። አብዛኛውን ጊዜ ዳኛው እንደ እምነቱ ስለሚመሰክር አንደኛው ሲደሰት ሌላው ሲያዝን ኖሯል። የክርክሩ ጠባይዕ በአብዛኛው በቃል የሚካሄድ እንዲያም ሲል በኃይል ላይ ያረፈበት ወቅት ነበር። ከነገሥታቱም በጉዳዩ ላይ የአስታራቂነት ወይም ለዘብተኛ አቋም የነበራቸውም /ዐፄ በካፋ፥ ዐፄ ምኒልክ/ ታይተዋል። በተለይም ከግብፃውያን ጳጳሳት አንዳንዶቹ አቡነ ማርቆስ፣ አቡነ ሲኖዳና አቡነ ክርስቶዶሉ ሦስተኛ ወደፊት በታሪክ ውስጥ እንደምናየው በጉዳዩ ላይ

/ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል/





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ባለፈው እትም የ «በ» ወይም የ «ቦ» ዝርዝር በሚል ርእስ በግእዝ ቋንቋ ስላለው የማለት ግስ አገልግሎት በዝርዝር አቅርበናል:: በዚህ እትም ደግሞ ቃል በገባነው መሠረት ከትምህርቱ ጋር መቅረብ የነበረባቸውን ቃላት እና መልመጃዎችን እናቀርባለን:: ከዚ ሀም ጋር የ «ለ» ዝርዝር እና «ዘ»፣«እንተ» እና «እለ» ከተሰሉት ርእሶች ጋር ሰፋ ያለ ትምህርት አቅርበናል:: የዓምዱ ተከታታዮች ከሚቀርቡት ትምህርቶች እየተማራችሁ እንደሆነ ከምትልኩልን ደብዳቤዎች እንረዳለን:: ወደፊትም ከዚህ በተጠናከረ መልኩ እንደምንማማር ቃል እየገባን በዚህ እትም ያቀረብነውን ትምህርት እንድትከታተሉ እንጋብዛለን::

## ቃላት ሀ

ጠያር/ጠያራ –አይሮፕላን
ጠያራት – ለብዙ
ሠረገላ – መኪና
መኪና – መኪና
ዘረቦን – ነጠላ ጫማ
ሣዕን – ጫማ
አሣዕን – ለብዙ
መልበስ – ልብስ
ልብስ – ልብስ
አልባስ – በብዙ
አራዝ – ልብሰ ቀሚስ
ስእርት – ፀጉር
ቆብዕ – ቆብ
ቆጳን – ጫማ፣ ገምባሌ
ፀጉር – በቁሙ
መስዕርት – ሚዶ
ገጽ – ፊት
መጽሔት – መስታወት
ሣጹን – ሣጥን
ክርታስ – ካርታ
ክሳድ – አንገት
ሕልቀት – ቀለበት
ሕልቀተ ወርቅ–የወርቅ ቀለበት
ሐብል – ሀብል፣ ገመድ
መነጽር – አጉልቶ የሚያሳይ
ነሳኢ – አንሽ
ነሳዒ ገጽ – ፎቶ አንሽ
በዓለ ሀብት – ሀብታም
ደራሲ – ደራሲ
ነዳይ – ድሀ
ነጋዲ – ነጋዴ

## ቃላት ለ

ዘፋኒ– ዘፋኝ
መድረክ – በቁሙ
ዘማሪ – ዘማሪ
ክታብ/ጦማር/–ደብዳቤ መልእክት
ማይ – ውኃ
ማያት – በብዙ
ማዕበል – ማዕበል፣ ጎርፍ
ማዕበላት – በብዙ
ዝናም – ዝናብ
ዝናማት – በብዙ
ደመና – ደመና
ደመናት – በብዙ
ጊሜ – ጉም
ነቅዕ – ምንጭ
አንቅዕት – ምንጮች
ፈለግ – ወንዝ
አፍላግ/አፍላጋት – ብዙ
ባሕር – ባሕር፣ ውቅያኖስ
አብሕርት – በብዙ
ቀላይ – ሐይቅ
ቀላያት – በብዙ
መጠር – ነጠብጣብ
ውቅያኖስ – በቁሙ
ሰማይ – ሰማይ
ምድር – ምድር
መብረቅ – መብረቅ
ነጎድጓድ – ነጎድጓድ
ነጎርጋር – ጉርምርምታ
በረድ – በረዶ
ቁር – ውርጭ /ብርድ/

## ቃላት ሐ

ክረምት/ክርም/–ዘመን፣ ክረምት
ኪሂላ – ኪስ፣ ሀሩር
ኩዕሶ – ኳስ
መርሕበ ኩዕሶ – ስታዲየም
ኩዕሶ ዘእግር – የእግር ኳስ
ኩዕሶ ዘእድ – የእጅ ኳስ
ኩዕሶ ዘመረብ– የመረብ ኳስ
ክረቦ – ቅርጫት
ኩዕሶ ዘክረቦ – የቅርጫት ኳስ
ፈታሒ – ዳኛ
ተውኔት – ጨዋታ
መስመር – መስመር
ፈታሒ–/ዘ/መስመር–መስመር ዳኛ

## ቃላት መ

ቤተ መጻሕፍት–የመጻሕፍት ቤት
ቤተ ሐኖት – ቡና ቤት
ቤተ ምኅጻብ – ሻወር ቤት
ሐጻኒ – ሞግዚት /ሞግዚት/
ንታሚ – አታሚ
አኅታሚ – አሳታሚ
ቤተ ማኅተም – ማተሚያ ቤት
ቤተ ሞቅሕ – ወህኒ ቤት
ቤተ ወይን–ጠላ ቤት፣ጠጅ ቤት
ቤተ ትምህርት–ትምህርት ቤት
ቤተ ላሕ – ኀዘን ቤት
ሐመር – መርከብ
አሕማር – መርከቦች
ኖትያ – መርከበኛ /ዋናተኛ/
በዓለ ሐመር – መርከበኛ

## ቃላት ሠ

መሀሪ – መምህር /አስተማሪ
መሀሪት – አስተማሪት መምህርት
መሀርያን – አስተማሪዎች
መሀርያት – ለሴት በብዙ
መሐሪ – ይቅር ባይ /ቸር
መሐርያን – ይቅር ባዮች
ተመሃሪ – ወንድ ተማሪ
ተመሃሪት – ሴት ተማሪ
ተመሃርያን – ተማሪዎች
ተመሃርያት – ለሴት
መምህር – መምህር
መምህራን – ብዙ
መምህርት – መምህርት
ርእሰ መምህራን – የመምህራን ራስ፣ አለቃ
ርእሳነ መምህራን – የመምህራን አለቆች
መርድእ – ተማሪ፣ ረድ፣ አገልጋይ
ረድእ – አገልጋይ
አርድእት – አገልጋዮች
አርዳእ – ተማሪዎች
አርዳኢሁ – ተማሪዎቹ
ሐብሬቲ – ወልዋይ፣ ሊስትሮ
ደፍተር – ደብተር
ደቂቃ – ደቂቃ ?
ክፍለ ጊዜ – ፔሬድ
እረፍት – እረፍት
መጥቅዕ – ደወል
ዐምሐራይ – አማርኛ
ልሳነ እንግልጣር – እንግሊዝኛ ቋንቋ

## የግስ ቃላት /ከላይ ለተጠቀሱት ቃላት መሠረት ናቸው/

አስሐወ – አወለቀ
ደረሰ – ደረሰ፣ ጻፈ
ተከወሰ – ተናወጠ፣ ተነዋወጠ
ነስአ – ያዘ፣ አገኘ፣ ነሳ
ሐፀነ – አሳደገ
ወዐለ – ዋለ
ተዐረዘ – ለበሰ
ውህዘ – ፈሰሰ
መሐረ – ይቅር አለ
ፈነወ – ላከ
ተፈነወት – ተላከች
ኀፀበ – አጠበ
ኀተመ – አተመ
ቤተ – አደረ
ረድአ – ረዳ፣ አገዘ፣ አገለገለ
ዘፈነ – ዘፈነ
ነጸረ – አየ
ተመሀረ – ተማረ
መሀረ – አስተማረ
ርሕቀ – ራቀ
ሞዓ – አሸነፈ
ሐብረተ – ወሰወሰ
ነገደ – ነገደ
ለብሰ – ለበሰ
ዘመረ – ዘመረ
ተዋነየ – ተጫወተ
ፈትሐ – ፈረደ
ዘነመ – ዘነበ
ክርመ – ከረመ
ወሰደ – ወሰደ



©ማኀበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## የ«ለ» ዝርዝር እና ዘ፣ እንተ፣ እለ

ለ = ለ ፣ ን ፣ የ ስለ = እየ

የ«ለ» ዝርዝር «ለ» ን መልኩን በመቀያየር ከላይ የተለመዱትን ቅጥያዎች በመጨመር ለኔ /ለ+ እኔ– to + me /፣ ላንተ/ ለ+አንተ– to + you/ ወዘተ በማለት የ«ለ»ን የተጠቃሽነት ሞያ የሚጠቁም ዝርዝር ነው። በ ለ የሚዘረዘሩ የግእዝ ቃላት እና ጥቅማቸው እንደሚከተለው ነው።

5.1. ለ እንደ ተጠቃሽ ተውላጠ ስም /Preposition + to + objective pronouns/

አነ ሊተ /ልየ/ – ለእኔ – to me
አንተ – ለከ – ለአንተ – to you
አንቲ – ለኪ – /ላንቺ –to you
አንትሙ – ለክሙ – ለእናንተ – to you
አንትን – ለክን – ለእናንተ– to you
ንሕነ – ለነ – ለእኛ – to us
ውእቱ – ሎቱ – ለእሱ – to him
ይእቲ – ላቲ – ለእሷ – to her
ውእቶሙ – ሎሙ/ሎቶሙ – ለእነሱ – to them
ውእቶሙ – ሎሙ/ – ለእነሱ – to them
ውእቶን – ሎን/ሎቶን/ ለእነሱ – to them

ምሳሌ:=

ሰላም ሊተ + ሰላም ለኔ፣ ሰላም ለኔ ይሁን፣ ሰላም ለኔ ይገባል – Peace to me
ሰላም ለከ – ሰላም ለአንተ፣ ሰላም ላንተ ይሁን፣ ሰላም ላንተ ይገባል– Peace to you
ሰላም ለኪ – ሰላም ላንቺ፣ ሰላም ላንቺ ይሁን፣ ሰላም ለአንቺ ይገባል– Peace to you
ሰላም ለክሙ – ሰላም ለእናንተ፣ ሰላም ለእናንተ ይሁን፣ ሰላም ለእኛንተ ይገባል– Peace to you
ሰላምለክን–ሰላም ለእናንተ፣ ሰላም ለእናንተ ይሁን፣ ሰላም ለእናንተ ይገባል–Peace to you
ሰላም ለነ – ሰላም ለእኛ፣ ሰላም ለእኛ ይሁን፣ ሰላም ለእኛ ይገባል – Peace to us
ሰላም ሎቱ/ሎ – ሰላም ለእሱ፣ ሰላም ለእሱ ይሁን፣ ሰላም ለእሱ ይገባል –Peace to him
ሰላም ላቲ – ሰላም ለእሷ፣ ሰላም ለእሷ ይሁን፣ ሰላም ለእሷ ይገባል – Peace to her
ሰላም ሎሙ ሰላም ለእነሱ፣ ሰላም ለእነሱ ይሁን፣ ሰላም ለእነሱ ይገባል – Peace to them
ሰላም ሎን – ሰላም ለእነሱ፣ ሰላም ለእነሱ ይሁን፣ ሰላም ለእነሱ ይገባል – Peace to them

5.2. የለ ሁለተኛ ዝርዝር /Verb + Preposition + Objective Pronouns/

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሊተ – | ልኝ | መጽአ ሊተ – | መጣልኝ |
| ለከ – | ልህ | መጽአ ለከ – | መጣልህ |
| ለኪ – | ልሽ | መጽአ ለኪ – | መጣልሽ |
| ለክሙ – | ላችሁ | መጽአ ለክሙ – | መጣላችሁ |
| ለክን – | ላችሁ | መጽአ ለክን – | መጣላችሁ |
| ለነ – | ልን | መጽአ ለነ – | መጣልን |
| ሎቱ – | ለት | መጽአ ሎቱ – | መጣለት |
| ለቲ – | ላት | መጽአላቲ – | መጣላት |
| ሎሙ – | ላቸው | መጽአ ሎሙ – | መጣላችሁ |
| ሎን – | ላቸው | መጽአሎን – | መጣላቸው |

ተጨማሪ ምሳሌዎች: – ሰአለ – ለመነ
ሰአልከ – ለመንህ ሰአል – ለምን
ሰአልኪ – ለመንሽ ሰአሊ – ለምኝ
አነ – ሰአሊ ሊተ ቅድስት ቅድስት ሆይ ለምኝልኝ
አንተ–
አንቲ –
አንትሙ –
አንትን –
ንሕነ – ሰአሊ ለነ ቅድስት – ቅድስት ሆይ ለምኝልኝ
ወእቱ – ሰአሊ ሎቱ ቅድስት – ቅድስት ሆይ ለምኝለት
ይእቲ – ሰአሊ ላቲ ቅድስት – ቅድስት ሆይ ለምኝላት
ውእቶሙ – ሰአሊ ሎሙ ቅድስት – ቅድስት ሆይ ለምኝላቸው
ውእቱን – ስአሊ ሎን – ቅድስት ሆይ ለምኝላቸው

ማስታወሻ

አንተ በሚለውና በሌሎቹ ባዶ ቦታ የሆነው ስለማይነገርባቸው ነው። ማለትም ሰአሊ ለከ ብንል ትርጉም ስለማይሰጠን ነው።

<u>ተጨማሪም ምሳሌ</u>

ወይ – ወዮ
አሌ –ወዬ

| | | |
|---|---|---|
| ወይ ሊተ– | ልየ ወዮልኝ /ወዮ ለኔ/ | Woe to me |
| ወይ ለከ – | ወዮልህ | Woe to you |
| ወይ ለኪ – | ወዮልሽ | Woe to you |
| ወይለክሙ – | ወዮላችሁ | Woe to you |
| ወይለክን – | ወዮልን | Woe to us |
| ወይሎቱ – | ወዮለት | Woe to him |
| ወይላቲ – | ወዮላት | Woe to her |
| ወይሎሙ – | ወዮላቸው | Woe to them |
| ወይሎን – | ወዮላቸው | Woe to them |



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አ፣ አሌ፣ ወይ፣ ሰይ – እህ፣ ወዮ ይሆናሉ ዬ፣ዮ ወየው ፣ ወዮው
አ – ሆይ፣ ይብላኝ:: እግዚእ – ጌታ፣ እግዚእ + አ – እግዚኦ – ጌታ ሆይ፣ አቤቱ::

**5.3. «ለ» ከ «ቦ» ጋር**

«ለ» ከ «ቦ» ጋር የማለት ግስ በመሆኑ ይተረጐማል

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቦ ለከ – | አለህ – አለህ – | You have | ነበረህ | You had |
| ቦ ሊተ – | /ለእኔ/ አለኝ – | I have | ነበረኝ | I had |
| ቦ ለኪ – | አለሽ – | You have | ነበረሽ | You had |
| ቦ ለክን – | አላችሁ – | You have | ነበራችሁ | You had |
| ቦ ለነ – | አለን – | We have | ነበረን | We had |
| ቦ ሎቱ /ሎ/ – | አለው – | He has | ነበረው | He had |
| ቦ ላቲ /ላ/ – | አላት – | She has | ነበራት | She had |
| ቦ ሎሙ – | አላቸው – | They have | ነበራቸው | They had |
| ቦ ሎን –አላቸው – | | They have | ነበራቸው | They had |

ከዚህ ላይ የ«ለ» ዝርዝር ያለ «ቦ» የማለት ግስ በመሆን ያገለግላል:: ምሳሌ : – ሎሙ አላቸው፣ ለነ፣ አለነ፣ ለከ– አለህ፣ ለኪ አለሽ....

**5.4. ባለቤት ተውላጠ ስም** /Subjective Pronouns/ Reflexive pronouns/.

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዓጸ – | ሊየ /ለልየ/ – | እኔ ራሴ – | I my self |
| አንተ – | ለሊከ – | አንተ ራስህ – | You your self |
| አንቲ– | ለሊኪ– | አንቺ ራስሽ– | You your self |
| አንትሙ – | ለሊክሙ – | እናንተ ራሳችሁ– | You your self |
| አንትን – | ለሊክን – | እናንተራሳችሁ– | You your self |
| ንሕነ – | ለሊነ – | እኛ እራሳችን– | We our self |
| ውእቱ – | ለሊሁ – | እሱ ራሱ – | He him self |
| ይእቲ – | ለሊሃ – | እሷ ራሳ – | She her self |
| ውእቶሙ – | ለሊሆሙ – | እነሱ ራሳቸው– | They themselves |
| ወእቶን – | ለሊሆን – | እነሱ ራሳቸው– | They themselves |

ምሳሌ: – ለሊሁ ፈጣሪነ ተሰቅለ ለነ /ፈጣሪያችን እርሱ ራሱ ተሰቀለልን/
ለሊሁ እግዚአብሔር ፈጠረነ /እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ፈጠረን/
ለሊክሙ ማርታ ወአስቴር ሖርክን ኀበ ደብረ ታቦር /ማርታና አስቴር እናንተ ራሳችሁ ወደ ደብረ ታቦር ሄዳችሁ/

**5.5. <u>የ«ለ» ዝርዝር ተጨማሪ ትርጉም ጠቅለል ባለ መልኩ</u>**

ሊተ – ለእኔ፣ አለኝ፣ አለልኝ፣ ኖረልኝ፣ ነበረልኝ፣ ይገባኛል፣ እኔ እኔን
ለከ – ላንተ፣ አለልህ፣ ኖረልህ፣ ነበረልህ፣ ይገባሀል፣ አንተ፣ አንተን
ለኪ – ላንቺ፣ አለሽ፣ አለልሽ፣ ኖረልሽ፣ ነበረልሽ፣ ይገባሻል፣ አንቺ፣ አንቺን
ለክሙ – ለእናንተ፣ አላችሁ፣ አለላችሁ፣ ኖረላችሁ፣ ነበረላችሁ፣ ይገባችኋል፣ እናንተ እናንተን
ለክን – ለእናንተ፣ አላችሁ፣ አለላችሁ፣ ኖረላችሁ፣ ነበረላችሁ፣ ይገባችኋል፣ እናንተ፣ እናንተን
ለነ – ለእኛ፣ አለን፣ አለልን፣ ኖረልን፣ ነበረልን፣ ይገባናል፣ እኛ፣ እኛን
ሎቱ/ሎ – ለእሱ፣ አለው፣ አለለት፣ ኖረለት፣ ነበረለት፣ ይገባዋል፣ እሱ፣ እሱን
ላቲ – ለእሷ፣ አላት፣ አለላት፣ ኖረላት፣ ነበረላት፣ ይገባታል፣ እሷ፣ እሷን
ሎሙ –ለእነርሱ፣ አላቸው፣ አለላቸው፣ ኖረላቸው፣ ነበረላቸው፣ ይገባቸዋል፣ እነሱ፣ እነሱን
ሎን – ለእነሱ፣ አላቸው፣ አለላቸው፣ ኖረላቸው፣ ነበረላቸው፣ ይገባቸዋል፣ እነሱ፣ እነሱን

**ሌላው ዝርዝር**

ሎቱ/ሎ/ – ኖረው፣ ነበረው፣ አለው፣ ይኖረው ነበር፣ ይኖረዋል፣ ይኖረው ይሆናል::
ሊተ – ኖረኝ፣ ነበረኝ፣ አለኝ፣ ይኖረኝ ነበር፣ ይኖረኛል፣ ይኖረኝ ይሆናል:: ሌሎችም እንዲሁ ይዘረዘራሉ::
ምሳሌ: – /ከተሰመረባቸው/:–
ለከ ስብሐት – ምስጋና ላንተ /ይገባል፣ ይሁን/
ለኪ ስብሐት – ምስጋና ላንቾ /ይገባል፣ ይሁን/
ሎቱ ስብሐት – ምስጋና ለእሱ /ይገባል፣ ይሁን/

**ለ«ለ» ፊደል ጥቅም፣**

1. ለ = ለ፣
   ምሳሌ:= ስብሐት ለእግዚአብሔር = ምስጋና ለእግዚአብሔር
   = ምስጋና ለእግዚአብሔር ይገባል፣ ይሁን::
2. ለ = ን:- ለ=ን ተብሎ ሲፈታ ተሳቢ ይባላል::
   <u>በግስ ጊዜ፣</u>
   ስብሐ = አመሰገነ፣ አከበረ = አከበረ፣ ይቤ = አለ
   - ስብሕዎ ለእግዚአብሔር = እግዚአብሔርን አመስግኑት ::
   - አክብርዋ ለቤተ ክርስቲያን = ቤተ ክርስቲያንን አክብሯት::
   - ይቤልዎ አይሁድ ለኢየሱስ= አይሁድ ኢየሱስን /ለኢየሱስ/ አሉት:: ይህ አካሄድ ዝርዝር ይባላል::
3. ለ = የ፣ ለ፣ን /የለ ተጠቃሺነትና ተሳቢነት ፀዝርዝር ጊዜ/
   <u>በስም ጊዜ፣</u>
   ወልድ = ልጅ
   ምሳሌ= ወልዳ ለማርያም = ለማርያም ልጇ
   = የማርያምን ልጅ/ን/
   = የማርያምን ልጅ
   ወልዱ ለአዳም - ለአዳም ልጁ
   - የአዳም ልጁ

<u>ማስታወሻ:-</u> በ«ለ» ሲያያዙ የሚዘረዘር ወይም በአገናዛቢ የሚነገር መሆኑን ያስተውሉ:: ወይም ለአንስታይ የወልድ የመጨረሻ ፊደል ሣድስ ወደ ራብዕ ለተባእታይ የወልድ መጨረሻ ፊደል ሣድስ ወደ ካዕብ መለወጡን ያስተውሉ::
-በአጠቃላይ ለ=የ፣ን፣ ዘ፣ ተ፣ ወደ፣ አዳማቂ፣ ተቀባይ፣ አቀብሎ ሸሺ፣ ላይ፣ በ፣ ስለ፣ መሆን ይችላል:: */ይቀጥላል/::*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የኢትዮጵያና የምዕራባውያን የዘመን መለወጫ ልዩነት ምክንያት

መልአከ ኃይል ወ/ያሬድ መኩሪያ

ከሥነ ፍጥረት በመነሣት የቆጠርን እንደ ሆነ ዐውደ ዕለታት /ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉ ዕለታት/ ሰባት መሆናቸው አይካድም፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ሰባቱ ዕለታት ለወሮችና ለዓመታት መሠረት መሆናቸው እሙን ነው። ይኸውም እነዚህ ዐውደ ዕለታት ከሥነ ፍጥረት ታሪክ ጀምሮ በሰባት ዕለታት ስምና መደብ የቀመር መነሻ ሆነው ይገኛሉ። ዘጸ.20÷9-10።

ስለዚህ እነዚህ ከላይ በሰባቱ ዕለታት የተመደቡት ዕለታት በየሳምንቱ እየተመላለሱ 12 ወሮችን (ክፍለ ዘመናትን)፣ አራቱን ክፍለ ዘመናትና ዐውደ ዓመትን ያስገኛሉ ማለት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ወራት በፀሐይ በ30-በ30 ዕለት ተቀምረው 12 ወራት ተከትለው በየስማቸው ሲጠሩ 5 ቀን ከሩብ ደግሞ ጳጉሜን /በግእዙ ዕለተ ተውሳክ/ ተብላ መጠራቷ የታመነ ነው። ይሁን እንጂ ይህ አቀማመር ኖኅ ልጆቹን ይዞ ወደ መርከብ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑ አያጠራጥርም። ዘፍጥረት 7÷24፤8÷1-3።

የኖኅ ልጅ ካም ከወንድሞቹ ጋር ዕጣ በተጣጣለ ጊዜ ለካም አፍሪቃ በዕጣ ስለ ደረሰው፤ ይልቁንም የገባበት ወር /መስከረም/ በልምላሜና በአበባ ደምቆና አሸብርቆ በሚታይበት፤ ከዚህም ሌላ ሌሊትና መዓልት በሰዓት በሚተካከልበት (ዕሪና ሌሊት ዕሪና መዓልት) በሚሆኑበት ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በመግባቱ ዕንቁ የሆነች ዕጣ ወጥታልኛለች ሲል ዕንቁ ዕጣ ወጣሽልኝ በማለት ፈጣሪውን አመስግኗል። ከዚህ ሌላ የካም ልጆች እግዚአብሔር ለእስራኤል ይህ ነጻ የወጣችሁበት ወር የዓመት መጀመሪያ ይሁናችሁ እንዳላቸው ሁሉ የካም ልጆችም ይህንን ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን ወር የዓመት መጀመሪያ የአባታችን የካም መታሰቢያ ይሁነን ብለው ርእሰ ዓውደ ዓመት ብለው ሰይመውታል።

ይኸውም ከዚያ በፊት የቀን መቁጠሪያ ነበር ወይ? የሚል ጥያቄ ቢኖር፦ የመጀመሪያው ሰው አዳም በዲያብሎስ ተንኮል እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ገነትን ያህል ቦታ አጥቶ ወደዚህ ዓለም በተሰደደ ጊዜ በፈታሒነቱ አንጻር መሐሪነቱን አምኖ ከፈጣሪው ለመታረቅ ንስሐ ገባ። ንስሐ የገባበት 40 ቀን ሳይሞላ በ35ኛው ቀን ሱባኤውን ሳይፈጽም ሰይጣን መልአክ መስሎ ቀርቦ ፈጣሪህ ይቅር ብሎሃል ውጣ አለው። እርሱም ወጣ፤ ከዚያም በኋላ መሥዋዕት ሠዋ። ነገር ግን ጌታ በአንተ መሥዋዕትነት አይደለም ዓለም የሚድነው፤ ይኸውም አንተ እኔን መሆን አትችልም፤ እኔ ግን አንተን መሆን እችላለሁ ካለው በኋላ "በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድኅክ ውስተ መርህብከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበሞትየ" ብሎ በሰጠው የተስፋ ቃል ኪዳን መሠረት ሱባኤ ዕለታትን በዓመት፣ ሱባኤ ዓመታትን በዓውደ ቀመር መቆጠር ጀመረ። ቀመረ አዳም የተባለ 532 ዓመት ነው። እምአመ ተሰደ አዳም እምገነት እስከ አመ አስተርአየ ክርስቶስ እግዚእነ ወበ ፶፻ወ፭፻ቱ፻ /5500/ በሥጋ ዓመት ወተፈልጦተ ዝንቱ ይነግር ክሡተ እምአዳም "የሚል አብነት ይገኛል። የእኛና የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት÷ እኛ ከገነት የተሰደደበትን ይዘን በመነሣታችን ሲሆን እነርሱ ደግሞ ከተፈጠረበት ጊዜ አንሥተው በገነት የኖረበትን ሰባት ዓመት ጨምረው ስለሆነ ነው።

ይህንንም አቆጣጠር ለልጆቹ በሕገ ልቡና እስከ ኖኅ ድረስ ላሉት ትውልድ ማስተላለፍን ለምሳሌ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜና ሰዓት አንሥቶ ጥንታውያን ሕዝቦች ከመበታተናቸው በፊት ሲጠቀሙበት ኖረው ኋላ የተዉት ነባር አቀማመር እያንዳንዱ ወር በ30 በ30 ቀን መድቦ የመጠቀም ሁኔታ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ይኸውም የጥፋት ውኃ በሆነ ጊዜ ኖኅ መርከብ ሲገባ "ውኃው 150 ቀን አሸነፈ" ይላል። እነዚህ 150 ቀኖች መሆናቸው በ5-30 ሲመደብ ልክ 5 ወር መሆናቸውን ያሳያል። ትርፍ የለበትም (ዘፍ.7÷11-13፤8÷3-7)። እንግዲህ ዓመተ አዳምና ዓመተ ኖኅ የተባለውን አቀማመር ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ሕገ ኦሪት ሳይጻፍ በሕገ ልቡና ሲጠቀሙበት የቆዩትን ያህል በኋላ ግን በየጊዜው በሚነሡት ፈላስፎችና አምባገነን ገዥዎች ምክንያት እየተዉ ሲሄዱ ኢትዮጵያና ግብፃውያን ሌሎችም ኦርቶዶክሳውያን የጥንቱን ማለት ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት ተገልብጦ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘውን አለቀቁም። ኢትዮጵያውያን ይህንን መሠረት በማድረግ 12ቱን ወሮች በ30 በ30 ቀን ቀምረው ያለ ምንም ትርፍ ማለት አንዳንድ ጊዜ 31 አንዳንድ ጊዜ 23 ሳያደርጉ ልክ በ30 በ30 ቀን መድበው 12 ወር አድርገው ሲሠሩባቸው ኖረዋል።

የመስከረም ወር ዘመን መለወጫ ስለ መሆኑ፤ "መስከረም" ማለት ስመ ወርኀ ከመሆኑም በላይ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከዘመነ ሥጋዌ በፊት በዓለም ሁሉ የወርና የዓመት መጀመሪያ ነበር። ይኸውም ሊታወቅ በመጀመሪያ ብሉይ ኪዳንን በተቀበሉ በአይሁድ ዓውደ ዓመትና በበዓለ መጥቅዕ መሠረትነት የታቀፈ መሆኑ ይታወቃል።

ከዚህም ሌላ መስከረም የክረምት ጫፍ መጨረሻ የመጸው መባቻ ከመሆኑም በላይ መዓልቱና ሌሊቱ የሚስተካከልበት ማለት ትክክል የሚሆንበት ወር ነው። ስለዚህ ይህን መቅድመ አውራኅ ርእሰ ዓውደ ዓመት ብለው ሰይመውታል። "ውእቱ ርእሰ ዓውደ ዓመት ዘአይሁድ ዘግብጽ ወዘኢትዮጵያ" የሚል አብነት ይገኛል። ስለዚህ የጥንቱን ሐሳበ ዘመን በብሉይ ኪዳን የተጻፈውን ይዛ ጠብቃ መኖሯዋን ያሳያል።

በተለይ ስለ አውሮፓውያን ዘመን መለወጫ ወይም የዘመን አቆጣጠር ዘይቤ የተባለው በመጀመሪያ የተመሠረተውን ዓለም ይጠቀምበት የነበረውን የእስያዎችን ካላንደር ትክክል አይደለም በማለት ጁልያን የሚባለው ከአውግስጦስ ቄሣር በፊት በ46 ዓ.ዓ. አካባቢ የነበረውን ወገቡን ታጥቆ በመነሣት የወቅቶችና የቀናት ሂደት አለመጣጣም በመጠኑ ለማረም የግብፁን ሥነ ፈለክኛ /አስትሮኖመር/ የሶኒጀኒስን ቅመራ ወደርሱ በማስመጣት ዓመቱን በ365 ቀናትና በ12 ወራት ከፋፈለው። አምስቱን ቀኖች እንደ ግብፅ እንደ ግሪክና እንደ ኢትዮጵያውያን ጳጉሜን የሚያወጣ ባይኖር በመጋቢትና በግንቦት በሐምሌና በጥቅምት ላይ እንዲደረቡ ከማድረጉም በላይ ሌላውንም በማሻሻል በአራት ዓመት የምትገኘውን አንድ ቀን ጨምሮ ያመቱን ቀናት 366 እንዲሆን አደረገ።

ከዚህ በኋላ ይህ ዛሬ በመላው አውሮፓ የቀዳማዊ ክርስትና ዘመን ቁጥር መነሻ ወቅት ተብሎ የሚሠራበት ሲሆን ይህን ካላንደር የሚቃወም ቄስ ፓናይረስ የሚባል ከግብፃውያን የዘመን አቆጣጠር ዘይቤና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማገናዘብ በ412 ዓ.ም አዲስ የዘመን መቁጠሪያ አወጣ።

በዚህ ሊቅ ትጋት መሠረት የዓመተ ዓለምን የተዛባውን ለማቃናት በጁልያን አቆጣጠር ነሐሴ 29 ቀን 5ሺ493 ዓ.ዓ ነው ብሎ የመደበው። ይህ ቀን ወደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሲለወጥ መስከረም አንድ ቀን 5493 ዓ.ዓ ይሆናል። ይሁን እንጂ የዚህ ሊቅ ተቃራኒ የሆነ ቄስ እንያኖስ የሚባል ሰው የዓመተ ዓለምን መጀመሪያ ወደ መጋቢት 25 ቀን 5ሺ492 ዓ/ም ከወሰደው በኋላ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን የፓናይረስን ቀመር ተቀብላ በሥራ ላይ አዋለች። ስለዚህ ነው የአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር ከግብፅና ከኢትዮጵያ የዘመን መቁጠሪያ ካላንደር የሰባት ዓመትና የወራት ልዩነት የመጣው። ይኸውም አውሮፓውያን የዓመተ ምሕረትን መነሻ ከክርስቶስ ልደት ለማቀራረብ ሲሉ ከብዙ ክርክር በኋላ ጥር አንድ ቀን 5ሺ507 ዓ.ዓ ብለው በካላንደር ውስጥ ሲያገቡ ኢትዮጵያና ግብፅ ግን አዳም ከጥንተ አብሶ በፊት በገነት የኖረበትን ሰባት ዓመት በመቀነስ መስከረም አንድ ቀን 5ሺ500 ዓ/ዓን የዓመተ ምሕረት መነሻ አድርጋለች። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ሰባት ዓመት ሊቀነስ ችሏል።

ምንጭ፦ ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ÷ ቁ.9÷1987 ዓ.ም÷ ገጽ 12–14።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org


## ማኅበረ ቅዱሳን የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ


- የካህናት አልባሳት
- የመዘምራን ልብስ
- ጧፍ፣ ዕጣን፣ ዘቢብ
- ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች አልባሳት
- በተክሊል ለሚጋቡ ሙሽሮች የካባ ኪራይ
- ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት

የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓት ጠብቀን ቀጠሮ አክብረን በተመጣጣኝ ዋጋ በጥራት እንድናዘጋጅልዎ ይጎብኙን።

አድራሻ:- አዲስ አበባ ከገነተ ጽጌ/አራዳ/ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ወደ 6 ኪሎ በሚወስደው መንገድ መቅደላ ሆቴል አጠገብ።

☎56 67 88 ✉ 80087




### አዲስ መጽሐፍ
### "አዋልድ መጻሕፍት እና መንፈሳዊነት በግቢ ውስጥ"

- በኅብረተሰብ ውስጥ በብሔረሰብ፣በባሕል፣ በጠባይ፣ በዕውቀት፣ በገንዘብ አቅም፣ በቦታ ወዘተ. ያለውን መለያየት አቻችሎ እንዴት በመንፈሳዊ ሕይወት መኖር እንደሚቻል ።
- በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ የተለያዩ ፈተናዎችን በማሳየት ዝርዝር መፍትሔዎችን ይጠቁማል።
- የአዋልድ መጻሕፍት ትርጓሜን ይጠቁማል።
- የአሥራው መጻሕፍትን የአዋልድ መጻሕፍት ግንኙነት ይጠቁማል።
- የአዋልድና የአሥራው መጻሕፍት የይዘት አንድነትን ይጠቁማል።
- የአዋልድ መጻሕፍት አከፋፈልን ዘርዝሮ ይጠቁማል።

አዘጋጅ የማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል
ዋጋ ብር 4.00

በሁሉም የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኛሉ።
ስልክ 56 51 59


ዋጋ ብር 3.50

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡